አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

# የሐጅ ሁሴን ዓለሙ (የነሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በአል ስርዓትና ቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ክዋኔ ጥናት

በ

አብዱራህማን ፈንታሁን

ሰኔ 2006 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ**

# የሐጅ ሁሴን ዓለሙ (የነሺህ ዳንግላ) የመውሊድ በአል ስርዓትና ቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ክዋኔ ጥናት

**በ**

**አብዱራህማን ፈንታሁን**

**የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት ለአማርኛ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር የቀረበ ጥናት**

**አማካሪ**

**ሰላማዊት መካ (ረዳት ፕሮፌሰር)**

**ሰኔ 2006 ዓ.ም.**

**አዲስ አበባ**

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

# የሐጅ ሁሴን ዓለሙ (የነሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በአል ስርዓትና ቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ክዋኔ ጥናት

በ

አብዱራህማን ፈንታሁን

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| ………………………………………………. | …………………….. |
| አማካሪ | ፊርማ |
| ………………………………………………. | …………………….. |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |
| ………………………………………………. | …………………….. |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |

## ምስጋና

ጥናቱ ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው አቅጣጫ በመስጠትና በማረም ይህን ቅርጽ ይዞ እስኪወጣ ድረስ ከፍተኛ እገዛ ያደረገችልኝን አማካሪዬ ወ/ሮ ሰላማዊት መካን ከማንም በላይ አመሰግናታለሁ፡፡

በሁለት ዙር የመስክ ሥራዬ ያለ አንዳች ማቅማማት በቂና ዝርዝር መረጃዎችን በማቀበል ይህን ጥናት ሙሉ አካል ያደረጋችሁት የዳንግላ ከተማ ነዋሪዎችና የበአሉ ተሳታፊዎች ከፍ ያለ ምስጋና ይገባችኋል፡፡ በተጨማሪም መረጃዎችንና ፎቶዎችን በመሰብሰብ ለተባበርከኝ ታላቅ ወንድሜ ጀማል ፈንታው የዚህ ጥናት ልዩ ደጋፊ ነህና ኩራት ሊሰማህ ይገባል፡፡

የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና መረጃ በመስጠት ለተባበራችሁኝ የዳንግላ ከተማ አስተዳድር ሰራተኞች ከልብ አመሰግናችኋለሁ፡፡

እድሜየን ሙሉ እገዛ ላደረጋችሁልኝ ቤተሰቦቼ (በተለይ ፈንታውየና እባባየ) ልዩውን ምስጋና ውሰዱ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የዳንግላው ሼህ ሁሴን አለሙን የመውሊድ ክብረ በአል እና በመውሊዱ ላይ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ በጥናቱ የተነሱ ሁለት ዋና የምርምር ጥያቄዎች የሐጅ ሁሴይን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ ስርዓተ ክዋኔ ምን ይመስላል? እና በመውሊድ ስርዓተ ክዋኔው ላይ የሚቀርቡት ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ ከሐይማኖታዊ ገጽታቸው ባሻገር ምን አይነት ፎክሎራዊ ገጽታ አላቸው የሚሉ ናቸው፡፡ ከቤተ መጻህፍት በተገኙ ስራዎች እና የጥናት ወረቀቶች ላይ ንባብ የተካሄደ ሲሆን ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ እና የቡድን ውይይትን በመጠቀም ከመስክ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

በዚህም መሰረት የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ ስርዓተ ክዋኔ ምን ይመስላል? ለሚለው መሰረታዊ ጥያቄ የመውሊድ በአሉ የየራሳቸው ዓላማ ያላቸው ሁነቶች ድምር ውጤት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመውሊድ በዓሉ የአከባበር ስርዓት ላይ በዋናነት የተስተዋሉትን የክዋኔ ሁነቶች ዚያራ፣ ዱኣ፣ ምርቃት እና መንዙማ ናቸው፡፡ የነዚህ ሁነቶች አጠቃላይ መጠሪያ "ሐድራ" ሲሆን "ዱኣ" የሚለውን ምትክ እንደሆነ በጥናቱ ተጠቁሟል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሁነቶቹ አንዱ ከአንዱ ጋር ጥብቅ የሆነ ቁርኝት ያላቸው እንደመሆናቸው ተሳታፊዎቹም ይህንን አውቀው ይፈጽሟቸዋል፡፡

በዚህ ጥናት በሁለተኛነት የተነሳው ጉዳይ በመውሊድ ስርዓተ ክዋኔው ላይ የሚቀርቡት ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ ከሐይማኖታዊ ገጽታቸው ባሻገር ምን አይነት ፎክሎራዊ ገጽታ አላቸው? ለሚለው መሰረታዊ ጥያቄ የመንዙማ ግጥሞች በተከወኑበት የክዋኔ ሒደት (በሐድራው ላይ በሚቀርቡበት መንገድ) አንጻር በሁለት መንገድ (በድቤና በእንጉርጉሮ) እንደሚባሉ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት በድቤ የሚቀርቡት ክዋኔያቸው አሳታፊ ሲሆን በእንጉርጉሮ በሚቀርቡት ላይ ግን ታዳሚዎቹ ከዋኙን ማድመጥ ሚናቸው መሆኑን ለማዎቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከመንዙማዎቹ ክዋኔ ጋር በተገናኘ የቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች (ድቤ፣ የድቤ መምቻና ከበል) በክዋኔው ሂደት ካላቸው ሚና አንጻር፤ ለመንዙማ ግጥሞቹ ክዋኔ የሚሰጡት ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ለማዎቅ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ የመንዙማ ግጥሞች በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ከማኅበራዊ፥ ታሪካዊ፥ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ጠቀሜታ በተጨማሪ ያላቸው ባህላዊ፣ ፎክሎራዊና ኪነ ጥበባዊ ዋጋ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ወደፊት ሰፋ ባለ ጥናት ቢጠኑ መልካም ነው የሚል ጥቆማ በመስጠት ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

## ማውጫ

1. መግቢያ ........ 8
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 9
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 10
1.3 የጥናቱ ዓላማ ........ 11
1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 11
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 12
1.6 የጥናቱ ትወራ እና የአጠናን ዘዴ ........ 12
1.6.1 የጥናቱ ትወራ ........ 12
1.6.2 የአጠናን ዘዴ ........ 14
1.6.3 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ........ 16
1.7 የመስክ ጥናት ተሞክሮ እና ገጠመኝ ........ 16
1.7.1 የመስክ ተሞክሮ ........ 16
1.7.2 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 19
2. ክለሳ ድርሳን ........ 21
2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ........ 21
2.1.1 ክብረ በአል ........ 21
2.1.2 ክዋኔ ........ 23
2.1.3. አውድ ........ 25
2.1.3.1 ባህላዊ አውድ ........ 26
2.1.3.2.ማህበራዊ አውድ ........ 27
2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 28
2.2.1 በማስተርስ ዲግሪ የቀረቡ ተዛማጅ ጥናቶች ........ 29
2.2.2 በመጀመሪያ ዲግሪ የቀረቡ ተዛማጅ ጥናቶች ........ 32
2.2.2.1 ቅኝት ያልተደረገባቸው ተቀራራቢ ጥናቶች ........ 32
2.2.2.2 በኡለማ መዉሊድ ስርዓተ ክዋኔና በስርአቱ ላይ በሚቀርቡ ቃላዊ ግጥሞች_ላይ ያተኮሩ የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች፣ ........ 32
3. ጥናቱ የተካሔደበት ማህበረሰብ አካባቢያዊ ዳራና የሼህ ሁሴን አለሙ የሕይወት ታሪክ........31
3.1 ጥናቱ የተካሔደበት አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ ........ 37
3.2 የዳንግላ ከተማ አሰያየምና አመሰራረት ........ 38
3.3 የነሼህ ዳንግላ (ሐጅ ሁሴን አለሙ) መስጅድ አመሰራረት ........ 40
3.4 የሐጅ ሁሴን አለሙ የህይወት ታሪክ........ 43

3.5 የመውሊድ ክብረ በአል ምንነትና አይነት ........ 46
3.6 የሼህ ሁሴን አለሙ (የነሼህ ዳንግላ) መውሊድ ታሪካዊ አጀማመር ........ 48
4. የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በአል ስርአትና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ ........ 50
4.1 የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በአል ስርአተ ክዋኔ ........ 50
4.1.1 የሥርዓተ ክዋኔው ቅድመ ዝግጅት ........ 50
4.1.2 የሥርዓተ ክዋኔው ዋዜማ ........ 52
4.1.3 የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓል አከባበር ስርዓት ........ 57
4.1.3.1 ዚያራ ........ 58
4.1.3.2 ዱኣ (ምርቃት) ........ 61
4.1.3.3 መንዙማ ........ 67
4.1.4 የክዋኔው ማግስት ........ 68
4.2 በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ ክብረ በአል ላይ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞችና ቃላዊ ግጥሞቹን ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች ........ 70
4.2.1 በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ ክብረ በአል ላይ የሚከወኑ መንዙማዎች ... 70
4.2.2 በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ ክብረ በአል ላይ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች ........ 81
4.3 የመውሊድ ክብረ በአል ተግባር ........ 84
5. ማጠቃለያና አስተያየት ........ 86
5.1 ማጠቃለያ ........ 86
5.2 አስተያየት ........ 88
ዋቢ ጽሑፎች ........ 89
ሙዳዬ ቃላት
አባሪዎች

## 1. መግቢያ

እስልምና በ7ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነቢዩ ሙሀመድ መልዕክተኞች አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ጀምሮ (Trimingham 1952, 42) እስከ አሁን ድረስ በርካታ ዓመታትን አስቆጥሯል። በዚህ ረጅም ጊዜ የኡለማ (የዓሊም) መውሊድ በተለያዩ ቦታዎች ሲከበር ኖሯል። በተለያዩ ቦታዎች መከበሩ ደግሞ አልፎ አልፎ ክዋኔ ስርአቱ ላይ ልዩነት እንዲስተዋል አድርጎታል።

ይህ ክብረ በአል እምነታዊ በሆነ ገጽታው ተመሳሳይ ቢሆንም፤ ያከዋወን ስርዓቱ ግን እንደ አካባቢው የባህል፣ የአኗኗር እና የአስተሳሰብ ዘይቤ በተወሰነ መልኩ ልዩነት ሲፈጥር ይስተዋላል። እነዚህ ልዩነቶች ደግሞ የማህበረሰቡ የባህልና የአኗኗር መገለጫ ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላሉ። የዚህ የጥናታዊ ጽሁፍ ትኩረት በዳንግላ ከተማ በሚከበረው የሐጅ ሁሴን አለሙ (የነሼህ ዳንግላ)[1] የኡለማ መውሊድ በዓል ላይ ባሉት ስርዓተ-ክዋኔና ቃላዊ ግጥሞች ሲሆን በጥናቱም የክብረ በዓሉን የአከባበር ስርዓተ-ክዋኔ እና ማህበራዊ ፋይዳውን በአውድ በመመስረት ተዳሶ ቀርቧል።

በዚህም መሰረት ጥናቱ በአምስት ምዕራፎችን ይዞ ተደራጅቷል። በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን አካሄድ ማለትም፤ የጥናቱን ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ አላማ፣ አስፈላጊነት፣ ወሰን፣ የአጠናን ዘዴ እና አደረጃጀት ይዟል። በምዕራፍ ሁለት ደግሞ የተዛማጅ ጥናቶች እና ርዕሰ ጉዳዩን የሚመለከቱ ትውራዊ ቅኝቶች ቀርበዋል። ምዕራፍ ሶስት ጥናቱ የተካሔደበትን ማህበረሰብ ታሪካዊና መልካዓምድራዊ ዳራ፣ የመውሊድ በአል ምንነት፣ የሼህ ሁሴን አለሙ የህይወት ታሪክ፣ የመውሊዱ አጀማመርና የመስጊዱ አመሰራረት ተጨምቆ የቀረበበት ክፍል ሲሆን በምዕራፍ አራት ደግሞ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ መሠረት በማድረግ በዓላማው ላይ የተገለፁትን ነጥቦች ከግብ በሚያደርስ መልኩ ሰፊ ትንታኔና ሐተታ ቀርቧል። ይህ ምዕራፍ

[1]በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ **እነሼህ ዳንግላ** የሚለው አገላለጽ ሼህ ሁሴን አለሙን ለመግለጽ ሲሆን ይህንንም መጠሪያ የከበራው ተሳታፊዎች የሚገለገሉበት መሆኑን ለመጠቆም እወዳለሁ። መጠሪውን የሚጠቀሙበት ዋና ምክንያት ደግሞ ሐጅ ሁሴን አለሙ በህይወት ዘመናቸው ለህብረተሰቡ ያበረከቱት አስተዋጾ (ለዳንግላና አካባቢው ማህበረሰብ ቁርኣን እና ሀዲስ ማስተማር፣ እስልምና የሚከለከክላቸውን የአምልዕኮት ተግባራትን መከልከል (በጠንቋይ ከአላህ ጋር በማሻረክ ያምኑ የነበሩትን ሰዎች ወደ እስልምና መመለሳቸው)፣ የተለያዩ በሽታዎችን በዱዓ (በጸለት) እና በተህሊል (በቅዱስ ውሃ) መፈወሳቸው፣ የአረሶ አደሩን ሰብል ከድርቅ እና ከበረዶ በዱዓ በመጠበቅ) በህብረተሰቡ (በሙስሊሙና በክርስቲያኑ) ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታንንና ውዴታን ማግኘታቸው እነ በሚል (አንድ ሁነው እንደብዙ) እንዲጠሩ እንዳስቻላቸው በጥናቴ ወቅት ለመረዳት ችያለሁ።

የጥናቱ ዋና የትንታኔ ክፍል ነው። ፤ በመጨረሻውና በአምስተኛው ምዕራፍ ደግሞ ከጥናቱ አጠቃላይ ትንታኔ በመነሳት ማጠቃለያና መደምደሚያ የቀረበበት ክፍል ነው።

በመጨረሻም ዋቢ መጻሕፍት እና ሌሎች አባሪዎች ከማጠቃለያው በኋላ ቀርበዋል። ከዚህ በተጨማሪም በይዘታቸው አዲስነት ያላቸው ሐሳቦች፣ ውክልናቸው አረበኛ የሆኑ ቃላት፣ ለተጨማሪ ንባብ የሚያገለግሉ ጽሑፎች፣ የጥናቱን የማጠንጠኛ ሐሳብ የሚደግፉ ነጥቦች፣ የጥናቱ የመረጃ ምንጮች እና ለሌላ ጥናት መነሻ የሚሆኑ ጉዳዮች በግርጌ ማስታወሻ መግለጫ ተሰጥቶባቸዋል።

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

መውሊድን በሚያከብሩ የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ሁለት አይነት የመውሊድ ክብረ በአላት አሉ። አንደኛው ክብረ በዓል የረቢል አወል መውሊድ (የነብዩ መሐመድ የልደት በዓል) ሲሆን ይህም የሂጅራ የዘመን አቆጣጠርን የሚከተል ነው። ሁለተኛው የመውሊድ አይነት የኡለማ መውሊድ (ኡለማን መሰረት በማድረግ የሚከበር ነገር ግን ነብዩ መሐመድና እስላማዊ አስተምሮዎች የሚቀርቡበት) ሲሆን ይህም በእምነቱ ዘንድ ታላቅ የሚባሉ ዓሊሞች (አዋቂዎች) በህይወት በነበሩበት ወቅት ከህብረተሰቡ ጋር የነበሩትን ታላላቅ ግለሰቦች ለማሰብ የሚከበር መውሊድ በመባል ይከፈላሉ። በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍም የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓልን መሰረት በማድረግ የሚከበረውን የመውሊድ በዓል (የኡለማ መውሊድን) አከባበር ስርዓት፣ ክዋኔውን ሁነቶች እንዲሁም ማህበራዊ ፋይዳውን አውዱን መሰረት በማድረግ ተዳሶ ቀርቧል።

ከዚህ ቀደም የኡለማ መውሊድን መሰረት በማድረግ የተሰሩ ውስን የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች መኖራቸው ለዚህ ጥናት ዝግጅት በማደርግበት ወቅት በተለያዩ የዩኒቨርሲው ቤተ መጻህፍቶች ለማስተዋል ተችሏል። ከነዚህም በተጨማሪ በኤም.ኤ ደረጃ ከተሰሩ ጥናታዊ ጽሑፎች መካከል በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መልኩ ከኔ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሁለት ጥናቶች ተገኝተዋል። እነዚህም የአሰፋ ማሞ (1987) "Some Prominent Features of Menzuma in Wollo Region" እና የብርሀኑ ገበየሁ (1990) "Islamic Oral Poetry in Wollo a Prelimainary Descriptive Analysis" ናቸው። እነዚህ ሁለት ጥናቶች በመውሊድ ላይ የሚቀርቡ የቃላዊ ግጥሞችን (መንዙማዎችን) ክዋኔ አውዱን መሰረት በማድረግ የቀረቡ ናቸው።

በአጠቃላይ ከላይ የጠቀስኳቸውን ቀደምት ጥናታዊ ጽሑፎች በማስተዋል ይዤው የተነሳሁት ርዕሰ ጉዳይ የጥናት ደረጃ ምን ያህል እንደደረሰ ማወቅ ይቻላል፡፡

እኔም ከዚህ በመነሳት የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓልን መሰረት በማድረግ የሚከበረውን የመውሊድ በዓል (የኡለማ ሞሊድን) አከባበር ስርዓት፣ ክዋኔውን እንዲሁም ማህበራዊ ፋይዳው፤ አውዱን መሰረት በማድረግ ተጠንቶ ቀርቧል፡፡ በዚህም በሌሎች ጥናት ላይ በስፋት ያልተስተዋለውን የከበራው ስርአትና የሁነቶች ትስስር፣ የክዋኔው ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳ እና የሚፈጸሙ ድርጊቶችን እንዲሁም ቃላዊ ግጥሞቹን (መንዙማዎቹን) ላይ ዳሰሳ ተደርጓል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማድረግ ያነሳሳኝ መሰረታዊ ምክንያት ከላይ በዳራው ላይ እንደገለጽኩት የኡለማ መውሊድን (የግለሰብ መውሊድን) በተመለከተ የተደረጉ ጥናቶች የሉም በሚባሉ ደረጃ ላይ መሆናቸው ነው፡፡ የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓልና ስርአተ ክዋኔ በውስጡ ሀይማኖታዊ መልኮች ቢኖሩትም ከሀይማኖቱ አስተምህሮት ጎን ለጎን ልዩ ልዩ ፎክሎራዊ ገጽታዎችን ይዟል፡፡ ፎክሎራዊ የሆኑትን ጉዳዮች በመለየት ማጥናቱ በትምህርት ክፍሉም ሆነ በመስኩ ያለውን ክፍተት ለመሙላት በሚደረገው ጥረት አስተዋጽኦ እንደሚኖረው እሙን ነው፡፡ ስለዚህ ጥናቱን ለማድረግ ተነሳስቻለሁ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ይህ (እኔ የማጠናው) የኡለማ መውሊድ በአካዳሚው አለም እስካሁን አልተጠናም፡፡ አለመጠናቱ የጥናቱ ትኩረት እንዲሆን ያስቻለ አንዱና መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ የሼህ ሁሴን አለሙ የህይወት ታሪክ ምን ይመስላል፤ የመውሊድ በዓሉ አመሰራረት እና አጀማመር፣ በከበራው ላይ ያሉት ስርዓቶቹና ሁነቶች ትስስር ፣ ከልዩ ልዩ ቦታ የሚመጡ ምዕመናን ላይ ያለውን ተጽዕኖ ማጥናቱ ክብረ በአሉን እንዲታወቅ ያደርጋል፡፡ ይህን በማሰብም ለጥናቱ እንድነሳሳ አድርጎኛል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ይህንን የጥናት ርዕስ በመምረጥ ለመመረቂያ ርዕስነት ያዋልኩበት ምክንያት ጥናቱ የሚመለከታቸው ማህበረሰቦች እምነት ተከታይ በመሆኔ የምፈልገውን ጥናት ለማካሄድ የቋንቋና የባህል ልዩነት ስለማይገጥመኝ ጥናቱን ለማጥናት የተሻለ እድል ስለሚፈጥርልኝ በማሰብ ነው፡፡

### 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓል ስርዓተ ክዋኔና ቃላዊ ግጥሞችን ከአውዳቸው አንጻር ትንታኔ መስጠት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- በዳንግላ ከተማ የሚከበረው የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ ስርዓተ ክዋኔ ምን እንደሚመስል በሁነቶች ላይ በመመስረት የክዋኔውን አውድ ማብራራት፤
- በስርዓተ ክዋኔው ላይ የሚቀርቡት ቃላዊ ግጥሞች እንዴትና ለምን እንደሚቀርቡ ተግባራቸውን በአውድ በመመስረት ማሳየት፤
- የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) መውሊድ ተሳታፊዎች ለበዓሉ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሆነ መግለጽ፤
- የስርዓቱ ተሳታፊዎች በስርዓቱ ላይ መገኘታቸው የሚያስገኝላቸው ጠቀሜታ ማብራራት የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ጥያቄዎች በጥናቱ ይመለሳሉ፡፡

- በሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ ስርዓተ ክዋኔ ላይ ታዳሚዎች እንዴት ይሳተፋሉ? ይህ ተሳትፏቸውስ የሚያስገኝላቸው ፋይዳ ምንድን ነው?
- የመውሊድ ስርዓተ ክዋኔ ላይ ምን ምን ነገሮች ይነሳሉ? ወይም ስርዓተ ክዋኔው የምን የምን ሁነቶች ድምር ውጤት ነው?
- ለሁነቶቹ መፈጠርና መከወን ምክንያቶቹ ምን ምን ናቸው?
- ተጠኝው ህብረተሰብ ለስርዓተ ክዋኔው የሚሰጠው ትርጉም ምንድን ነው?

### 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል፡

- የመውሊድ በዓሉ የሚከበርበትን ባህላዊና ማህበራዊ አውድ ማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች እንዲረዱት ያስችላል፡፡
- በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርግ ተመራማሪ መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡
- የአጥኝው የመስክ ተሞክሮ ለሌሎች ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች ይረዳል፡፡

- የበዓሉ ክዋኔ መጠናት ለፎክሎር ጥናት መስክ አንድ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

### 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ አንፃር በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በአዊ መስተዳድር ዞን በዳንግላ ከተማ ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ከሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ አንፃርም ከእምነት ጋር ተያይዞ የሚነሳውን ሐይማኖታዊ ከበራ በዳንግላ የሼህ ሁሴን የመውሊድ በዓል ላይ መሠረት አድርጎ የተቃኘ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓል ስርዓተ ክንዋኔና ቃላዊ ግጥሞችን ክዋኔን በተፈጠረበት፥ ባደገበትና አገልግሎት በሚሰጥበት ማህበራዊና ባህላዊ አውድ ተንትኖ በማቅረብ ከተግባራቸው አንጻር ትንታኔ በመስጠት ላይ የተወሰነ ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ትወራ እና የአጠናን ዘዴ

### 1.6.1 የጥናቱ ትወራ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓል ስርዓተ ክንዋኔና ቃላዊ ግጥሞችን ከአውዳቸው አንጻር ትንታኔ መስጠት እንደሆነ ቀደም ሲል ገልጫለሁ፡፡ አላማዬን ከግብ አደርስ ዘንድ ስለ ክብረ በአላት ምንነት እና ባህሪ የሚያስረዱ የተለያዩ ተመራማሪዎችን ስራዎች በግብአትነት ተጠቅሜያለሁ፡፡

ይህን ጥናት ለማካሔድ የምጠቀመው ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ አውዳዊ አቀራረብን (Contextual Approach) ወይም ክዋኔ ተኮር አቀራረብ (Performance Centered Approach) ነው፡፡ ምክንያቱም የሼህ ሁሴን የመውሊድ በዓል ክዋኔን በተፈጠረበት፥ ባደገበትና አገልግሎት በሚሰጥበት ማህበራዊና ባህላዊ አውድ ተንትኖ ለማቅረብ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ ይህንንም በተመለከተ Ben-Amos (1974) ቴክስትን ከአውድ ነጣጥሎ መመልከት አስቸጋሪ እንደሆነ ሲያስረዳ "The *meaning of a text is its meaning in context... In terms of contextual analysis there is no dichotomy between text and context.* (1993, 209) በማለት ይገልጻል፡፡ በዚህም መሰረት ቴክስትን ከአውድ ነጥሎ መመልከቱ እምብዛም ትርጉም የሚሰጥ አይደለም፡፡ ይህም ማለት በመውሊዱ በዓል ላይ የሚደረጉ ስርዓቶችንም ሆነ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞች እንዲሁ ብናቀርባቸው የተሟላ ስሜት ላይሰጡ ይችላል፡፡ ነገር ግን በተከወኑበት አውድ ውስጥ እያስገባን ስንመለከታቸው እንዲሁ ከቀረቡት የበለጠ ነፍስ የሚዘሩ ይሆናል፡፡

ስለዚህ የሼህ ሁሴን ዳንግላንም የመውሊድ በዓል ስርዓቶች ከሚከወኑበት ማህበራዊና ባህላዊ አውድ አንጻር መተንተንና ትርጓሜ ላይ መድረስ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ክዋኔ ተኮር አቀራረብ የሚፈልጋቸውን ስነ-ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም በማስመልከት Bauman (1983) በበኩሉ አንድ ጉዳይ በዚህ አቀራረብ ሲጠና ጉዳዩ እንዴት እና የት ተከወነ? ቅንጅቱ እንዴት ነው? እነማን ነበሩ? ስርአቱ ምን ይመስላል? ተደራሲው እንዴት ምላሽ ይሰጣል? የሚሉ ጉዳዮችን አጽእኖት ሰጥቶ ማጥናት አለበት ይላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ፎክሎር ያለ ክዋኔ እንደማይገለጽና ህልውና ሊኖረውም እንደማይችል (Finnegan 1977, Rappaport 1999) ያስረዳሉ፡፡ የአራቱ ምሁራን ንድፈ ሐሳባዊ ጥቆማ በምእራፍ ሁለት የሚካተቱት ሌሎች ሀሳቦች ጥናቱ ምን ላይ ማተኮር እንዳለበት አመላክተዋል፡፡ ለአብነት ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ ብንመለከት ጥናቱ በመውሊድ ስርአቱ ላይ ብቻ ሳይወሰን በስርአቱ አማካይነት የታዳሚውን እሴት አመለካከት እና እምነት ምን እንደሚመስል ለማሳየት እንዲሞከር ሆኗል፡፡ እኔም ከዚህ ነጥብ በመነሳት በጥናቱ ወቅት የሚከተሉትን መሰረታዊ የትኩረት አቅጣጫዎች በጥያቄ መልክ በማንሳት ጥናቴን አካሒጃለሁ፡፡

- ✓ የትኛው ክብረ በዓል ለምን ይከበራል?
- ✓ ታሪካዊ አጀማመሩ ምን ይመስላል?
- ✓ መቼ እንዴት ያከብሩታል? በምን አውድ?
- ✓ የከበራው አጠቃላይ መዋቅር ምን ይመስላል?
- ✓ በክብረ በዓሉ ላይ የሚስተዋል የተለየ ልብስ፣ ቁሳቁስ፣ ምግብ… አለ? ለምን?
- ✓ የመከበሩ አጠቃላይ ማህበራዊ ፋይዳውስ ምንድን ነው?
- ✓ በከበራው ላይ የሚከሰቱት ዋና ዋና ሁነቶች ምን ምን ናቸው?

የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ በዳንግላ ከተማና አካባቢው የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የተከበረውን የሼህ ሁሴን ዓለሙ የመውሊድ በዓልን አጥንቻለሁ፡፡ በዚህም በዳንግላ የሼህ ሁሴን ዓለሙ መስጊድ የነበረው ገጽታ እና አጠቃላይ ሁነቶች ከላይ የተጠቀሱትን የትኩረት አቅጣጫዎች (መሪ ጥያቄዎች) መሰረት በማድረግ ተዳሶ ቀርቧል፡፡

### 1.6.2 የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ የቀረበው በገላጫዊ (descriptive) ስልት ሲሆን ክዋኔ ተኮር አቀራረብን ተከትሎ የመውሊድ በዓሉን መቼት፣ አከዋወን፣ አውድ፣ በክዋኔው ላይ የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ክስተቶች (events) እና ተሳታፊዎች ያላቸውን ቦታ ተንትኗል። ይህን በማደርግበት ወቅት የመስክ ሥራ በስፋት ስለሚጠይቅ ለአንድ መስከኛ የሚያስፈልጉ ትጥቆችን በማሟላት ጥናቱ ተካሒዷል። በዚህም መሠረት ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚከተሉትን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተግባራዊ በማድረግ ጥናቴን አካሒጃለሁ።

ጥናቱ ቀዳማይ እና ካልአይ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም የተካሔደ ሲሆን በተለይም ከመስክ በተገኙ መረጃዎች የተዋቀረ ነው። በመሆኑም መረጃዎቹን ለማግኘት እንዲሁም የተገኙትን መረጃዎች ለመተንተን የተከተልኳቸው ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው።

የቃል ግጥም ጥናት፥ በአጠቃላይም የፎክሎር ጥናት የመስክ ምርምር የሚጠይቅ እንደመሆኑ ይህ ጥናትም በቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ማለትም በቃለ መጠይቅ፥ በምልከታ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መስክ ላይ በተገኙ መረጃዎች በመታገዝ የተካሔደ ነው።

#### ሀ. ምልከታ

ምልከታ አንድ መስከኛ ከውጭ ሆኖ ሌሎች ሰዎች የሚያከናውኑትን ድርጊት ቀጥታ በመመልከት ድርጊቱንም በተመለከተበት ሁኔታ የሚገልጽበት ሲሆን፤ ምልከታው ከእይታው ገጽታ አንጻር ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ የስሜት ህዋሳቱን በመጠቀም መረጃ የሚያገኝበት ዘዴ መሆኑን Jackson (1987) እና Goldstein (1974) ገልጸዋል።

እኔም ይህንን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመጠቀም በዳንግላ ከተማ በመገኘት የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓል ስርዓተ ክንዋኔና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ የሚያልፉባቸውን ሂደቶች በአንክሮ ተከታትያለሁ። በተጨማሪም የመውሊዱ በዓል ክዋኔ የሚያስገኘውን ማህበራዊ እና ባህላዊ ጠቀሜታ ከምልከታየ ለመገንዘብ ሞክሪያለሁ። ይህን ሳደርግ የመውሊዱን ክዋኔ እንቅስቃሴ በፎቶግራፍ ፥ ቪዲዮ እንዲሁም በግል ማስታዎሻዎች በማገዝ መረጃውን ሰብስቤለሁ።

#### ለ. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ፥ አንድ መስከኛ በጥናቱ ውስጥ ለሚያነሳቸው ሀሳቦችና ሁኔታዎች መረጃ ያስገኙልኛል ያላቸውን ጥያቄዎች በማዘጋጀት ስለጉዳዩ መረጃ ይኖራቸዋል ተብለው

የሚታመኑ ሰዎችን በመጠየቅ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ መሆኑን Goldstein (1974፥77-78) ጠቁሟል፡፡ በዚህ መሰረት እኔም መስክ ላይ በመገኘት ላጠናሁት ጥናት ተገቢውን መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ መረጃ አቀባዮችን በአላማ ተኮር ዘዴ በመታገዝ መርጬ ጥናቱን አካሒጃለሁ፡፡ ይህንንም ያደረኩት በአውዱ በመገኘት የመውሊድ በዓሉን ክዋኔ ስመለከት ግልጽ ያልሆኑ ነገሮችን በቀጥታ ነገሩ ይመለከታቸዋል ከምላቸው የሐይማኖቱ አዋቂዎች (ኡለማዎች) ለመጠየቅ በማሰቤ ነው፡፡

ይህን በማካሔድበት ወቅት የተጠቀምኩባቸው ስልቶች፤ ቀድመው በተዘጋጁ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች /structured interview/ እና ቀድመው ባልተዘጋጁ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች (unstructured interview) ሲሆን እነዚህም ሲከናወኑ መቅረጸ ድምጽ (ቴፕ) ተጠቅሜያለሁ፡፡ ምክንያቱም ከመስክ በኋላ ደጋግሜ በማዳመጥ ወደ ትርጓሜ እንዲያደርሱኝ በማሰብ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከ31 ሰዎች ጋር ቃለ መጠይቅ አድርጌለሁ፡፡ ከነዚህ መካከል 8ቱ ቁልፍ መረጃ አቃባዮቸ ናቸው፡፡

### ሐ. ተተኳሪ ቡድን ውይይት

ይህ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ከአንድ በላይ የሆኑ መረጃ አቀባዮች የሚሳተፉበት ሲሆን በተለይ በቃለ መጠይቅ የተገኙ የግል አስተሳሰቦችና አመለካከቶች በቡድን ስለመደገፋቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል አይነተኛ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ በመገልገልም በግል ያገኘኋቸው አስተሳሰቦችና አመለካከቶችን፣ መረጃ ሰጭዎችን ማለትም የበዓሉ ታዳሚዎች (ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ)፥ በማህበረሰቡ ለብዙ ጊዜ የቆዩ፥ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑ እንዲሁም የአካባቢውን ታሪክ ያውቃሉ ተብሎ የተመሰከረላቸው ሽማግሌዎችን 4ጊዜ በማወያየት፤ በቃለ መጠይቅ የተገኙ የግል አስተሳሰቦችና አመለካከቶች በቡድን ስለመደገፋቸው አረጋግጫለሁ፡፡

ሌላው ለዚህ ጥናት የተጠቀምኩት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ካልኣይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም አንድ መስከኛ ወደ መስክ ምርምር ከመውጣቱ በፊት በሚያጠናው ጉዳይ ላይ ቅድመ መስክ ዝግጅት ሊያከናውን ይገባል፡፡ ይህንኑ ጉዳይ MacDonald (1972፥407) “እንደሚታወቀው ማንም ሰው በባህል ወደ ዳበረ አካባቢ በመሄድ ጠቃሚ ነገር ማግኘት ይችላል፤ ነገር ግን በአብዛኛው ስርአት ያለው የመስክ ምርምር የሚጀመረው በቤተመጻህፍትና በቤተ መዛግብት ባለ ጠረጴዛ ላይ ነው”፡፡ በማለት ይገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት ከርእሰ ጉዳዬ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ቀደምት ተዛማጅ ስራዎችን፥ መጻህፍትን፥ መጽሄቶችን፥ ጋዜጦችን እንዲሁም የኢንተርኔት ምንጮችን በመመልከት ጠቃሚ ሀሳቦችን በማስታወሻዬ በመያዝ ጥናቴን ጀምሬለሁ። በጥናቱ ሒደትም በአማካሪና በጓደኞቸ ጥቆማ የቀደሙ ተዛማጅ ጽሑፎች ዳሰሳ አካሒጃለሁ።

### 1.6.3 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

በቀዳማይ እና በካልአይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ጥናቱን ከግብ በሚያደርስ መልኩ በማደራጀት ተንትኜ አቅርቤያለሁ። ይህን ሳደርግ ገለጻን (description) ተጠቅሜያለሁ። ይህም ማለት በዋናነት የመውሊድ በዓሉን ክዋኔ በሁነት ላይ በመመስረት እየገለጽኩ ወደ ትርጓሜ አምርቻለሁ። በዚህም ዘዴ በመገልገል የክዋኔው ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳ እና የሚፈጸሙ ድርጊቶችን (ዝየራ፣ ዱኣ (ምርቃት) እና መንዙማ) ከአውዱ በመነሳት አጥንቻለሁ።

## 1.7 የመስክ ጥናት ተሞክሮ እና ገጠመኝ

### 1.7.1 የመስክ ተሞክሮ

ለዚህ ጥናት መረጃ ለማግኘት ለጥናት ወደተመረጡት ቦታዎች የተደረጉት ጉዞዎች ሁለት ጊዜ የተከናወኑ ሲሆን ሒደታቸውም የሚከተለውን ይመስላል። የመጀመሪያው ጉዞየ የተከናወነው ቅዳሜ የካቲት 2 ቀን 2005 ዓ.ም ነው። በዚህ እለት ማለዳ 12 ሰአት አዲስ አበባ ክፍለ ሀገር አውቶቡስ ተራ ደርሻለሁ። ከአዲስ አበባ - ባህር ዳር በሚለው የህዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ተሳፍሬ የአዲስ አበባን ምድር ስለቅ ከጥዋቱ አንድ ሰአት ሆኗል። በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስር ካሉት አስር ዞኖች አንዱ ወደ ሆነው አዊ ዞን ለመድረስ ቢያንስ አስር ሰዓታት መጓዝ ይጠበቅብኛል።

ይዞን የሚሄደው አውቶቡስ በእንጦጦ በኩል ይዞን ከተነሳንበት አዲስ አበባ በሱሉልታ አቋርጠን ከረፋዱ አራት አዓት ላይ ገርበ ጉራቻ ላይ ስንደርስ ለምሳ እና ለሻይ እረፍት ጥቂት አረፍ አልን። ገርበ ጉራቻ ላይ ትንሽ ካረፍን በኋላ ቀጣዩን ጉዟችንን ጀመርን። ከገርበ ጉራቻ ከተማ ጥቂት ኪሎ ሜትር እንደተጓዝን የተሳፈርንበት አውቶቡስ ቁልቁል እያንደረደረን አባይ በረሀን አሳልፎ ከቀኑ ስምንት ሰአት ገደማ ደጀን፣ ቀጥሎም ማርቆስ፣ ፍኖተ ሰላም እና ሌሎች ከተሞችን እያለፈ 11:05 ላይ ዳንግላ ሲደርስ 70 ኪሎ ሜትር የሚቀራቸውን አብረውኝ የተቀመጡትን የባህር ዳር ተጓዦች ተሰናብቸ ወረድኩ።

በዚህ ጉዞ ካስተዋልኳቸው ነጥቦች መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው በጉዞ ላይ አብራውኝ ተቀምጠው የነበሩት የባህርዳር ከተማ ነዋሪ የሆኑት የ65 አመቱ አዛውንት አቶ ቢራራ ሞገስ ያጫወቱኝ ጉዳይ ነው፡፡ አቶ ቢራራ የጉዞየን አላማ ስነግራቸው፤ ስለ ሐጅ ሁሴን (ሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓል ስርዓተ ክንዋኔ፣ ስለ አገው ማህበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ (የሚነገሩ አፈታሪኮችን) ፤ እንዲሁም ስለክርስቲያንና ሙስሊሙ ተቻችሎና ተከባብሮ አብሮ በመብላትና በመጠጣት የሚኖር ህዝብ መሆኑን የነገሩኝን በማስታወሻ መዝገቤ ይዣለሁ፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ በመውሊድ በዓሉ ክዋኔ ላይ ባደረኩት ቃለ መጠይቅ ትክክል መሆኑን በማረጋገጤ አቶ ቢራራ ያላቸውን አካባቢያዊ እውቀት መለስ ብየ ለማድነቅ ተገድጃለሁ፡፡

በሚቀጥለው እሁድ በመሆኑ ይህን ቀን በዕረፍት ለማሳለፍ በመወሰን ወደ አልጋየ አመራሁ፡፡ በማግስቱ የጥናቴን እቅድ በማጤን አርብ (08/06/2005 ዓ.ም) ለሚጀመረው ክብረ በዓል ከሰኞ ጀምሬ ማን ማንን ማናገር እንዳለብኝ፣ ምን አይነት መረጃዎች በምን መልኩ እንደምሰበስብ እሁድ በ 03/06/2005 ዓ.ም እቅድ ሳዘጋጅ ዋልኩ፡፡

የካቲት 04 ሰኞ ቀን ዳንግላ ከተማ ውስጥ ሊረዱኝ የሚችሉ በዞን እና በወረዳ አመራር ላይ ያሉ የከተማው ተወላጆችን አነጋገርኩ፡፡ በዚህም የተነሳሁበትን ዓላማ በማበረታታት አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ እንደሚያደርጉልኝ ነገሩኝ፡፡ ለጥናቴ ጅማሬ እንዲያግዘኝ በማለት በዞኑ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ስለ ዳንግላ አጠቃላይ መረጃ ወሰድኩ፡፡ በዚህም የህዝቧን ቁጥርና መልካምድራዊ ገጽታዋን ለመረዳት ቻልኩ፡፡ በዚሁ ቀን ወደ ማታ አካባቢ የሐጅ ሁሴን ዓለሙ (የሼህ ዳንግላ) መውሊዱን አስተባባሪ አቶ ኡስማን ሰይዱ በጀማል ፈንታው አማካኝነት አግኝቼ ተዋወኩ፡፡ በሚቀጥለውም ቀን ላናግረው እንደምፈልግ ገልጬለት ቀጠሮ ይዘን ተለያየን፡፡

የካቲት 05 እለተ ማክሰኞ ከሰአት በኋላ ከመውሊዱ የአስተባባሪ (አቶ ኡስማን ሰይዱ) ጀማል እና እኔ በመገናኘት ሻይ ቡና እያልን ስለ መውሊዱ አጀማመር፣ አከባበር፣ በበዓሉ ላይ ስለሚገኙ ተሳታፊዎችና እነማንን ባናግር ዓላማየ ከግብ ሊደርስ እንደሚችል ተጨዋወትን፡፡ በጨዋታችን ማብቂያም በሚቀጥለው ቀን ማለትም ረቡዕ 06/06/2005 ዓ.ም መውሊዱ የሚከበርበትን ስፍራ እንደሚያስጎበኙኝ እና ይመለከታቸዋል ያልኳቸውን ሰዎች ሊያስተዋውቀኝ ቃል ገብቶልኝ ተለያየን፡፡ በቀጠሮአችንም መሰረት ረቡዕ ከጀማል ጋር በመሆን ከአቶ ኡስማን ሰይዱ ተገናኝተን ወደ መውሊዱ መከበሪያ ስፍራ አመራን፡፡ በቦታውም ስንደርስ ዳስ ለመዘርጋት ህብረተሰቡ በከፍተኛ ስራ ተወጥሮ አገኘን፡፡ የሚያስገርመው ነገር ግን ዳሱን

ለመዘርጋት የሚጣደፉት ሙስሊሞች ብቻ አልነበረም፡፡ በርካታ በአካባቢው የሚኖሩ ክርስቲያኖች በከፍተኛ ጥድፊያ በማገዝ ላይ ነበሩ፡፡ እኔም ጎን ለጎን የሚመለከታቸውን አካላት በመተዋወቅ እንዲሁም በዳሱ ዝርጋታ ላይ ለማገዝ እየሞከርኩ በስራው ላይ ተሳታፊ የነበሩ አንዳንድ ግለሰቦችን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መልካም ግንኙነት መፍጠር ቻልኩ፡፡

ሐሙስ 07/06/2005 ዓ.ም ጠዋት እኔ፣ ጀማል፣ ሙሐመድና አንዋር (መውሊዱን ለማክበር ከወረታ የመጡ ወንድሞቼ ናቸው) በመሆን መውሊዱ ወደሚከበርበት ስፍራ አመራን፡፡ በዚህም የእንጀራ ጋገራ፣ የሽንኩርት ከተፋ፣ የዕርድ ስርዓት ሲካሔድ በማግኘቴ የተለያዩ የበዓሉ ተሳታፊዎችን ቃለ መጠይቅ አደረኩ፡፡ ከሰዓት በኋላ ደግሞ ከተለያዩ አካባቢዎች ክብረ በዓሉን ለመሳተፍ የመጡትን እንግዶች ቃለ መጠይቅ አደረኩ፡፡

አርብ 08/06/2005 ዓ.ም ምሽት ዋናው የመውሊድ ክብረ በዓል የሚጀመርበት ቀን በመሆኑ እለቱ ከፍተኛ የስራ ጫና የሚበዛበት ነበር፡፡ በዚህም ቀን ቪዲዩ ካሜራየንና መቅረጸ ድምጼን አስተካክየ ከተለያዩ ቦታ የመጡት የበዓሉ ታዳሚዎች “ዚያራ” ሲያካሒዱ ምልከታየን አካሒጃለሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከላይ ስማቸው የተዘረዘሩት ሰዎች የጥናቴን አላማ ከጉዞዬ አስቀድሜ በዝርዝር ነግሬአቸው ስለነበር እኔ ዚያራውን ስከታተል፤ እነሱ ከመውሊዱ አስተባባሪ ጋር በመሆን ወደ ዳሱ በመሄድ ለቃለ መጠይቅ እና ለቡድን ውይይት የሚመጥኑ ሰዎችን አዘጋጅተውልኝ ስለነበር በቀላሉ መረጃ ማግኘት ችያለሁ፡፡ በመሆኑም በዚህ ቀን ከፊል ምልከታና ከፊል ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በሁለት ጉዳዮች ላይ የቡድን ውይይት በማካሔድ መረጃየን ሰብስቤያለሁ፡፡

በዚሁ ቀን ከምሽቱ 3:30 ጀምሮ እስከ 10:30 ድረስም በዱኣ፣ በመንዙማና በሐድራ ሌሊቱን ሙሉ ስርዓቱ የተከናወነ ሲሆን በቪዲዩ ካሜራና መቅረጸ ድምጽ በመጠቀም ምልከታዬን ሙሉ ለማድረግ ሞክሬያለሁ፡፡ በሁለተኛውም ቀን ማለትም ቅዳሜ በ09/06/2005 ዓ.ም በተመሳሳይ መልኩ እንግዶችን በማስተናገድና ከላይ የተጠቀሱት ስርዓቶች በመፈጸም ስርዓቱ ሲከናወን ውሎ አድሯል፡፡ በዚህም ቀን ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ከረዳቶቸ ጋር በመሆን መረጃየን ስሰበስብ ውያለሁ፡፡ በመጨረሻም እሁድ በ10/06/2005 ዓ.ም የስርዓቱ የመጨረሻ ቀን በመሆኑ በዕቅዴ መሰረት ያላሟላሁዋቸውን መረጃዎች በማረጋገጥ ቃለ መጠይቅ ሳካሒድ ውያለሁ፡፡ ነገር ግን በክብረ በዓሉ ወቅት ከፍተኛ ሚና የነበረውን የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) ታላቅ ልጅ ሐጅ ሲራጁዲን ሁሴን ለማነጋገር ብሞክርም በወቅቱ ይካሔድ የነበረውን የዚያራ ስነ ስርአት ይመራ ስለነበር አዲስ አበባ ቃለመጠይቅ ለማድረግ ቀጠሮ ይዤ ተመልሻለሁ፡፡

ሁለተኛው ጉዞዬ የተካሄደው ሚያዚያ 11 ቀን 2005 ዓ.ም ሲሆን በዚህ ጉዞዬ በመጀመሪያ ያላገኘኋቸውን መረጃዎች እና አዲስ አበባ ከመጣሁ በኋላ መረጃውን ስተነትን ክፍተት የፈጠሩብኝን ነጥቦች ማካተት እና መሙላት ችያለሁ፡፡

### 1.7.2 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በዚህ ንኡስ ርእስ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና ችግሮቹን ለመቅረፍ የተወሰዱ መፍትሄዎች ቀርበዋል፡፡

ጥናቱ የመስክ ስራን የሚጠይቅ በመሆኑ የተለያዩ ችግሮች ማጋጠማቸው አይቀርም፡፡ መስክ ላይ ካጋጠሙ ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ችግር፥ ለጥናቱ በመረጃ አቀባይነት ከተመረጡት መረጃ አቀባዮች ውስጥ አስራ ሁለቱ ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ የበአሉ ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ እነዚህን እንግዳ ሰዎች ለማነጋገር ደግሞ የጥናቱን ዓላማ በስርአት ማስረዳት ግድ ይላል፡፡ ነገር ግን አብዛኞቹ የከበራ ስርዓቱን ለመሳተፍ ካላቸው ጉጉት አንጻር የመቸኮልና ለማናገር ፈቃደኛ ያለመሆን ነገር ነበር፡፡ ስለዚህ እነዚህን እንግዶች ለማነጋገር ሶስቱንም ቀን የዝሁር ሰዓትን መጠበቅ ነበረብኝ፡፡ በዚህም ጥናቱን ባሰብኩት ሰአት ለማካሄድ ባለመቻሌ የመሰላቸትና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት እንዲያድርብኝ ሆኖ ነበር፡፡

ሁለተኛው ችግር የጥናቴን አላማ ከግብ ለማድረስ ለታዳሚዎቹ ካቀረብኳቸው ጥያቄዎች ውስጥ የተወሰኑትን በጥርጣሬ አይን መመልከታቸው ያስከተለው ችግር ነው፡፡ ይኸውም የመስክ ስራውን በሚገባ እያከናወንኩ እያለ አንዳንድ ጥያቄዎቼን በጥርጣሬ የማየትና ለመመለስ ፈቃደኛ ያለመሆን ችግር ገጥሞኝ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የችግሩን መንስኤ ለማጣራት ሞከርኩ፡፡ አንዳንድ መረጃ አቀባዮቼ ጥቂት ፍንጭ ሰጡኝ፡፡ ለካስ መረጃ አቃባዮቼ "በወቅቱ ካለው እስላማዊ እንቅስቃሴ" በማያያዝ ነበር ጥያቄዎቼን ከመመለስ ወደኋላ ያሉት፡፡ ስለዚህ የቡድን ውይይት በማካሒድበት ወቅት ጥያቄዎቸን ላለመመለስ እርስ በራሳቸው ተነጋግረዋል፡፡ ይህም ጥናቴ ላይ እንቅፋት ሆኖብኝ ነበር፡፡

በጥናቱ ያጋጠመኝ ሶስተኛው ችግር አንዳንድ መረጃ አቀባዮቼ መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆኑ በኋላ ድምጻቸው በቴፐም ሆነ በቪዲዮ ካሜራ እንዳይቀረጽ መከልከላቸውና ፎቶ ግራፍ አንነሳም ማለታቸው ነው፡፡

አራተኛው ችግር ወንዶች ወደ ሴቶች ዳስ (ክልል) መሄድ የተከለከለ በመሆኑ በምልከታ ወቅት የሴቶችን ስረዓተ ክዋኔ በቀላሉ ለማየት እንዳልችል እንቅፋት ሆኖብኝ ነበር፡

መስክ ላይ ያጋጠሙኝን ችግሮች የፈታሁት በሚከተለው መልኩ ነው፡፡ አንደኛ፥ እንግዳ መረጃ አቀባዮቼን ለማነጋገር ሶስቱንም ቀን የዝሁር ሰዓትን መጠበቅ ብቸኛው አማራጭ መሆኑን ሳውቅና ጥናቴን ባሰብኩበት መንገድ እንደማያስኬደው ስገነዘብ ሌላ ዘዴ ዘየድኩ፡፡ ይኸውም ክብረበዓሉ በሚከበርበት ቦታ መድረኩን ይመራ ለነበረው ሰው በማስረዳትና እንዲተባበረኝ በመጠየቅ "ለጥናት የመጡ ሰዎች ስላሉ አስፈላጊውን መረጃ እንድትተባበሯቸው" የሚል መልእክት በማይክራፎን አስነገርኩ፡፡ በተለይ ላለፉት ስምንት ዓመታት መድረኩን የመራውና የዚህንም ዓመት መድረክ እየመራ የነበረው መምህር ሙሀመድ ጠሐ በጣም ስለተባበረኝ ከሌላ ቦታ የመጡ የክብረ በአሉ ተሳታፊዎችን በቀላሉ ለማነጋገር ችያለሁ፡፡

ሁለተኛው ችግር የተቃለለው እንደላይኛው ሃሳብ ሁሉ የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓል ስርዓተ ክንዋኔ በሚካሔድበት ቦታ በተገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ የጥናቴን አላማ ለአስተባባሪዎቹና እና ለእንግዶቹ በሚገባ ለማስረዳት መሞከሬ ነው፡፡ በተለይ አቶ ኡስማን ሰይዱ (የመውሊዱ ዋና አስተባባሪ) በጥናቴ ወቅት የተፈጠሩትን ችግሮች በማቃለል በኩል ከፍተኛ እገዛ አድርጎልኛል፡፡

ሶስተኛውን ችግር ያቃለልኩት ደግሞ ድምጻቸውን በቴፕ እና በቪዲዮ ካሜራ ለማስቀረጽ ያልፈለጉትን እንዲሁም ምስላቸውን በፎቶ ግራፍ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑትን መረጃ አቀባዮች፤ መረጃው ጠቃሚ እስከሆነ ድረስ በጽሁፍ በማስታወሻዬ ለማስፈር በመሞከር ነው፡፡

አራተኛውን ችግር ያቃለልኩት የበዓሉ ተካፋይ ለሆነች ሴት ቴፕና የቪዲዮ ካሜራ በመስጠት የዕለቱን ስርዓተ ክዋኔ በምስል እና በድምጽ በማስቀረጽ ነው፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ ሁለት መሰረታዊ ነጥቦች ተዳሰው ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል የእምነት ከበራ፣ ክዋኔ እና አውድ በሚሉ ጽንሰ ሐሳቦች ላይ ንድፈ ሐሳባዊ ማብራሪያ ቀርቧል፡፡ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከእኔ የጥናት ርእሰ ጉዳይ ጋር ቅርበት ያላቸው በትምህርት ክፍሉ እና ከትምህርት ክፍሉ ውጭ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶች ተከልሰዋል፡፡

### 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

በዚህ ክፍል በጥናቱ ይገኘው ለተነሳሁት ርዕሰ ጉዳይ ንድፈ ሐሳባዊ ማዕቀፍ በመሆን የሚያገለግሉትን ክብረ በአልን፣ ክዋኔን እና አውድን በማስመልከት በተለያዩ ምሁራን የቀረቡ ንድፈ ሐሳባዊ ትወራዎች ላይ ቅኝት ያደረኩበት ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል ንድፈ ሐሳቦቹን የተመለከቱና በመስኩ ምሁራን የተጻፉ መጽሐፎችና ልዩ ልዩ የአርቲክል ጽሑፎች በማቀናጀት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### *2.1.1 ክብረ በአል*

ስለ ክብረ በዓል ምንነት የተለያዩ ምሁራን ተመሳሳይ አንድምታ ያለው የተለያዩ ምላሾች ሰጥተዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡ Sims እና Stephens (2005፣95) ሲገልጹ፡ “በማህበረሰቡ ዘንድ ተደጋጋሚ (repeated) ሆኖ የሚከበር፣ የተለመደ ድርጊት የሚስተዋልበትና ዘወትር ከምንከውናቸው ልማዶች የተለየ ዓላማ ያለው ነው፡፡” በማለት ይገልጹና፤ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ያለውን ቦታ ሲያስረዱን፤ “ክብረ በዓል አንድ ነጠላ የትራዲሽን አይነት ሆኖ ፎክለረኞች ሲያጠኑት ግን የተለያየ ምድብ ውስጥ ያስገቡታል፡፡” ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እንደ Rappaport (1992) አገላለጽ ክብረ በዓል ከአብዛኞቹ የመግባቢያ አይነቶች አንዱ ሳይሆን ለሌሎች (በቋንቋ ጭምር ለማይገለጹት) ተግባቦቶች መነሻ የሆነ፤ ግልጽ የሆነ ቅርጽ ያለው፤ የተለያዩ ገጽታዎችና ባህሪያት ያሉት ከመሆኑም በላይ እነዚህ ባህሪያቶቹ አነሰም በዛም እርስ በእርስ የተያያዙ መሆናቸውን ይገልጻል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እያንዳንዱ ማህበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ በዝግጅትና በጉጉት የሚጠብቃቸው ክብረ በዓላት አሉት፡፡ እነዚህ ክብረ በዓላት ደግሞ ወቅታዊ፣ ማህበራዊ እና ሀይማኖታዊ በሚል የሚታወቁ ናቸው፡፡ Sims እና Stephens (2005፣102-105) እንደሚያስረዱት ክብረ በዓላት ሀይማኖታዊ ይዘት ያላቸውና እና ከሀይማኖታዊ ይዘት ውጭ

መሆናቸውን ይገልጹና አንዳንዶቹ ክብረ በዓላት ደግሞ ሁለቱንም የሚይዙ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

የነዚህ ክብረ በዓላት የአከባበር ስርዓት በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ ፌሽታና ጭፈራ ያለበት ነው። ከበዓላቱም ጋር ልብሱ፣ ድግሱ፣ ዘፈኑ፣ ጭፈራው… አብሮ ይመጣል። ለምሳሌ፡- ወቅታዊ ከሆኑቱ የመኸር ወቅት፣ እሼት ሲደርስ፣ የሚከናወን ስርዓት አለ። ምርት የሚሰበስበው ማህበረሰብ ስራው የሚሰራበትን አጋጣሚ እንደ በዓል ያከብሩታል (በዘፈን፣ በእንጉርጉሮ፣ በጭፈራ…በተለያዩ ስርዓቶች)፤ ምርት በመገኘቱና ምርት በመግባቱ ደስተኛ በመሆን ማህበረሰቡ ፌሽታ ያደርጋል።

ማህበራዊውንም የወሰድን እንደሆነ ልደት፣ ክርስትና ሰርጉን እንመለከታለን። እነዚህ የህይወት ምዕራፍ መክፈቻዎች ሁለቱንም (sacred እና secular) የሚይዙ ክብረ በዓላት መሆናቸው ደግሞ ግልጽ ነው።

ሐይማኖታዊው በዓሉም እንደየሰው እምነት በተለያየ መንገድ ይከበራል፤ እያንዳንዱ ሰው እንደየእምነቱ ለሚያመልከው ለአምላኩ ምስጋና የሚያደርስበት ክብረ በዓላዊ ስርዓት የሚመለከት ነው። እነዚህ ክብረ በዓላት በሚከበሩበት ወቅት የቡድኑ አባላት በስርዓት የተደራጁና በክብረ በዓሉ ስርዐተ ማዕቀፍ ውስጥ የገቡ ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ አብዛኞቹ ክብረ በዓላት ሲከበሩ በተመሳሳይ ጊዜ በርካታ ፎክሎራዊ ጉዳዮን በአንድ አጠቃለው ይዘው ይመጣሉ። ለምሳሌ፡- የዚህ ጥናት ትኩረት አቅጣጫ የሆነውን የመውሊድ ክብረ በዓል ስንመለከት ክብረ በዓሉን ራሱን ችሎ ለማጥናት ተያይዘው የሚመጡትን፡ ቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ፣ ልዩ ልዩ ቁሳዊ ባህሎችና ከመንዙማው ክዋኔ ጋር ተያይዞ የሚመጡ እንቅስቃሴዎችን ማጥናት (መዳሰስ) ያስፈልጋል ማለት ነው።

ይህንንም በተመለከተ Sims እና Stephens (2005፣95) እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> …Rituals are frequently highly organized and controlled, often meant to indicate or announce membership in a group. Most rituals bring together many types of folklore: verbal, such as chants, recitations, poems or songs; customary, such as gestures, dance or movements; and material, such as food, books, awards, clothing and costumes…

በአጠቃላይ ክብረ በዓላት ሲባሉ ወቅታዊ፣ ማህበራዊም ሆነ ሀይማኖታዊ በዓላት ሆነው፡ የባህሉ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ በጉጉት፣ በዝግጅት የሚጠብቋቸውና በጊዜው

የሚያከብሯቸው ናቸው፡፡ በነዚህ ጉዳዮች ላይ ጥናት ለማድረግ የሚሞክር ፎክሎሪኛ  የክብረ በአሉን አጠቃላይ ይዘት መግለጽ ላይ ብቻ መወሰን የለበትም፡፡ ነገር ግን አንድ ፎክሎሪኛ አውዱን መነሻ በማድረግ ክብረ በአላትን በሚያጠናበት ወቅት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለበት Finnegan (1992፣86) ትመክራለች፡፡ "አጥኚው በዙሪያው ያሉ ቁሳቁሶች፣ ጌጣጌጦች፣ ስዕሎች፣ ምልክቶች እርስ በራስ ምን ግንኙነት አላቸው? በትርጉሙስ ላይ የሚያመጡት ነገር አለ?" በሚሉት መሰረታዊ ጥቄዎች ላይ መመስረት እንዳለበት ገልጻለች፡፡

የክብረ በዓላትን አይነት በተመለከተ በርካታ ምሁራን በተለያዩ ጽሑፎቻቸው በሶስት፣ በአምስት፣ በስድስትና በስምንት እየከፈሉ አይነታቸውን ለማስረዳት ይሞክራሉ፡፡ ለዚህ ጥናት ዝግጅት በማደርግበት ወቅት የክብረ በአል አይነቶችን በስፋትና በጥልቀት ከብዙ ምሳሌዎች ጋር በማዋዛት ያቀረበችው Bell (1997: 93-94) ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ክብረ በአላት በስድስት ተከፍለው ቀርበዋል፡፡ ከስድስቱ የክብረ በአላት አይነት ደግሞ የኔ ጥናት የሚያተኩረው "አመታዊ እና የመታሰቢያ ከበራ" በሚለው ነው፡፡

አመታዊ እና የመታሰቢያ ክብረ በዓላት ወቅትን መሰረት አድርገው የሚከበሩ ናቸው፡፡ በዚህ ውስጥ ከሚካተቱት መካከል፡ የዘመን መለወጫ፣ አመታዊ በዓላት፣ የአየር ንብረት ለውጥን መሰረት አድርገው በዓመት የሚከበሩ ናቸው፡፡

Bell (1997: 239). ይህንን ከበራ በተመለከተ "Calenderical rites give socially meaning full definition to the passage of time, creating an ever-renewing cycle of days, months and years. …," በማለት ትገልጻለች፡፡ እነዚህ ከበራዎች ጊዚያቸውን ጠብቀው የሚከበሩ ስለሆኑ ከተቆረጠላቸው ቀን ወይም ወር ላይ የማያልፉ ናቸው፡፡ ጊዜያቸውን የሚወስኑትም በዓሉን የሚያምኑትና የሚያከብሩት የማህበረሰቡ አባላት ናቸው፡፡ በየአመቱ ከመጋቢት 8 እስከ 10 የሚፈጸመው የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓል ስርዓትም ከዚሁ የክብረ በዓል አይነት ጋር የሚገናኝ ነው፡፡

### *2.1.2 ክዋኔ*

ክዋኔ ንድፈ ሀሳብን በተመለከተ Green (1997፣630) Folklore an Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art; በሚለው መዝገበ ቃላት የክዋኔ ንድፈ ሀሳብን በተመለከተ የሚከተለውን ሀሳብ አስፍሮ እናገኘዋለን፡-

ክዋኔ በፎክሎር ውስጥ ማንኛውም ከዋኝ በታዳሚው ፊት ሲቀርብ ጥበባዊነቱንና ኪናዊነቱን በጠበቀ መልኩ የሚያቀርበው ድርጊት ነው፡፡ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ስንመለከተው ደግሞ የክዋኔ ጽንሰ ሀሳብ የሚገነባው ነገሮች ላይ ተመስርተን ለነገሮች በምንሰጠው ፍችና ትርጓሜ አንጻር ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው በሚተገበረው ነገርና በተግባሪው ችሎታ ፣ የሚገለጸውን ካለን እውቀት ፣ ከበራን ከእምነት ፣ የሚታዩ ተጨባጭ ባህሪያት ካለው ሁኔታ ጋር መጣጣም እና በተለይ በቃላት፣ በሙዚቃ፣ በዳንስና ድራማ የሚቀርበውን ኪናዊ እይታ ይመለከታል፡፡ በፎክሎር ጥናት ክዋኔ በሚቀርበውና በተሰነደው መካከል ያለውን ክፍተት ይሞላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ከዚህ ገለጻ የምንረዳው ክዋኔ ማህበራዊ መሰረት ያለው ሆኖ ማንኛውም ከዋኝ በታዳሚው ፊት ሲቀርብ ጥበባዊነቱንና ኪናዊነቱን በጠበቀ መልኩ የሚያቀርበው ድርጊት ከመሆኑም በተጨማሪ ፎክሎራዊ ጉዳዩ ጥበባዊ የሚሆነው ሲከወን መሆኑን እንረዳለን፡፡ በዚህም መሰረት ክብረ በዓላት ወቅትና ጊዜ ጠብቀው እንደየማህበረሰቡ ልማድ የአከባበር ስርዓት የሚለያዩ ናቸው፡፡ በዚህም የክዋኔያቸው ስርአት እንደየማህበረሰቡ ልምድ የሚለያይበት አጋጣሚ አለ ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ክብረ በዓላት ለበዓሉ ድምቀት ከሚሰጡት ፌሽታ፣ ጭፈራ፣ ዘፈን እንዲሁም አለባበስ ጨምሮ ወቅትና ጊዜ ጠብቀው የሚከበሩ ከመሆናቸው በተጨማሪ የራሳቸው የሆነ ማህበራዊ ፋይዳ አላቸው፤ አብሮነትን፣ ህብረትን እንዲሁም መደጋገፍን መፍጠሪያና ማጠናከሪያ ናቸው፡፡ ይህን ውጤት የሚያስገኙት ግን የክብረ በዓሉ ክዋኔ የጋራ በመሆኑ ነው፡፡

ይህንኑ ጽንሰ ሐሳብ በተመለከተ (Bauman 1976: 4-5) ክዋኔ ውበታዊ ተግባር ነው፤ የፎክሎር አፈጻጸም ነው፤ በፎክሎር ውስጥ ያለ ውበታዊ ክስተት መገለጫ ነው፡፡ ክዋኔ ከከዋኝ ፣የአከዋወን ስርአትን፣ ታዳሚንና መቼትን በአንድ ላይ የክዋኔ አቀራረብን እድገት ማሳደግ በሚችሉበት ሁኔታ አጣምሮ ይይዛል፡፡" በማለት ይገልጻል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም የክዋኔና የክብረ በዓል ትስስር በተመለከተ Rappaport (1992, 250) ላይ የሚከተለውን ሐሳብ አስፍሮ እናገኛለን፡፡

> …there is no performance, there is no ritual; performance it selaf is an aspect of that which is performed. The medium is apart of the message; more precisely, it is a metamessage about what ever is encoded in the ritual.

ከዚህ ገለጻ የምንረዳው ክብረ በአል ያለክዋኔ ብቻውን መኖር እንደማይችልና በከበራው ወቅት የሚደረገው ማንኛውም ነገር በራሱ ክዋኔ መሆኑን ነው፡፡ ክዋኔና ክብረ በአል የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይም ይህኑ ጉዳይ Sims እና Stephens (2005፣ 94-126) ከምሳሌ ጋር በማዋዛት አቅርበዋል፡፡ ስለዚህ የመውሊድን ክብረ

በአል አጠቃላይ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ምን ምን እንደሚደረግ ይዘቱን ስንገልጽ በሌላ መልኩ ክዋኔውን ተናገርን ማለታችን ነው፡፡

ይህን ንድፈ ሐሳብ ከማጠቃለሌ በፊት ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባውን ጉዳይ ላንሳ፤ ክዋኔ እንደየባህሉ አይነትና ይዘት የተለያየ አቀራረብ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ክዋኔ የሚቀርብበት እና የሚተረጎምበት ሁኔታ የተለያየ ይሁን እንጂ ዋናው ጉዳይ ፎክሎር ያለ ክዋኔ እንደማይገለጽና ህልውና ሊኖረውም እንደማይችል (Finnegan 1977, Rappaport 1999) ያስረዳሉ፡፡ በክዋኔ ተኮር አቀራረብ አንድን ክዋኔ ለማጥናት/ ለመረዳት የተለያዩ ነጥቦችን ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም ነጥቦች ከዋኙ፣ አድማጩ/ተደራሲው፣ ለክዋኔ የሚቀርበው ጉዳይ፣ መቼቱ፣ መልዕክቱ፣ የአቀራረብ ቅደም ተከተሉ፣ ደንቡና የአድማጩ ምላሽ ዋነኞቹ ናቸው፡፡

### *2.1.3. አውድ*

በርካታ ምሁራን ስለ አውድ የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል Dundes (1994፤ 86) ፤ አውድን አንድ ድርጊት የሚከወንበት ጊዜና ቦታ እንደሆነ በአጭሩ ይገልጻል፡፡ የአንድ ፎክሎራዊ ማህበረሰብ በክብረ በዓል ወይም በማንኛውም ክዋኔ የሚግባባበት መንገድ ነው፡፡ አውድ ፎክሎራዊ ይዘትና ጉዳይ ስላለው ውስብስብነት የሚታይበት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Abrahams (1972፡45) "*Context is semm in such phrase as ''cermonial communicative interactionof small groups'' complex communicative event.*") በማለት ይገልጸዋል፡፡ Sims እና Stephens (2005፡37) ደግሞ “Context refers to anything and everthing that surrounds a text and performance” በማለት ይገልጹታል፡፡

አውድን በሚመለከት ለመንደርደሪያ ያህል ይህን ለመግለጽ ሞከርኩ እንጂ በተለያየ ጊዜ በርካታ ምሁራን ከራሳቸው ግንዛቤ በመነሳት ተመሳሳይ አንደምታ ያላቸው ልዩ ልዩ ብያኔዎችን ሰጥተውት እናገኛለን፡፡ ከእነዚህ ብያኔዎቸ አንጻር አውድ ማንኛውም ፎክሎራዊ ክዋኔ የሚከወንበት ጊዜና ቦታ እንዲሁም አጠቃላይ ድባብ ነው ማለት ይቻላል፡፡

አውድን በተመለከተ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን በገለጹበት መንገድ ለመበየን ቢሞክሩም ገዥ ሀሳብ ተደርጎ የሚቆጠረው ግን Bauman፣ 1983፣ (362- 367) ባቀረበው ጽሑፍ ውስጥ የተሰጠው ማብራሪያ ነው፡፡ በዚህ ጽሑፉ ሪቻርድ ቦውማን እንደሚያስረዳው አንድ የፎክሎር

ክዋኔ ቢያንስ ሁለት አውዶች ይኖሩታል ይላል፡፡ እነዚህም ባህላዊና ማህበራዊ አውድ መሆናቸውን ይገልጻል፡፡ በሁለቱም አውዶች ውስጥ ሶስት ሶስት አውዶች እንደሚካተቱ ጨምሮ ይተነትናል፡፡ የኔም ጥናት የትኩረት ነጥብ የሚመሰረተው በዚሁ በቦውማን ባስቀመጣቸው ማህበራዊ አውድ (social context) እና ባህላዊ አውድን (cultural context) በመሆኑ ነጥቦቹን በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.1.3.1 ባህላዊ አውድ

ባህላዊ አውድ ማህበረሰቡ ባለው ባህል መሰረት ለአንድ ቴክስት፣ ድርጊት ወይም ሁኔታ የሚሰጠው አውዳዊ ፍቺ ነው፡፡ ይህም ማለት የአንድ ቡድን ግንኙነት መግባቢያ ደንብ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ አውዱ ለፎክሎሩ ባህሉ የሚሰጠውን ትርጓሜ ይመለከታል፡፡ በዚህም ስር ሶስት ንኡሳን አቅፎ እንደሚይዝ (Bauman 1983:363) ላይ ይገልጻል፡፡ እነዚህንም አውዶች እንደሚከተለው በአጭሩ እንመልከታቸው፡፡

#### ሀ. የትርጉም አውድ

ይህ አውድ የፎክሎሩን ባህላዊ ትርጉም ለመረዳትና ለማወቅ ወሳኝ ነው፡፡ ይህም ማለት ባህሉ ፎክሎራዊ ጉዳዩን የሚተረጉምበትን አንጻር ለማወቅ ያስችላል ማለት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፎክሎራዊ ጉዳዩ በባህሉ ባለቤቶች በምን መልኩ እንደተወከለ፣ እንዴት እንደሚተላለፍና ምን ምን እሴቶች እንደተወከሉበት ይመረምራል፡፡ በፎክሎሩ ውስጥ የሚገኙትን የአከዋወን ስልቶች፣ መንስኤና ውጤት እንዲሁም ትምርታዊና ዘይቤያዊ አገላለጾች እንዴት እንደተገለጹበት ትኩረት ይሰጣል፡፡ ቦውማንም ፎክሎረኞች ባህላዊ ትርጉምን ከባህሉ ባለቤቶች በቀጥታ ቢወስዱ ጥናታቸው የተሻለና ትክክለኛ እንደሚሆን ያስረዳል፡፡

#### ለ. ተቋማዊ አውድ

በዚህ አውድ ፎክሎራዊ ጉዳዩ በተለያዩ ተቋማት ውስጥ ያለውን አውድ ይመለከታል፡፡ ይህን ሲያደርግ ተቋማቱና ፎክሎራዊ ጉዳዩ በምን እንደሚገናኙ መመርመር፣ ተቋማቱ በየትኛው ባህል ውስጥ እንደሚገኙና እንዴት እንደሚያገለግሉም ማተኮር አስፈላጊ እንደሆነ ቦውማን ያስረዳል፡፡

### ሐ. ተግባቦታዊ አውድ

በዚህ አውድ በክዋኔው ውስጥ በፎክሎራዊ ጉዳዮች መካከል ያለውን ዝምድና ይመለከታል። ይህም ማለት በአንድ ክብረ በዓል ወቅት ከበዓሉ ጋር ተያይዞ ልብሱ፣ ድግሱ፣ ዘፈኑ፣ ጭፈራው... አብሮ ይመጣል። ለምሳሌ፦ የዚህ ጥናት ትኩረት አቅጣጫ የሆነውን የመውሊድ ክብረ በዓል ስንመለከት ክብረ በዓሉን ራሱን ችሎ ለማጥናት ተያይዘው የሚመጡትን፡ ቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ፣ ልዩ ልዩ ቁሳዊ ባህሎችና ከመንዙማው ክዋኔ ጋር ተያይዞ የሚመጡ እንቅስቃሴዎችን ማጥናት (መዳሰስ) ያስፈልጋል ማለት ነው።

### 2.1.3.2.ማህበራዊ አውድ

ይህ አውድ ከቤተሰብ አባላት ባልና ሚስት፣ ልጆች፣ እስከ ቡድናዊ፣ ሀይማኖታዊ ቡድኖች፣ አካባቢያዊና የመሳሰሉትን ተግባቦት የሚያጠቃልል ነው። ማህበሩ (Folk group) የሚገናኙበት ነው። በመሆኑም ከዋኝ፣ ተመልካች ወይም ተሳታፊ በጋራ ይገናኙበታል። ማህበራዊ አውድ ማህበራዊ መሰረት፣ ግለሰባዊ አውድ እና ሁኔታዊ አውድ የተሰኙ ሶስት መልኮች አሉት። እነዚህን ቀጥሎ እንመለከታለን።

### ሀ. ማህበራዊ መሰረት

የማህበራዊ ግንኙነት አውድ በክዋኔ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አለው። አንድ ፎክሎራዊ ቴክስት የሚከወነው እንደ ማህበረሰቡ የስልጣን ደረጃ የክብር ተዋረድ ሊወሰን ይችላል። አንድ ቀልድ፣ ታሪክ፣ ሚስጢር ወይም ስነቃል በሚከወንበት ወቅት እንደ ማህበረሰቡ የአመለካከት ሁኔታ ይወሰናል። እያንዳንዱ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ የእድሜና የስልጣን ተዋረድ አለው። ስለዚህ ይህ አውድ ትኩረቱ ከፎክሎሩ ባለቤቶች ማንነት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን አውድ ያጤናል ማለት ነው።

ክዋኔ በጾታ፣ በእድሜ፣ በቡድን ይለያያል። ስለዚህ ክዋኔውን ማህበረሰቡ የሚጋራው ቢሆንም ክዋኔው ሁሉንም ማህበረሰብ አይወስንም ማለት ይቻላል። ስለዚህ የፎክሎሩን አውድ ለመረዳት የፎክሎሩን ባለቤቶች ማንነት (ፎክ ቡድን) ማወቅ ግድ ይላል።

### ለ. ግለሰባዊ አውድ

በዚህ አውድ ግለሰቡ በፎክሎራዊ ጉዳዩ የሚኖረው ሚና፣ ፎክሎሩ ለግለሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ፣ ግለሰቡ ለፎክሎሩ የሚሰጠው ትርጉም እንዲሁም ግለሰቡ ከሌሎች ግለሰቦች ጋር በመዋቀር ቡድን የመሰረተበትን አውድ ያጠናል።

### ሐ. ሁኔታዊ አውድ

አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ የተደራጀ፣ ፍሰታዊና የተለመደ አከዋወን ወይም አውድ ሊኖር ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ድንገተኛ ለውጥ የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች የሚከሰቱትም ከፎክሎራዊ ጉዳዩ፣ ካለው ነባራዊ ሁኔታ፣ ለመከወን ከምንጠቀምበት ስልት እና ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ፎክሎራዊ የቀልድ ቴክስት ለመከወን እንደየ ማህበረሰቡ የአኗር ሁኔታ፣ ባህልና አካባቢ ሁኔታ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ ቴክስቱም ሲከወን በከዋኙና በተሳታፊዎቹ መካከል እንዲሁም በተመልካቹ መካከል ባለው ማህበራዊ አውድ ይወሰናል፡፡

አጥኚው ሁኔታዊ አውድን ለማግኘት ራሱንም ሆነ ቡድኑን መጠየቅ ያለበት እየተከናወነ ያለው የፎክሎር ቅንጣት አሁንባለው ሁኔታ ውስጥ ምን ማለት ነው? ብሎ በመጠየቅ ለቡድኑ ተግባቦት እንዴት እንደሚውል ማጣራት ላይ ነው፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ተዛማጅ ጥናት ቅኝት በማደርግበት ወቅት የተገኙት ቀደምት ጥናቶች በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ የተሰሩ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም እና በኬኔዲ ላይብረሪ 15 ተቀራራቢ ጥናቶች ተገኝተዋል፡፡ ከተገኙትም መካከል 13ቱ በመጀመሪያ ዲግሪ የተጠኑ ሲሆን 2ቱ ደግሞ በሁለተኛ ዲግሪ የተጠኑ ናቸው፡፡ ከነዚህ ጥናቶች መካከል ለተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የተመረጡት 6ቱ ናቸው፡፡ የተመረጡበትም ምክንያት 4ቱ በቀጥታ ከዚህ ጥናት ጋር የመመሳሰል ባህሪይ ስላላቸው ሲሆን 2ቱ ደግሞ በሁለተኛ ዲግሪ የቀረቡ በመሆናቸው በቀጥታ ባይገናኙም የመስኩ ጥናት ደረጃ የነበረበትን ከፍታ ለማሳየት እንዳሉ የተወሰዱ ናቸው፡፡

በኡለማ መውሊድ ላይ ከዚህ ቀደም የተደረጉት ጥናቶች ሁሉም በመጀመሪያ ዲግሪ የቀረቡ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚገናኙት 4 ጥናቶች ናቸው፡፡ በሁለተኛ ዲግሪ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች ደግሞ ትኩረታቸው እስላማዊ ቃል ግጥም ሲሆን የኡለማ መውሊድን እንደ አንድ የግጥሞቹ መከወኛ አጋጣሚ አድርገው ያቀረቡ ናቸው፡፡

የኡለማ መውሊድንም ሆነ ቃላዊ ግጥሞቹን በተመለከተ በሶስተኛ ዲግሪ የቀረበ ጥናት አላገኘሁም፡፡ በተጨማሪም በልዩ ልዩ አርቲክሎችና መጽሐፎች የተገኙ በርካታ እስላማዊ

ጥናቶች ቢኖሩም በዚህ ጥናት የተነሳውን ጉዳይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መልኩ ባለማንሳታቸው በቅኝቴ ውስጥ አላካተትኳቸውም፡፡

### 2.2.1 በማስተርስ ዲግሪ የቀረቡ ተዛማጅ ጥናቶች

ለማስተርስ ደረጃ ከቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች መካከል በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ ከኔ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሁለት ጥናቶች ተገኝተዋል፡፡ እነዚህም የአሰፋ ማሞ (1987) "Some prominent Features of Menzuma in Wollo Region" እና የብርሀኑ ገበየሁ (1990) "Islamic Oral poetry in Wollo a prelimainary Descriptive Analysis" ናቸው፡፡ እነዚህም ጥናቶች በእስላማዊ ቃል ግጥሞች ላይ የቀረቡ ሲሆን የኡለማ መውሊድን እንደ አንድ የግጥሞቹ መከወኛ አጋጣሚ አድርገው ያቀረቡ ናቸው፡፡

የአሰፋ ማሞ ጥናት መንዙማ በቁምና መንዙማ በቁጭታ በማለት አጠቃላይ ሒደቱን በማሳየት ተንትኖ አቅርቧል፡፡ የብርሀኑ ገበየሁ ደግሞ ሰፋ ባለ መልኩ በእስልምና ቃላዊ ግጥሞች ላይ ጠለቅ ያለ ምርምር በማድረግ፤ በእስልምና ውስጥ በባእላት፣ በሐድራ፣ ተወሒድን ለማስተማር የሚቀርቡ ግጥሞች፣ በአረብኛ የተጻፉ የአማርኛ እንጉርጉሮ ግጥሞችን ክዋኔያቸውንና ይዘታቸውን በሰፊው በመተንተን እስላማዊ ግጥሞች ያላቸውን ባህሪያት ጠቅለል ባለ መልኩ በመዳሰስ አቅርቧል፡፡

የአሰፋ ማሞ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው መረጃዎቹን ለማግኘት የተጠቀመው ስነ ዘዴና የመንዙማ ግጥሞቹን ለመተንተን የተጠቀመበት ስልት ሲሆን የሚያለያየው ደግሞ የሱ ጥናት የመንዙማ ቃላዊ ግጥሞቹ ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ፣ አጠቃላይ መንዙማዎች የሚያሳዩትን የተለየ ባህሪይ መተንተን ላይ ብቻ መመስረቱ ሲሆን የኔ ጥናት ደግሞ የመንዙማ ግጥሞችን ባህሪ ምን ይመስላል? ሳይሆን በኡለማ መውሊዱ ላይ የተከወኑት ቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ክዋኔያቸው ምን ይመስላል? በሚል የማጠንጠኛ ነጥብ የተጠና በመሆኑ ይለያያል፡፡

ብርሀኑ ገበየሁ የወሎ ሙስሊሞች ቃል ግጥም በሚል ያቀረበው ጥናት ዋና አላማ የቃል ግጥሞቹን በዋናው አውድ ውስጥ አስገብቶ በሚገባ መተንተን ነው፡፡ የጥናቱ ንዑሳን አላማዎችም የተለያዩ ቃል ግጥም አይነቶች መለየትና ባህላዊውንና ስነጽሁፋዊ ባህርያቶቹን መግለጽ፤ የገጣሚ አይነቶቹ ባለሙያ መሆን ያለመሆናቸውን ማየት፤ የቃል

ግጥሞቹን የድረሳ የክዋኔና የተስተላልፎቱን ሁኔታ ማሳየትና የተለያዩ የቃል ግጥሞችን ይዘት መለየት የሚሉት ናቸው፡፡

የቃል ግጥሞቹ የተሰበሰቡባቸውና ጥናቱ የተካሄደባቸው አካባቢዎች ስድስት ናቸው፡፡ እነሱም አምባሰል፣ ደሴ ዙሪያ፣ የጁ፣ ቃሉ፣ ቦረናና ወረይሉ ናቸው፡፡የዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት በተሳትፏዊ ምልከታ እና በቦታው ተገኝቶ በመዘገብ ነው፡፡ በተጨማሪም ከገጣሚዎችና ከሃይማኖት አባቶች ጋር ቃለምልልስ የተካሄደ ሲሆን አላማውም ተቋማዊ፣ ሃይማኖታዊና አካባቢያዊ ትርጓሜዎችን በባህላዊ አውዱ ውስጥ ማስገኘት ነው፡፡

የብርሃኑ ገበየሁ ጥናት በቀዳሚው ምዕራፍ ወሎ ውስጥ ስለእስልምና አነሳስና እድገት ያብራራል በዚህም ትንታኔው ቃል ግጥሞቻቸው እንደ ታሪካዊ ማጣቀሻ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች እንደሆኑ ያብራራል፡፡ ስለእስልምና አነሳስና እድገት ያወራበትን ምክንያት ሲገልጽ ደግሞ በግጥሞቹ ውስጥ ስህተት ያለበት ድምዳሜ ላይ ላለመድረስ እና አንባቢያኑም ታሪክ ጠቃሽ ግጥሞችን መረዳት እንዲችሉ የሚያደርግ በመሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም በእስላማዊ ቅዱስ ቦታዎችና በቃል ግጥሞቹ ውስጥ ያለውን ትስስርም አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡

በዚህ ጥናት ሌላው የትኩረት ነጥብ የቃላዊ ግጥሞቹ ማህበራዊ አውዶችና የከበራ ሂደት የሚል ነው፡፡ እነዚህም ኢድ-አል- አድሃ፣ ኢድ-አል-ፊጥር፣ ራመዳን፣ መውሊድና ወዳጃ ናቸው፡፡ አጥኝው በነዚህ ሁሉ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ተሳታፊ ምልከታ አካሂዶ በቦታው ያየውን የመቼት ሁኔታ አቅርቧል፡፡ በዚህም መሰረት በሁሉም አጋጣሚዎች ሃድራ የሚባል ዝግጅት እንዳለ ገልጿል፡፡ በዚህ ማጠቃለያም ሃድራ የሚባለው ደስታንና ሀዘንን ለመግለጽ የሚያገለግልና ለህክምናም የሚጠቀሙበት ዝግጅት ነው፡፡ ይህ የተወሰነ መዋቅር ያለው፣ ቅደም ተከተላዊነት የሚታይበትና በሆነ ምክንያት የሚፈጸም ዝግጅት አምስት የከበራ ይዘቶች አሉት፡፡ እነሱም ጫት፣ ቡና፣ ጭስ፣ የቡድን ድራማና ለማህበረሰቡ ትርጉም ያላቸው የተለያዩ ድርጊቶችና አምልኮዎች ናቸው፡፡ በዝግጅቱ ላይ ያለውን አጠቃላይ ገጽታ በሚገባ የገለጸው ሲሆን የገለጸበት አላማም የዝግጅቱ አውድና ድባብ በቃል ግጥሞቹ ትርጓሜና በታዳሚዎች ስሜት ላይ የሚፈጥሩትን ተጽኖ ለማሳየት የሚረዳ በመሆኑ ነው፡፡ይህም ቃል ግጥምን ከነአውዱ ለማጥናት ለሚሻ ተመራማሪ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ አንባቢያንንም በቃል ግጥሙ አውድ ውስጥ ሊያስገባ በሚችልና በተገቢው የምርምር ቋንቋ የቀረበ መሆኑ የምርምሩን ጥንካሬ የሚያሳይ ነው፡፡ስለሃድራ ከተሰጠው

የአውድ ገለጻ በተጨማሪ በሃድራው ተፈጥሯዊ መቼት ላይ የቀረቡት ፎቶግራፎች ሃድራውን በማሳየት በኩል ወሳኝ ናቸው፡፡

በብርሃኑ ገበየሁ ጥናት በአላማና በጥናቱም የሚታየው ጉዳይ ገጣሚያን፣ ደረሳ፣ ክዋኔ፣ ተስተላልፎና ምደባ የሚሉት ጽንሰሃሳቦች ናቸው፡፡ እነዚህ የቃል ግጥምን ለመረዳት የሚስፈልጉ ጽንሰሃሳቦች በጥናቱ አንድ በአንድ ዘርዘር ያለ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸው እናገኛለን፡፡ ማብራሪያ የተሰጠበት ምክንያት ደግሞ የተለያዩ አይነት የሙስሊም ገጣሚያንን ለማሳየት ነው፡፡ በዚህ ውስጥም ገጣሚያኑ ራሳቸውንና ግጥማቸውን የሚያዩበትን መንገድ የሚያስረዳ በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ወዳልተፈለገና አግባብነት ወደሌለው ትርጓሜ አጥኝውና አንባቢያን እንዳይሄዱ ልጓም የሚያደርግ ነው፡፡

የብርሀኑ ገበየሁ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር ከሚመሳስልበት ነጥቦች መካከል የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ስልት፣ መንዙማዎቹ ላይ አውዳዊ ትርጓሜ መስጠታችን፣ ለመንዝማዎቹ ትርጓሜ የተጠቀምንው የንድፈ ሀሳብ ምርጫ ነው፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያለያዩን ነጥቦች ደግሞ ብርሀኑ በዋና አላማነት ያነሳው የመንዙማዎቹን ገጣሚያን፣ ደረሳ፣ ክዋኔ፣ ተስተላልፎና ምደባ በዝርዝር ለመተንተን ሲሆን የኔ ጥናት ደግሞ በኡለማ መውሊድ ላይ የቀረቡትን መንዙማዎች የክዋኔ ሒደት ለመተንተን ነው፡፡

በአጠቃላይ ብርሃኑ ገበየሁ ጥናት የተነሳበትን አላማ ያሳካ እንዲሁም ያቀረባቸውን ግጥሞችም በተገቢው መንገድ የተነተነ እና ቴክስቶቹን በአውዳቸው ውስጥ በማስገባት የቃል ግጥም ንድፈሃሳቦችን በመጨመር ያሳየ ጥናት ነው። ከዚህ ጥናት በርካታ እውቀቶችን ያገኘሁ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የጥናት አወቃቀር የመረጃ አሰባሰብ አደረጃጀት የንድፈሃሳብና የስነዘዴ ምረጫ ተገቢነት ለምርምር የሚሰጠውን ትልቅ ዋጋ ከስነዘዴ አኳያ ሲሆን፤ ከንድፈሃሳብ አኳያ ደግሞ የቴክስትና የአውድ እንዲሁም የአጋጣሚ ትስስር ምርምርን ምን ያክል ምልዑ የሚያደርግ እንደሆነ በተጨማሪም ግጥምን ስንከፋፍል በተለመደው አይነት የመከፋፈያ መንገድ ሳይሆን በሃገር በቀል ዘር ምደባ ቢሆን የተሻለ እንደሚሆን ተገንዝቢያለሁ።ከዚህ ጥናት ያገኘሁበት ደካማ ጎን ከሰበሰባቸው ግጥሞች ውስጥ ትንታኔ ያልሰጠባቸውን አባሪ አድርጎ አለማቅረቡ ነው።

እነዚህ ሁለት ጥናቶች በመውሊድ ላይ የሚቀርቡ የቃላዊ ግጥሞችን (መንዙማዎችን) ክዋኔን በተመለከተ አውዱን መሰረት በማድረግ መተንተናቸው ከታች በመጀመሪያ ዲግሪ ከቀረቡት

ጥናቶች በተሻለ ከፍ ያለ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ በተለይ የብርሐኑ ገበየሁ ጥናት መንዙማዎቹ የሚባሉበትን የመውሊድ አውድ ከማሳየት ባለፈ ቃላዊ ግጥሞቹን አውድን መሰረት ባደረገ ዝንር ለመከፋፈል መሞከሩ ጥሩ የሚባል ጥናት ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

### 2.2.2 በመጀመሪያ ዲግሪ የቀረቡ ተዛማጅ ጥናቶች

#### 2.2.2.1 ቅኝት ያልተደረገባቸው ተቀራራቢ ጥናቶች

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በቀጥታ ከዚህ ጥናት ጋር ባለመገናኘታቸው አግኝቻቸው ቅኝት ያላካሔድኩባቸው 9 ጥናቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ቦጋለ ተፈራ (1972) "ሼህ ሁሴንና ግጥሞቻቸው"፣ ሐሊማ ሙሐመድ (1974) "ለባሌው ሼህ ሁሴን የተገጠሙ ግጥሞች"፣ ጥበቡ ሽፈራው (1976) "የሐጅ ሐሚድ መንዙማዎች ይዘት"፣ አብዱልናስር ሐጅ ሀሰን (1982) "የአውተራህም እና የአሽሪፍ ስርዓተ አምልኮ በደደር"፣ ኡመር ዳውድ (1982) "በአዲስ አበባ እስላሞች ዘንድ በመስጊድ ላይ የሚባሉ እንጉርጉሮዎች ጥናት"፣ ሙሐመድ ጀማል (1984) "በወሎ ክፍል ሐገር የሼህ ጫሌ የመውሊድ ግጥሞች (መንዙማዎች) ትንታኔ ከቅርጽና ከይዘት አንጻር"፣ አሊ የሱፍ (1995) "የሼህ ሙሐመድ የህይወት ታሪክ ሐድራቸው ክዋኔያቸውና ግጥሞቻቸው"፣ ሰይድ ሙሐመድ (1997) "የሼህ ሙሐመድ አወል መንዙማዎች ይዘት ትንተና"፣ ሙሐመድ በረሁ (2002) የሼህ ኡመር አብራር መንዙማዎች ፎክሎራዊ ጥናት" የሚሉ ናቸው፡፡

ቅኝት ያደረኩባቸውን ጥናቶች ግን ለአቀራረብ እንዲያመች በሚል ባተኮሩባቸው ርዕሰ ጉዳዮች በመመስረት  እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### 2.2.2.2 በኡለማ መዉሊድ ስርዓተ ክዋኔና በስርአቱ ላይ በሚቀርቡ ቃላዊ ግጥሞች ላይ ያተኮሩ የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች፣

ከኔ ጥናት ጋር በተመሳሳይ መልኩ የትኩረት ነጥባቸውን በኡለማ መውሊድ ስርዓተ ክዋኔና በስርዓቱ ላይ በሚቀርቡ ቃላዊ ግጥሞች ላይ ያተኮሩ ጥናቶች ተሰርተዋል፡፡ ከነዚህም መካከል በቀጥታ ከዚህ ጥናት ጋር በተገናኘ መልኩ ሊቃኙ የሚችሉ አራት ቀደምት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ቤተ መጽሐፍት ለማግኘት ተችሏል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ጥናታዊ ጽሑፎች ለዚህ ጥናት ባላቸው የቅርበት ደረጃ መሰረት ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

በዚህም መሰረት በቀጥታ ስርዓተ ክዋኔውና ቃላዊ ግጥሞቹ  ምን እንደሚመስል በመግለጽ የቀረቡ ቀደምት ጥናቶች ስንመለከት፤  ፅጌ ንጋቱ አስጨናቂ (1982) "የሼህ ሰይድ ቡሽራ

ታምራት አፈ-ታሪክና የመውሊድ በዓል አከባበር በገታ/ወሎ"፣ኪሩቤል ሸንቁጤ (1986) "የቃጥባሬው ሼህ ህይወት ታሪክና የበዓላቸው አከባበር"፣ መሐመድ ሁሴን (1997) "የገበሮች ሼህ የህይወት ታሪክና የበዓላቸው አከባበር"፣ አሸናፊ ምስጉን (1998) "የሼህ አሊ ጎሬ ታምራት አፈ-ታሪክና የበአላቸው አከባበር በጅጅጋ አካባቢ" በሚሉ ርዕሶች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች ናቸው፡፡

ፅጌ ንጋቱ አስጨናቂ (1982) "የሼህ ሰይድ ቡሽራ ታምራት አፈታሪክና የመውሊድ በዓል አከባበር በገታ/ወሎ" የሚለው ጥናት ለዚህ ጥናት በተዛማጅነት ሊቃኙ ይችላሉ ተብለው ከተመረጡት ጥናቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ጥናት ዋና ዓላማው አድርጎ የተነሳው የሼህ ሰይድ ቡሽራን ታዓምራትና አፈታሪክ ከመውሊድ በዓሉ አከባበር ጋር በማጣመር መተንተን ላይ ነው፡፡ በዚህም አፈ ታሪኩ በምዕመናኑ ላይ ያለውን ተጽዕኖ፣ ተግባራዊ አገልግሎቱን፣ የክዋኔ ተሳታፊዎቹና አጠቃላይ ይዘቱን ለመግለጽ ሞክራለች፡፡

ጽጌ መረጃዎቹን ለመሰብሰብና ይህን ጥናት ለማከናወን ቃለመጠይቅንና ምልከታን በዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልትነት ተጠቅማለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ልዩ ልዩ መጽሐፎችን በማጣቀስ እስልምና በኢትዮጵያ ያለውን ገጽታ አብራርታለች፡፡ የሰበሰባቸውን መረጃዎች ለመተንተን ገላጭ ስልትን ተጠቅማለች፡፡

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ከኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ይዘት ቢኖረውም ክፍተቶች ግን ነበሩበት፡፡ ከነዚህም መካከል በጉልህ የሚጠቀሱት ለምታቀርባቸው ጉዳዮች በቂ ማብራሪያ ያለመስጠት፣ በርካታ ጉዳዮችን ለመነካካት መሞከር (ማንሳቱ ጥሩ ቢሆንም ቁንጽል ሆኖ ከቀረበ ቅንጭባጫቢ ስለሚሆን አይመከርም) ፣ መረጃዎቹን በትክክል የት የት እንዳገኘቻቸው ያለመግለጽ እና ስለ ክብረ በዓልም ሆነ ክዋኔ ንድፈ ሐሳብ አስደግፋ ለማቅረብ ክፍተቶች ነበሩበት፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን የፅጌ ንጋቱ አስጨናቂ ጥናት አጠቃላይ የአጠናን ዘዴው፣ ዓላማውና የመረጃ አሰባሰቡ ከኔ ጥናት ጋር የመመሳሰል ገጽታ አለው፡፡

የኪሩቤል ጥናታዊ ጽሁፍ "የቃጥባሬው ሼህ ህይወት ታሪክና የበዓላቸው አከባበር" በሚል ርዕስ በጉራጌ ክልል ውስጥ ስለ አንድ ታላቅ ሰው የሚነገረውን የመውሊድ አከባበር እና በሥርዓቱ ላይ የሚነገሩ (የሚዜሙ) ግጥሞችን መሰብሰብ ዋና ዓላማው በማድረግ ጥናቱን አካሒዷል፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስም የተከተለው ስልት አውዳዊ አቀራረብ ሲሆን መረጃ

ለመሰብሰብ ደግሞ ምልከታና ቃለ መጠይቅን ተጠቅሟል፡፡ መረጃውን ለመተንተንም ገላጭ ስልትን ተግብሯል፡፡

በዚህም ጥናቱን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ከፋፍሎ አቅርቧል፡፡ ይህ ጥናት በመጀመሪያው ክፍል የጉራጌን ህዝብ አጭር ታሪክ የገለጸ ሲሆን በሁለተኛው ክፍል ደግሞ የቃጥባሬው ሼህ (ሼህ ዒሳ) የህይወት ታሪክ ቃላዊና የጽሑፍ መረጃዎችን በማጠናከር አቅርቧል፡፡ በሶስተኛው ክፍል ደግሞ አመታዊውን የሸህ ዒሳ የመውሊድ በዓል አከባበር ሐይማኖታዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ከመግለጹም በተጨማሪ የበዓሉን ቅድመ ዝግጅት እስከ ፍጻሜውና የበዓሉ ተሳታፊዎች ምን እንደሚመስሉ በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ በመጨረሻም ማጠቃለያ በመስጠት ጥናቱን አጠናቋል፡፡

በአጠቃላይ ኪሩቤል ጥናቱን ሲያጠናቅቅ ከጥናቱ በመነሳት ሼህ ዒሳ መስጊድ በማሰራት፣ የስግደት ቦታ በመወሰን፣ የቁርዓን ትምህርት ቤት በማስከፈት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ መሆናቸውን ይገልጻል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የእሳቸውን መልካም ስራና ህያውነት ለማስታወስ በሚከበረው በዓላቸው የሚሳተፉት ታዳሚዎች  መውሊድ በዓሉ ላይ ከፍተኛ የሆነ ሐይማኖታዊ እውቀት እንደሚያገኙ ይገልጻል፡፡ በመጨረሻም በዓሉ ከኢኮኖሚው አንጻር ምዕመናኑን ችግር ላይ የሚጥል ነው በማለት ጥናቱን ያጠናቅቃል፡፡

የኪሩቤልን ጥናት ከእኔ ጥናት የሚለየው ስለ ክብረ በዓልም ሆነ ክዋኔ ንድፈ ሐሳብ አስደግፎ ባለማቅረቡ እና የተመለከታቸውን ክዋኔዎች በጥልቀት ለምን እንደሚባሉ ባለመግለጹ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር አጠቃላይ የአጠናን ዘዴው፣ ዓላማውና የመረጃ አሰባሰቡ ከኔ ጥናት ጋር የመመሳሰል ገጽታ አለው፡፡

ለዚህ ጥናት በተዛማጅነት የተመረጠው ሌላው ጥናት የመሐመድ ሁሴን (1997) “የገበሮች ሼህ የህይወት ታሪክና የበዓላቸው አከባበር” በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ይህ ጥናት በዋናነት ዓላማው አድርጎ የተነሳው የገበሮች ሼህ የሱፍን የህይወት ታሪክና የበአላቸውን አከባበር መተንተን ላይ ነው፡፡ በዚህም በአላቸው ወቅት የሚደረጉ ዱአዎችንና የሚዜሙ የመንዙማ ግጥሞችን፣ የበአላቸው ክዋኔ ምን እንደሚመስልና በበአሉ ወቅት ምእመናን ያላቸው ሚና በመግለጽ አቅርቧል፡፡

መሐመድ ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ደግሞ ቃለመጠይቅንና ምልከታን በዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ስልትነት ተጠቅሟል፡፡ በዚህም በርካታ ቃል ግጥሞችን ሰብስቦ በምልከታ

ካስተዋለው ክዋኔ ጋር በማጣመር ትንታኔ ሰጥቷል። ለትንታኔው ደግሞ ገላጭ ስልትን ተግብሯል። በትንታኔውም የገበሮች ሼህ የህይወት ታሪክ፣ የአካባቢው ሰው ለእሳቸው ያለው አመለካከት፣ በእሳቸው የተፈጠሩ ታዕምራቶችን እና የክዋኔውን ሒደት ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው ከማሳየቱም በተጨማሪም ሐይማኖታዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የከበራውን ገጽታዎች ተመልክቷል። መሐመድ በዚህ መልኩ ያቀረበውን ጥናት ማጠቃለያ ስንመለከት በትንታኔው ያነሳውን ነጥብ ከመድገም ውጭ አንዳች ማጠቃለያ ላይ የሚያደርስ ነጥብ አልገለጸም። ይህን ባለማድረጉም ጥናቱ በዕንጥልጥል ላይ ያለ እስኪመስል ድረስ በመደምደሚያው ላይ ክፍተት ይታያል።

በአጠቃላይ የመሐመድን ጥናት ከኔ ጥናት የሚለየው ስለ ክብረ በዓልም ሆነ ክዋኔ ንድፈ ሐሳብ አስደግፎ ባለማቅረቡ፣ የተመለከታቸውን ክዋኔዎች በጥልቀት ለምን እንደሚባሉ አለመግለጹ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ለማሳያነት በትንታኔው ውስጥ ያቀረባቸውን የመንዙማ ግጥሞች ላይ በቂ ማብራሪያ አለመስጠቱ (አንዳንዴም መዝለሉ) እና በቂ ማጠቃለያ አለመስጠቱ ነው። ከዚህ ባሻገር አጠቃላይ የአጠናን ዘዴው፣ ዓላማውና የመረጃ አሰባሰቡ ከኔ ጥናት ጋር የመመሳሰል ገጽታ አለው።

ሌላው ተዛማጅ ጥናት በአሸናፊ ምስጉን (1998) "የሼህ አሊ ጎሬ ታምራት አፈታሪክና የበአላቸው አከባበር በጅጅጋ አካባቢ" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሼህ አሊ ጉሬ ታምራት፣ አፈታሪክና የበዓላቸው አከባበር ምን እንደሚመስል መግለጽ ነው። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስም የተከተለው ስልት አውዳዊ አቀራረብ ሲሆን መረጃ ለመሰብሰብ ደግሞ ምልከታና ቃለ መጠይቅን ተጠቅሟል።

መረጃውን ለመተንተንም ገላጭ ስልትን ተግብሯል። በዚህም የህይወት ታሪካቸውን፣ ዓመታዊና ሳምንታዊ የመውሊድ በዓል አከባበሩን ከመግለጹም በተጨማሪ በሕይወት ዘመናቸውና ሕይወታቸው ካለፈ በኂላ ፈጽመዋቸዋል ተብለው በቃል የሚተረኩ የሼህ ዓሊ ጉሬ ተዓምራቶች በምዕመናኑ ላይ የሚያሳድሩትን ስነ ልቦናዊ ተጽዕኖ ለመግለጽ ሞክሯል። ከዚህም በተጨማሪ የበዓሉን ሐይማኖታዊና ማህበራዊ ገጽታዎች ከበዓሉ ተሳታፊዎች ጋር በማያያዝ ገልጿል። በመጨረሻም ከበዓሉ ዋዜማ እስከ ፍጻሜ የሚታየውን ክዋኔ ምዕመናን በበዓሉ ላይ በሚፈጽሟቸው ተግባራት በመመስረት በአጭሩ ገልጿል።

በአጠቃላይ የአሸናፊን ጥናት ከኔ ጥናት የሚለየው ስለ ክብረ በዓልም ሆነ ክዋኔ ንድፈ ሐሳብ አስደግፎ ባለማቅረቡ፣ ከተሰራበት ዘመን አንጻር ቀደምት በሱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተጠኑ ተገቢ (በመውሊድ በዓል ስርዓተ ክዋኔ ላይ ያተኮሩ ጥናቶች) ቅኝት ካለማካሔዱም በተጨማሪ የተመለከታቸውን ክዋኔዎች በጥልቀት ለምን እንደሚባሉ አለመግለጹ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር አጠቃላይ የአጠናን ዘዴው፣ ዓላማውና የመረጃ አሰባሰቡ ከኔ ጥናት ጋር የመመሳሰል ገጽታ አለው፡፡


በአጠቃላይ ከላይ የጠቀስኳቸውን ቀደምት ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ ያየኋቸውን ክፍተቶች በማስተዋል ይገኘው የተነሳሁት ርዕሰ ጉዳይ የጥናት ደረጃ ምን ያህል እንደደረሰ ማወቅ ይቻላል፡፡ እኔም ከዚህ በመነሳት የሐጅ ሁሴን (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓልን መሰረት በማድረግ የሚከበረውን የመውሊድ በዓል (የኡለማ መውሊድን) አከባበር ስርዓት፣ ክዋኔውን፣ ማህበራዊ ፋይዳው እና አውዱን አጥንቼ አቅርቤለሁ፡፡ በዚህም በሌሎች ቀደምት ጥናቶች ላይ በስፋት ያልተስተዋለውን የከበራው ስርዓትና የሁነቶች ትስስር፣ የክዋኔው ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳ እና የሚፈጸሙ ድርጊቶችን (ዝየራ፣ ዱኣ (ምርቃት) እና መንዙማ) ከአውዱ በመነሳት አጥንቻለሁ፡፡

# 3. ጥናቱ የተካሔደበት ማህበረሰብ አካባቢያዊ ዳራና የሼህ ሁሴን አለሙ የሕይወት ታሪክ

## 3.1 ጥናቱ የተካሔደበት አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ

የአዊ ዞን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙት አስራ አንድ ዞኖች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ዞን ደግሞ በክልሉ ከሚገኙት ሶስት የብሄረሰብ ዞኖች (ሰቆጣ፣ ኦሮሚያና አዊ) አንዱ ሲሆን  በውስጡ ስምንት ወረዳወችና ሶስት ከተማ አስተዳድሮች አቅፎ ይዟል፡፡[2] ይህ ጥናት በዋናነት ከነዚህ ሶስት ከተማ አስተዳድሮች (እንጅባራ፣ቻግኒ እና ዳንግላ) መካከል በዳንግላ ወረዳ በምትገኘው በዳንግላ ከተማ አስተዳድር ውስጥ የተካሔደ ነው፡፡

ዳንግላ ከተማ ከአዲስ አበባ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ 471 ኪ.ሜ ፣ ከክልሉ ባህር ዳር ከተማ በ76 ኪ.ሜ እና ከዞኑ ርዕሰ ከተማ እንጅባራ በ36 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ናት፡፡




*ምስል ፦ የዳንግላን ከተማ የሚያሳይ ካርታ (ምንጭ ጎግል ኧርዝ)*

ከተማዋ በ $11^{\circ}$ $18^{N}$ ላቲቲዩድ እና በ$36^{\circ}$ $57^{E}$ ሎንግቲዩድ ላይ ከበሀር ጠለል በላይ በ 2190 ሜትር ከፍታ ላይ ትገኛለች፡፡ የዚች ከተማ የቆዳ ስፋት 9486.4 ሔክታር ሲሆን የአየር ንብረቷ ወይና ደጋ የሆነ እና በአመካኝ 18℃ የሙቀት መጠን እና 1481.25 ሚ.ሜ የዝናብ

---

[2] ምንጭ በ2001 ዓ.ም የታተመው "ገጽታ" መጽሔት የዳንግላ ከተማ አስተዳድር አመሰራረትና የዕድገት ደረጃ (አቶ አሳየ አንተነህ) ብሎ ባሳተመው ዕትም ላይ የተገኘ መረጃ፡፡

መጠን አላት፡፡ አጠቃላይ ከተማዋ አምስት የከተማ እና አምስት የገጠር ቀበሌዎች ያሏት ሲሆን የሚያዋስኗትም ዙሪያ ወረዳዎች በሰሜን ጉልት አብሽካን፣ በደቡብ ጉንድሪና ኳንድሻ በምስራቅ ዘለሳ እና በምዕራብ አጋጋና ድምሳጢምም ናቸው፡፡

በ2005 ዓ.ም የከተማ አስተዳድሩ ባለው መረጃ መሰረት በከተማዋ ውስጥ በሚገኙ አምስት ቀበሌዎች የሚገኙ የህዝብ ብዛት 15940 ወንድ እና 16003 ሴት በድምሩ 31943 ሲሆን በአምስቱ ገጠር ቀበሌዎች 2235 ወንድ እና 1201 ሴት በድምሩ 3436 ሲሆን አጠቃላይ የከተማዋ የህዝብ ብዛት ወንድ 18175 ሴት 17204 በድምሩ 35379 ነው፡፡

በከተማዋ ውስጥ የሚኖረው ነዋሪ የብሔር ስብጥር አማራ 78%፣ አገው 21%፣ ትግሬ 0.3%፣ ኦሮሞ 0.1% እና ሌሎች 0.6% ነው፡፡ በከተማው ውስጥ በስፋት የሚነገረውን የአማርኛ ቋንቋ ሲሆን አልፎ አልፎ የአዊኛ ቋንቋ ይነገራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የከተማ መስተዳድሩ የስራ ቋንቋ አማርኛ ነው፡፡[3] በከተማዋ ውስጥ የሚገኙትን የዕምነት ስብጥር ስንመለከት ኦርቶዶክስ 88.4%፣ ሙስሊም 11%፣ ፕሮቴስታንት 0.6% ነው፡፡

### 3.2 የዳንግላ ከተማ አሰያየምና አመሰራረት

የዳንግላ ከተማ ስያሜን በተመለከተ የሚነገረው አፈ-ታሪክ እንደሚያስረዳው፣ ከሰባቱ የአገው አዊ መስራች ወንድማማቾች[3] አንዱ የሆነው  ዳንግሊ ይኖር የነበረው በዚች ከተማ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚነገረው ነው፡፡ ይህ አፈ-ታሪክ የከተማዋን አሰያየም ሲያስረዳ የ"ዳንግሊ" ወንድሞች ወደዚች ከተማ በመምጣት "ዳንግሊ አለ" ብለው ሲጠይቁ "ዳንግሊ  ዕላ" (ዳንግሊ የለም) የሚል ምላሽ ያገኛሉ፡፡ ከዚህም ምላሽ ተነስተው "ዳንግሊ ዕላ" (ዳንግሊ የለም) የሚለው በሒደት ወደ "ዳንግላ" እንደተቀየረ ከ76 አመት አዛውንቱ ከአቶ በየነ መርሻ ጋር በቀን 12/05/2005 ዓ.ም ባደረኩት ቃለመጠይቅ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ በመሆኑም የዳንግላ ከተማ ስያሜዋን ያገኘችው ከሰባቱ የአገው መስራች ወንድማማቾች አንዱ በሆነው "ዳንግሊ" ስያሜ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

የዳንግላ ከተማ አመሰራረትን በተመለከተ በ2001 ዓ.ም የታተመው "ገጽታ" መጽሔት በመረጃ ላይ ያልተመሰረቱ አፈ-ታሪኮች እንደሚያስረዱት የዳንግላ አመሰራረት ከንግድ እንቅስቃሴ ጋር

---

[3] ምንጭ የዳንግላ ከተማ አስተዳድር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት፤

[3] ሰባቱ የአገው አዊ መስራች ወንድማማቾች የሚባሉት፤ባንጂ፣አንክሸ ፣ኳኩሪ፣ቱምሂ፣ዳንግሊ፣ዚገሚ እና ቻሪ እንደሆኑ ከ76 አመት አዛውንቱ ከአቶ በየነ መርሻ ጋር በቀን 12/05/2005 ዓ.ም ባደረኩት ቃለ. ለመረዳት ችያለሁ፡፡

የተያያዘ መሆኑን ይገልጻል። በዚህ ገለጻ መሰረትም ዳንግላ በሚባል ገበያ ዚጉዳ ኪዳነ ምህረት አካባቢ በአዳም ሰገድ እያሱ (በአፄ እያሱ ዘመነ መንግስት) 1676-1696 ዓ.ም በወቅቱ የዳንግላና አቸፈር ገዥ በነበሩት በኪዳኑ ዲቁ እንደተቋቋመ ይነገራል። ከዚህ በተጨማሪም ለአጋው ምድር እና የአቸፈር ነጋዴዎች መቀመጫ ከመሆኗም በተጨማሪ ለረጅም ጊዜ የቀረጥ ማስከፈያ ኬላ እንደነበረች ይነገራል።

"ገጽታ" መጽሔት የታዋቂው ስኮትላንዳዊ አሳሽ ጀምስ ብሩስን (1761-1763) የጉዞ ማስታወሻ መሰረት አድርጎ እንዳቀረበው፣ "ወደ ዳንግላ ገበያ ልዩ የሆነ በግ ይመጣል ስሙንም ሙክት ይሉታል።" በሚል ያሰፈረውን በማጣቀስ የአሁኗ ዳንግላ ከተማ ከተቆረቆረች ቢያንስ ከ240 አመት በላይ ማስቆጠሯን ይገልጻል።

ይህ መሰረቱን ዳንግላ ያደረገው የንግድ እንቅስቃሴ በስድስት ዋና ዋና የንግድ መስመሮች የተዘረጋ ሲሆን እነሱም፡-

1. ከዳንግላ አዲስ ቅዳም እንጅባራ፣ ቡሬ፣ ደ/ማርቆስና ባሶ ሲሆን
2. ከዳንግላ በጫራ፣ቻግኒ፣ በወንበራ ሊሙ ይዘልቃል።
3. ከዳንግላ ሳምሲ ፈረስ ወጋ ይዘልቅና ለሁለት በመክፈል አንዱ ወደ ደብረታቦር

   ሲያቀና ሌላኛው መስመር ደግሞ በአዴት ወደ ሞጣ የሚያደርስ ነው።
4. ከዳንግላ - ዱርቤቴ - መራዊ - ባህርዳር - በጌ ምድር ሲሆን
5. ከዳንድላ - ዘጌ - ጎንደር የሚሔደው እና
6. ከዳንግላ - ይስማላ - ቋራ - መቻያ - ግብ ግቢት - ቆላ ድባ፣ አዘዞ፣ ጎንደር ሲሆኑ በዚህ መስመር ወደ መተማ የሚደረገው የንግድ እንቅስቃሴ እንደሚካተት መረጃዎች ያመላክታሉ።[4] ይህ የንግድ እንቅስቃሴ የኢትዮ-ጅቡቲ የባቡር ሀዲድ መገንባትን ተከትሎ ከደቡብ ኢትዮጵያ አቅጣጫ ጋር ያለው እንቅስቃሴ ቢቀዛቀዝም በወቅቱ የነበረው የባሪያ ንግድ[5] እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ ይካሔድ ነበር።

---

[4] ይህ መረጃ የተገኘው የዳንግላ ከተማ አመሰራረትን በተመለከተ በ2001 ዓ.ም የታተመው "ገጽታ" መጽሔት ላይ ሲሆን መጽሔቱ መረጃውን የተጠቀመው ደግሞ በ1904 ዓ.ም በሻለቃ ዳውቲ ዋይሌ የተደረገውን ጥናት መሰረት በማድረግ ነው።

[5] በኢትዮጵያ ይደረጉ የነበሩ የባሪያ ንግድ እንቅስቃሴዎች ወቅት ዳንግላም ከይፋግ ጋር በተመሳሳይ መልኩ የንግዱን እንቅስቃሴ ታካሒድ ነበር። እንዲያውም "ገጽታ" መጽሔት ላይ የተገለጸው መረጃ እንደሚያመላክተው፣

ለአሁኗ ዳንግላ በዘመናዊ መልክ መመስረት ተጠቃሽ ከሚሆኑት በዋናነት ከ1910 እስከ 1920 አመታት የተቋቋሙት ልዩ ልዩ ተቋማት ሲሆኑ ለምሳሌ፡- በ1912 ዓ.ም የፖስታ አገልግሎት መጀመሩ፣ የተለያዩ መጠጥ ቤቶች መከፈታቸው እና የተለያዩ የእደጥበብ ባለሞያዎች መታየታቸው እንደሆነ ይነገራል፡፡ በተጨማሪም እንግሊዝ በ1914 ዓ.ም በከተማዋ የቆንጽላ ጽህፈት ቤት መክፈቷ፣ በ1918 ዓ/ም ሎኒል ሳንድፎርድ በተባለ እንግሊዛዊ የሽቀጣሽቀጥ ሱቅ መከፈቱ እና የተለያዩ ማህበራዊ (የጤና፣ የትምህርት፣ የማዘጋጃ ቤት እና የፍትህ) ተቋማት መከፈታቸው እንደምክንያት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

በዚህ ሁኔታ የጀመረው የከተማዋ እድገት ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ በመሄዱ ከ1934 ዓ/ም እስከ 1948 ዓ/ም ድረስ የጎጃም ጠቅላይ ግዛት ከነበሩት አምስት አውራጃዎች ውስጥ አንዷ በመሆን የአገው ምድር፣ የባህር ዳር እና የመተከል ዋና ርዕሰ ከተማ ሁና እንድታገለግል አድርጓታል፡፡ በ1948 ዓ/ም መተከል እንዲሁም በ1949 ዓ/ም ባህር ዳር እራሳቸውን ችለው አውራጃ ከሆኑ በኋላ ሦስት ወረዳዎችን (አንከሻ ፣ባንጃ እና ዳንግላ) በመያዝ እስከ 1983 ዓ/ም የአገው ምድር አውራጃ ዋና ከተማ በመሆን ቆይታለች፡፡

በመጨረሻም ከተማዋ ከ1983 ዓ/ም እስከ 2000 ዓ/ም ድረስ የዳንግላ ወረዳ ከሆነች በኋላ በ2001 ዓ/ም ባገኘችው በከንቲባ የመተዳደር ዕድል መሰረት ጀምሮ የዳንግላ ከተማ አስተዳደር በመባል ተሰይማ በውስጧ 5 የከተማ እና 5 የገጠር ቀበሌዎችን በማስተዳደር ትገኛለች፡፡

### 3.3 የነሼህ ዳንግላ (ሐጅ ሁሴን አለሙ) መስጅድ አመሰራረት

የነሼህ ዳንግላ መስጅድ በከተማው ውስጥ ከሚገኙ ሶስት ታላላቅ መስጅዶች አንዱ ነው፡፡ የዚህ መስጅድ አመሰራረትን በተመለከተ ሐጅ ሙሀመድ ሐሰን[6] በቀን 12/05/2005 ዓ.ም በተደረገ ቃለ ምልልስ ላነሳሁላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጡኝ፡-

> …መስጅዱ አሁኑን ቅርጽ ከመያዙ በፊት እነሼህ እዚያው እግቢያቸው አነስ ያለ ለመስገጃነትና ለዱኣ ማድረጊያ የምትሆን እራሷን የቻለች ከለዋ (ትንሽ መስጊድ) ነበረች፣ ይሁንና ይቺ መስጊድ እነሼህን ብሎ የሚመጡ እንግዶችን ለማስተናገድ ስላልቻለች ይህንን ችግር የተረዱት የቅርብ ዘመዶቻቸው ማለትም ከሼህ የሱፍ ሀሰን እና ሐጅ አህመዴ ሀሰን "አንተ እንግዳህ ብዙ ነው ሰፋ ያለ መስጅድ

---

ከተማዋ የባሪያ ንግድ እንቅስቃሴ ከይፋግ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ መደረጉ የከተማዋን የረጅም እድሜ ባለቤትነት ለመጠቆም በዋቢነት ያቀርባል፡፡

[6] እኚህ ሰው በነሼህ ዳንግላ መስጅድ ግንባታ ላይ የሳተፉና ሐጅ ሁሴን አለሙን በህይወት የሚያውቋቸው ሲሆኑ የቅርብ ዝምድናም ያላቸው ናቸው፡፡

ያስፈልግሀል፤ ስለዚህ በዚህ ቦታ ላይ ትልቅ መስጅድ ስራ” በማለት ሰፊ ቦታ ሰጧቸው። እነሼህም ህብረተሰቡንና ዘመዶቻቸውን በማስተባበር በ1962 ዓ.ም የያሁኑን መስጅድ አሰሩ።…

በተመሳሳይ መልኩም ከአቶ ኡስማን ሰኢዱ ጋር ከላይ በተጠቀሰው ቀን በተደረገ ቃለ መጠይቅ ከበራው የሚካሔድበት ቦታ አመሰራረት በተመለከተ የቀረበውን ጥያቄ ሲብራሩ፡-

…የቦታው አመሰራረት በሀይለስላሴ ጊዜ ነው። የሼሆቹ አጎት ነበሯቸው፣ ሐጅ አህመድ ሀሰን ናቸው በስጦታ ያበረከቱላቸው። ሲሰጧቸውም “አንተ እንግዳህ ሰፊ ነው። ሰፊ ቦታ ያስፈልግሀል፤” በማለት ነው ያበረከቱላቸው። ከዚያ በኋላ ይኸ የምታዩት መስጊድ ተሰራ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አሁን 43ኛ አመቱ ነው ይኸ መውሊድ መከበር ከጀመረ፣ በየጊዜውም እንግዳው ከአመት አመት እየጨመረ አሁን ከምታየው ደረጃ ላይ ደርሷል።

በማለት ነግረውኛል። ከነዚህ ገለጻ ለመረዳት እንደሚቻለው መስጅዱ የአሁኑን ቅርጽ ከመያዙ በፊት በትንሽ መስጅድ እንደተጀመረና በ1962 ዓ.ም የያሁኑን መስጅድ መሰራቱን ነው። የዚህ ጥናት አቅራቢም በጥናቱ ወቅት በምልከታ ለማስተዋል እንደቻለው በ1962 ዓ.ም ከተሰራው መስጅድ በተጨማሪ በቋሚነት የመውሊድን ክብረ በዓል ለማክበር የሚያገለግል አንድ ሰፊ አዳራሽ መገንባቱን ተመልክቷል። በተጨማሪም ከአቶ ኡስማን ሰኢዱ (የመውሊዱ ክብረ በዓል ሊቀ መንበር) ጋር በዕለቱ በተደረገ ቃለ ምልልስ አዳራሹ ከመውሊዱ ማክበሪያነት በተጨማሪ የረመዷን ወርን የተርሐዊ ሶላት መስገጃነት በመሆን እንደመስጅድ እንደሚያገለግል ለመረዳት ተችሏል።




ምስል ፡- ከግራ ወደ ቀኝ በ1962 ዓ.ም ተሰራው የነሼህ ዳንግላ መስጅድ እና ለመውሊዱ ማክበሪያ የተሰራው አዳራሽ ከፊል ገጽታ

ከላይ ከቀረቡት ምስሎች በተጨማሪ የመውሊዱ ክብረ በአል በሚከናወንበት ወቅት ለሚመጡ ተሳታፊዎች ማረፊያ፣ ለሴቶች የጸሎት ማከናወኛ፣ ለሌሎች እምነት ተከታዮች ማስተናገጃ፣ ለምግብ ማከማቻና ማብሰያ የሚያገለግሉ በጊዜያዊነት የሚሰሩ ተጨማሪ ዳሶችና ድንኳኖች መዘጋጀታቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ከዚህ በተጨማሪ የዚህ መስጅድ ታሪክና የመውሊዱ ክብረ በአል ሲነሳ በዋናነት በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ልዩ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል በመስጅዱ ውስጥ የሚገኘው የውሀ ጉድጓድ አንዱ ነው። ይህን የውሀ ጉድጓድ በተመለከተ ሐጅ ሙሀመድ ሐሰን ሲገልጹ፡-

> … ሼሆቹ "እዚህ ላይ ውሀ ጉድጓድ ቆፍር" አሉኝ፤ እኔም በጣም እቀርባቸው ስለነበር ውስጡ ድንጋይ እንዳይኖረው ይመርምሩልኝ አልኳቸው። እሳቸውም ምን ለማለት እንደፈለኩ ስለገባቸው፣ ሳቅ ብለው "ወደ ጎን አድርገህ የምታገኘውን ድንጋይ እለፈው" አሉኝ። እኔም በምቆፍርበት ወቅት ከጎኔ ተቀምጠው ያወሩኝ ነበር። ለ5 ቀናት ያህል ከቆፈርኩኝ በኋላ ውኃው ተንፎልፉሎ ሲወጣ እነሼህ "ለቡዙ ሚሊዩን አመት የተደበቀው ወጣ ጠጣው… ጠጣው…" አሉኝ። ስጠጣው እነሼህም "ከእንግዲህ ስምህን ቀይሬዋለሁ፣ ሙሀመድ ባህሩ ብየኂለሁ" አሉኝ። ከዚያ በኋላ በተለያዩ ሰዎች እድሳት እየተደረገለት ቆይቶ በመጨረሻም እነሼህ ከሳውዲ ለሐጅ ደርሰው ሲመጡ ካመጡት ማኡ ዘምዘም (መካ ውስጥ የሚገኝ ቅዱስ ውሀ) ጨመሩበት። ከዚያን ቀን ጀምሮ እንደመዳኒትነት ያገለግላል …በቃ ከዛ በኋላ ደርቆም አያውቅም፣ እድሳትም አልተደረገለትም። በዚህ መልኩ ለረጅም አመታት ሲያገለግል ቆይቶ፣ ዘመናዊ ለማድረግ ተፈልጎ ሻለቃ ብርሐኑ የተባለ የመንግስት ባለስልጣን ባደረገው ድጋፍ በ1987 ዓ.ም በብረት መነቅነቂያ ውሀው እንዲወጣ ተደርጎ እስካሁን እያገለገለ ይገኛል። ከመድሀኒትነት ባሻገር በከተማው ውሀ በጠፋ ጊዜም እስላም ክርስቲያኑ ለመጠጥ ይጠቀምበታል። (10-06-05 በክበራው ቦታ የተደረገ ቃለ መጠይቅ)

በማለት የውሀውን አመሰራረትና ታሪክ ነገሩኝ። ከዚህም በመነሳት የነሼህ ዳንግላ መስጅድ የአመሰራረት ታሪክ ሲነሳ ይህ ውሀም የታሪኩ አንዱ አካል ተደርጎ ይወሰዳል። (ይህ ውሀ በክብረበአሉ ተሳታፊዎች የሚሰጠውን ትርጓሜ በቀጣዩ ምዕራፍ በክዋኔው የመጨረሻ ክፍል የምንመለከት ይሆናል።) አጠቃላይ የሼህ ሁሴን አለሙ መስጅድ ከከተማው የያዘው ቦታ በቀጣይነት ከሳተላይት በተወሰደ ምስል መመልከት ይቻላል።




**ምስል ፡- በዳንግላን ከተማ መውሊዱ የሚከበርበትን ቦታ የሚያሳይ ካርታ (ምንጭ ጎግል ኧርዝ)**

### 3.4 የሐጅ ሁሴን አለሙ የህይወት ታሪክ

ሐጅ ሁሴን አለሙ ከአባታቸው ከአቶ አለሙ ሀሰንና ከእናታቸው ወ/ሮ ሻሸቱ አቡበክር በ 1912 ዓ.ም በይልማና ዴንሳ ልዩ ስሙ መንደረ ኢየሱስ በተባለ ቦታ ተወለዱ፡፡ አባትና እናታቸው በንግድና በግብርና ስራ ይኖሩ ነበር፡፡ ከሼሆቹ በፊት አንድ ወንድና ሶስት ሴት የወለዱ ሲሆን ሐጅ ሁሴን አለሙ ለቤተሰባቸው አምስተኛ ልጅ ነበሩ፡፡ አባታቸው አቶ አለሙ ሐሰን የሼሆቹ ታላቅ ወንድም የሆኑትን ሐጅ ይሁኔ አለሙ ገና በልጅነታቸው በሬ ጠምደው ወደ እርሻ ሲልኳቸው ልጃቸውን ሼሆቹን ግን ምንም አይነት ስራ እንደማያዟቸውና በተለየ አክብሮት በማየት ልጄ ቁርአን ብቻ መቅራት አለበት በማለት ያበረታቷቸው ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ሐጅ ሁሴን አለሙ እድሜያቸው ለቁርአን ሳይፈቅድ ከሰፈራቸው ከነበሩ ሼህ የህያ ጅብሪል ቁርአን በሉህ[7] እያስከተቡ ከታላቅ ወንድማቸው ጋር እርሻ ቦታ ሂደው ወንድማቸው ሲያርሱ ሼሆቹ በልጅነታቸው ከድንጋይ ላይ ተቀምጠው ብቻቸውን ቀርአን ሲቀሩ ውለው ማታ ወደቤታቸው ይመለሱ ነበር፡፡ በዚህ አይነት እያስከተቡ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ሲቀሩ ቆይተው እራሳቸውን ችለው መቅራት ጀመሩና በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ጨረሱ (ኸተሙ)፡፡

---

[7] ሉህ በቁርአን ትምህርት ቤት ቁርዓን ለመክተቢያነት (ለመጻፊያነት) የሚያገለግል ከጠፍጣፋ ጣውላ የሚዘጋጅ ነው፡፡ አንድ ቁርዓን የሚማር ሰው በጣውላው ላይ የተጻፈውን ቁርዓን ሙሉ በሙሉ ማወቁ ከተረጋገጠ በኋላ በውሀ በማጠብ እንደየአካባቢው ነጭ አመድ ወይም የሸክላ አፈር ቀብቶ በማድረቅ በድጋሚ ቀጣዩ የቁርአን ትምህርት ይከተብበታል (ይጻፍበታል)፡፡

ቁርአን አስከትበው ወደ እርሻ ቦታ ሲሔዱ በጣም አስተዋይና ገና በልጅነታቸው ዝምተኛ በመሆናቸው አባታቸው "ሁሴን አባታችሁ ስለሆነ አባ ሐጅ ሁሴን በሉት" እያለ ህጻን ጓደኞቻቸውን ያስተባብሩና አብረው እንዲቀሩ ያደርጓቸው ነበር፡፡ በጣም አክብረው ይይዟቸው እንደነበርና እናታቸውም ገና ከልጅነታቸው ጀምረው በክበር እንደያዟቸው፤ በልጅነት እድሜ ከልጅ ጋር ተጣልተው ወይም ተሳድበው የመምጣት ልምድ በጭራሽ እንዳልታየባቸው ታላቅ ወንድማቸው ሐጅ ይሁኔ አለሙ በታላቅ አክብሮት ይናገሩ ነበር፡፡

ሼሆቹ ቁርአን እንደጨረሱ አባታቸው በሞት ተለዩ፡፡ በዚህን ጊዜ እድሜያቸው 11 ዓመት ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ ለ6 አመታት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ቆይተው በ1929 ጣሊያን አካባቢውን ሲወር ዘጌ ወደ አጎታቸው አቶ እንዳለው ሐሰን ሒደው ለ10 ዓመት ያህል ሼህ የሱፍ ከተባሉ ሰው ኢልም ሲታአለሙ[8] ቆዩ፡፡ ከዚህ በኋላም ተመልሰው ባህር ዳር ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመሆን ከ1930-1936 ዓ.ም ኢልም ሲታአለሙ ቆይተው በ1936 ዓ.ም ከአጎታቸው ልጅ ኢብራሂም ሙሀመድ ጋር ሁነው ኢልም ለመታአለም ወደ ጎንደር ጠንታ ወደተባለ ቦታ ሄዱና ለአንድ አመት ያህል ሲታአለሙ ቆይተው አብሯቸው የሄደው የአጎታቸው ልጅ ስለሞተ ፋቲሀ[9] በማሰኘት ሼሀቹውን አስፈቅደው ወደ ቤት ሲመለሱ በ1937 ቤተሰባቸው ከባህር ዳር ዳንግላ መግባታቸውን ሲሰሙ በቀጥታ ወደ ዳንግላ መጡ፡፡

ዳንግላ እንደደረሱም እናታቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በሰላም አግኝተው የአጎታቸውን ልጅ ሞት ተናግረው ፋቲሀ ካሰኙ በኋላ እዛው ዳንግላ ቂራታቸውን ቀጥለው ለሁለት አመታት እንደቆዩ ወንድማቸው ሐጅ ይሁኔ አለሙና በጥሩ ሁኔታ ይንከባከቧቸው የነበሩት አጎታቸው ሐጅ አህመዴ ሀሰን ተመካክረው የሸሆቹን ፈቃድ ጠይቀው በ1939 ዓ.ም ከወ/ሮ ገዳ አብዴን ጋር አጋቧቸው፡፡ ሼሆቹ ትዳር በመሰረቱበት ወቅት የቤተሰቦቻቸውን ፈቃድ ለመፈጸም እሽ አሉ እንጅ ትዳራቸውን የሚመሩበት ገቢም ሆነ ገንዘብ አልነበራቸውም፡፡ ነገር ግን የመጨረሻው ትልቁ ገንዘባቸው ቁርአንና ሐዲስ በመሆኑ ህይወታቸው ተጀምሮ እስኪጨርስ የፈለጉትን አላማ ከግብ ማድረስ ችለዋል፡፡[10]

---

[8] ኢልም መታለም ማለት እስላማዊ የሆኑ ትምህርቶችን መማር (ትምህርቱ የሚካሔደው ከቀደሙት የእምነቱ አዋቂዎች (ኡለማዎች) ነው)፡፡

[9] ፋተሀ ማለት ለሞተ ሰው የሚቀራ ቁርአን ወይም የሚደረግ ዱአ (ጸሎት) ነው፡፡

[10] አቶ ሙሀመድ አሊ (የሼህ ሁሴን አለሙን የህይወት ታሪክ የሚዳስስ መጽሐፍ በማዘጋጀት ላይ የሚገኝ) በቀን 09/05/2006 ዓ.ም በተደረገ ቃለ መጠይቅና ከሚያዘጋጀው መጽሐፍ ረቂቅ ላይ የተወሰደ፡፡

ከአቶ ሙሀመድ አሊና ከሐጅ ሙሀመድ ሐሰን ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በሳቸው ዙሪያ እየተዘጋጀ ባለው መጽሀፍ ላይ ባገኘሁት መረጃ መሰረት ሐጅ ሁሴን አለሙ ከወ/ሮ ገዳ አብዴን ጋር በመሆን መንድማቸው በሰጣቸው ጎጆ መኖር ይጀምራሉ፡፡ በዚህ ጊዜም የራሳቸው መተዳደሪያ ስላልነበራቸው ንግድ ስራ እንዲጀምሩ ቢያደርጓቸውም ውጤታማ አልነበሩም፡፡ በአንጻሩ እቤታቸው በመቀመጥ ቁርአን በመቅራትና ዚክር በመዘከር ይውሉ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ አካባቢዎች እተዘዋወሩ ከታላላቅ ሼሆች ኢልም ታልመዋል፡፡ በትዳር ዘመናቸውም ስድስት ልጆችን አፍርተዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ደግሞ አራቱ ወንዶች ሲሆኑ ሁለቱ ሴቶች ናቸው፡፡



**ምስል ፡- ሼህ ሁሴን አለሙ፡፡**

ሼሆቹ ህይወታቸው እስካለፈበት በ1986 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ ሐገራት (ሱዳንና ግብጽ) በመሔድ የእስልምና አስተህምሮን በተለያዩ አሊሞች ታልመዋል፡፡ ከውጭ ከተመለሱ በኋላ

ደግሞ ወደ ዳንግላ በመመለስ ለአካባቢው ማህበረሰብ አሰጋጅ ኢማም በመሆን ልዩ ልዩ ኢስላማዊ ትምህርቶች ሰጥተዋል፡፡ በነዚህ ጊዜያት ታዲያ በአካባቢው ከሚገኙ ትልልቅ አሊሞች ያገኙዋቸውን እውቀቶች ከማካፈል ባለፈ የአካባቢው ሙስሊም ማህበረሰብ በዲኑ ጠንካራ እንዲሆን በርካታ ስራዎችን አከናውነዋል፡፡ ሼሆቹ በመጨረሻው የህይወት ዘመናቸው ህልፈታቸው በመካ እንዲሆን በማሰብ ወደዚያው አምርተው በዚያው እንደተቀበሩ ከቅርብ ዘመዶቻቸው ያገኘሁት መረጃ ያመላክታል፡፡ ይህን ያደረጉበትን ምክንያት ከላይ ስማቸውን የጠቀስኳቸው መረጃ አቃባዮች ሲገልጹ "ሼሆቹ ቀብራቸው ከዚህ እንዳይሆን አጥብቀው መመኘታቸው፣ የአካባቢው ህብረተሰብ በተሳሳተ መልኩ ቀብራቸውን እንዳይዘየርባቸው በመስጋታቸው መሆኑ አንዱ ምክንያት ነው፡፡" ብለውኛል፡፡

ሐጅ ሁሴን አለሙ በህይወት ዘመናቸው ለህብረተሰቡ ያበረከቱት አስተዋጾ ስንመለከት ደግሞ ለዳንግላና አካባቢው ማህበረሰብ ቁርኣን እና ሀዲስ ማስተማር፣ እስልምና የሚከለክላቸውን የአምልዕኮት ተግባራትን መከልከል (በጠንቋይ ከአላህ ጋር በማሻረክ ያምኑ የነበሩትን ሰዎች ወደ እስልምና መመለሳቸው)፣ የተለያዩ በሽታዎችን በዱዓ (በጸለት) እና በተህሊል (በቅዱስ ውሃ) መፈወሳቸው፣ የአረሶ አደሩን ሰብል ከድርቅ እና ከበረዶ በዱዓ በመጠበቅ በህብረተሰቡ (በሙስሊሙና በክርስቲያኑ) ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታንንና ውዴታን አግኝተዋል፡፡

በመውሊዳቸውም ሆነ በዱኣ ወቅትም እሳቸውን ለመዘየር የሚመጡ ሰወች "ወንድሞችና እህቶች የሆናችሁ ሁሉ ለዲኑ ሊላሂ ልንመካከር ስትመጡ ለጀባታ ምን ይገፄ ልሒድ በማለት ያሰባችሁ እንደሆነ አፉ አላልኩም፤ ነገ የቂያም ቀን እጠይቃችኋለሁ፤ እኔ የምፈልገው ግን ወንድሞቼ መጣችሁ እኔን በማየት ሼቀዋየን ልትጠርጉልኝ ልታነሱልኝ እኔም የእናንተን ፊት እያየሁ ዱኣ ለማድረግ እንጂ ለጥቅምና ለገንዘብ የተቀመጥኩ እንዳልመስላችሁ" በማለት ይናገሩ እንደነበርና የሚያመጡላቸውን ጀባታዎችንም (ስጦታዎች) ቢሆን አቅም ለሌላቸው ያከፋፍሉ እንደነበር በአቶ ሙሀመድ አሊ እየተዘጋጀ በሚገኘው የሼህ ሁሴን አለሙን የህይወት ታሪክ የሚዳስስ መጽሐፍ ረቂቅ ላይ ጽሁፉ ላይ ለማስተዋል ችያለሁ፡፡

### 3.5 የመውሊድ ክብረ በአል ምንነትና አይነት

መውሊድን በሚያከብሩ የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ሁለት አይነት የመውሊድ[11] ክብረ በአላት አሉ፡፡ እነዚህም ክብረ በአላት ረቢል አወል (የነቢዩ መሐመድ የልደት በዓልን መሰረት

[11] መውሊድ የአረበኛ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም ልደት እንደማለት ነው፡፡

በማድረግ የሚከበር) እና የኡለማ መውሊድ (በህይወት በነበሩበት ወቅት በእምነቱ ታላቅ አሊም (አዋቂ) የነበሩትን ታላላቅ ግለሰቦች ለማሰብ የሚከበር መውሊድ) በመባል ይከፈላሉ፡፡

የ(ረቢል አወል) መውሊድ ክብረ በዓል የነብዩ መሐመድ የልደት በዓልን መሰረት በማድረግ በየአመቱ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በየመስጊዱ በመሰባሰብ የነብዩ መሐመድ ታሪካቸውና ውዳሴአቸው እየተነበበ በአማኙ ህብረተሰብ ዘንድ በቋሚነት የሚከበር በዓል ነው፡፡ ይህ በዓል ሲከበር እንደ ማህበረሰቡ ልምድና ባህል፤ የአከባበሩ ስርአት፣ ውዳሴውና የሚቀርብበት መንገድ ይለያያል፡፡ ይህም ሲባል የህብረተሰቡ የአኗኗር ሁኔታና የዘመኑ መንፈስ ሲቀየር፡ የክብረ በዓሉ ይዘትና ቅርጽ በተወሰነ መልኩ ይቀየራል ማለት ነው፡፡

የመውሊድ ክብረ በዓልና ታሪካዊ መነሻን የክብረ በዓሉን ሂደት በማስመልከት፡ ሐጅ ሐሩን ሙሳ (የታላቁ አኑዋር መስጊድ ኢማም) ጋር ባደረኩት ቃለ መጠይቅ፡ የመውሊድ ክብረ በዓል ምንድን ነው? ታሪካዊ መነሻውስ ምን ይመስላል? ብዬ ለጠየኳቸው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ቃል በቃል ሰጥውኛል፡፡

> "የኋላ ታሪክ የሌለው ነገር ሁሉ መሰረት የለውም፡፡ ነብዩ ሙሀመድ ተወልደው በ40ኛው ዓመት ሲሞላቸው የአላህን ትእዛዝ በመቀበል የእስልምናን ሀይማኖት የመሩ የመጨረሻ ነብይ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በእስልምና ዙሪያ ያሉትን ድንጋጌዎች ሁሉ ለሙስሊሙ ህብረተሰብ ያስተዋወቁት እሳቸው ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ለሳቸው ክብርና ዝና ለማስተዋወቅ/ ለማሳወቅ በእምነቱ የተለያዩ አጋጣሚዎች ተቀምጠዋል፡፡ ከነዚህም መካከል ዋናውና የመጀመሪያው አንድ ሰው በአላህ አንድነትና በነብዩ መልዕክተኛነት ካላመነ ሙስሊም አይባልም፡፡ ለዚህም መሰረቱ ሁልጊዜ አላህን ባወሳን ቁጥር እንድናወሳቸው/ እንድናስታውሳቸው ታዟል፡፡ ምሳሌ፡-_አዛን ሲወጣ (ሲባል) ስማቸው ይጠራል፣ በቀን 5ቱ ሰላት ላይ ስማቸው ይነሳል፡፡ በአጠቃላይ የሙስሊሙ እንቅስቃሴ ሁሉ አስፈላጊውን ድንጋጌ ያስቀመጡ በመሆናቸው ስራው ራሱ የግድ እንድናስታውሳቸው ያደርጋል፡፡
>
> በሌላ መልኩ ደግሞ እንደማንኛውም ታዋቂ ሰዎች በሙስሊሞች ዘንድ በአመት ልዩ ቀን ተደርጎ እንድናስታውሳቸው ተቀምጧል፡፡ በተለይ የተወለዱበትን ዕለት በማክበር፡፡ ይኸም የሚጠቅመው በይበልጥ ልክ በሳይንስም፣ በፖለቲካም፣ የሀገርን ጉዳይ፣ የነፃነት ቀን ተብሎ እንደሚሰየም ሁሉ በሀይማኖት በኩልም መሪያችን በመሆናቸው አርአያቸውን ለመከተል እንድንችል የተወለዱበትን ቀን በማክበር ሙስሊሙ ህብረተሰብ ዝናቸውን እንዲያስታውስና እንዲከተላቸው ጎላ ባለ ሁኔታ በመውሊድ መልክ ይከበራል፡፡ በተለይ ከሰላማዊ ትምህርት ርቆ የሚገኙ ሰዎች (በንግድና በምርምር) በእንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ካልሆነ በስተቀር ስለሳቸው ብዙም ግንዛቤ ስለማያገኝ ዕለቱን በነብዩ ዙሪያ ላይ በማተኮር አስፈላጊውን ትምህርት እሚሰጥበት አጋጣሚ ነው፡፡ ... በማለት ይገልጻሉ፡፡"
> **(ሐጅ ሐሩን ሙሳ (የታላቁ አኑዋር መስጊድ ኢማም) በባዕሉ ማክበሪያ ቦታ በዕለቱ የተደረገ ቃለ መጠይቅ)**

ስለዚህ የነቢዩ ሙሀመድ የመውሊድ ክብረ በዓል የነቢዩ መሐመድ የልደት በዓልን መሰረት በማድረግ በየዓመቱ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በየመስጊዱ በመሰባሰብ በአማኙ

ህብረተሰብ ዘንድ ታሪካቸውና ውዳሴአቸው እየተነበበ በማነቃቃት የእምነቱን መሰረታዊ መሰረቶች እንዳይረሳ ለማድረግ በቋሚነት የሚከበር በዓል ነው፡፡

ሁለተኛውና የዚህ ጥናት የትኩረት ጉዳይ ደግሞ የኡለማ መዉሊድ ነው፡፡ የኡለማ መውሊድ የሚከበረው በአንድ አካባቢ ነው፡፡ የሚከበርበትም ምክንያት በህይወት በነበሩበት ወቅት በእምነቱ ታላላቅ ኡለማ (አዋቂ) የነበሩትንና ታላላቅ ስራዎችን ለዕምነቱ ያከናወኑትን ግለሰቦች ለማሰብ ነው፡፡

አቶ ኡስማን ሰይዱ የዳንግላ የሐጅ ሁሴን (የነሼህ ዳንግላ የመውሊድ በዓል አስተባባሪ) እንደገለጹልኝ "የኡለማ መውሊድ ማለት በእስልምና እምነት ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ስማቸው ከፍ ብሎ ለሚጠሩ ሰዎች የሚከበር ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የሰሯቸው መልካም ስራዎች ለአማኙ በምሳሌነት የሚጠቀስ፣ የነብዩ ሙሐመድን አርአያነት የተከተሉ፣ እውቀታቸው የተመሰከረላቸው፣ በልዩ ልዩ ገድል የሚታወቁ ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡" በማለት ነግረውኛል፡፡

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍም በዳንግላ ከተማ የሐጅ ሁሴን ዓለሙ (የሼህ ዳንግላ) የመውሊድ በዓልን መሰረት በማድረግ የሚከበረውን የመውሊድ በዓል (የኡለማ መውሊድ) የአከባበር ስርዓት፣ ክዋኔውን እንዲሁም ማህበራዊ ፋይዳው በመዳሰስ ቀርቧል፡፡

### 3.6 የሼህ ሁሴን አለሙ (የነሼህ ዳንግላ) መውሊድ ታሪካዊ አጀማመር

የነሼህ ዳንግላ መውሊድ መከበር የተጀመረው በ1964 ዓ/ም ሲሆን ይህን በዓል ለማክበርም ሀሳብ ያቀረቡት የቅርብ ወዳጆቻቸው ናቸው፡፡ ይህ ጉዳይ በተመለከተ የቅርብ ዘመድ ከሆኑት ሐጅ ሙሀመድ ሐሰን (የሱፍ) ጋር በቀን 12/05/2005 ዓ.ም ባደረኩት ቃለ መጠይቅ የሚከተለውን ነገሩኝ፡-

> …በወቅቱ ሼህ ሠጠኝ ኸድር የተባሉ ግለሰብ "ለምን ሼሆቻችን የራሳቸው መውሊድ አይኖራቸውም?" የሚል ሀሳብ አቅርበው ሀሳባቸው በሌሎች እና በሼሆቹ ዘንድ ተቀባይነትን ሲያገኝ ወዲያውኑ አስር ብር በጀባታ (በስጦታ) መልክ ሲሰጡ ሌሎችም እንደፍላጎታቸው በማዋጣት አንድ ላም ገዙ፡፡… በዚህ መዋጮ የተገዛው ከብት ሼሆቹ "ወገኔን ሁሉ ጥሩ" ስላሉ ከባህር ዳር፣ ከዳንግላ፣ ከመሸንቲ፣ ከዱርቤቴ፣ ከመራዊ፣ ከፒኮሎ (ወተት አባይ) … የመጡ እንግዶችን ሁሉ አስተናግዶ ስጋው ሳያልቅ ቀረ፤ ተመልከት እንግዲህ በረካው፣ እንግዲህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ካመት አመት እየተከበረ ይገኛል፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ የሰውና የሚታረደው ከብት ቁጥር እየጨመረ መጣ፡፡

በዚህ ሀሳብ መነሻነት የሼህ ሁሴን አለሙ የመወሊድ ክብረ በአል መሰረታዊ መነሻ የነበረው የቅርብ ወዳጆቻቸው ፍላጎት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም ጊዜ የሚከበርበትን ጊዜ ወስነው መስያየታቸውን ከአጠቃላይ ቃለ ምልልስ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

በፎክሎር መስክ የሚደረጉ ምርምርና ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ከሆነ ደግሞ የእያንዳንዱ ክብረ በአል የሚከበርበት ዕለት የሚወሰነው ለከበራው የሚያመች ወቅት መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ በዚህ ጥናት ወቅት ከሰበሰብኩት መረጃ ለመረዳት እንደቻልኩት ከሆነ ደግሞ የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ ክብረ በአል አሁን ላይ (የካቲት 10) እንዲከበር የተወሰነበት የራሱ የሆነ ምክንያት አለው፡፡ ይህ ምክንያትም መውሊዱ ከመሰረቱ ሲጀመር (በ1964 ዓ/ም) ረቢል አወል (የነብዩ ሙሀመድ የልደት ቀን) በተከበረ ከ10 ቀን በኋላ እንዲከበር ተስማምተው ነበር፡፡ ነገር ግን የተወሰነ ጊዜ በዚህ ስምምነት ከተከበረ በኋላ የረቢል አወል መውሊድ የጨረቃን ኡደት (የሒጅራን ቀን አቆጣጠር) ተከትሎ ስለሚከበር በየአመቱ ቋሚ የሆነ ቀን ባለመኖሩ ለዝግጅት አይመችም የሚል ሀሳብ ቀረበ፡፡

በዚህ ሀሳብ መነሻነት ለመውሊዱ ዝግጅት የሚያመቸውና የከብት አቅርቦት በስፋት የሚገኘው ለገና (ታህሳስ 29) ስለሆነ ጥር 1 ቀን ቢከበር የተሻለ ነው የሚል መስማማት ተደረሰና ለተወሰኑ አመታት ጥር 1 ቀን መከበር ጀመረ፡፡ ነገር ግን ይህ ቀንም ቢሆን ለከብት አቅርቦት ቢመችም የምግብ እህል እንደልብ ስለማይገኝ፣ ምርቱ ጠቅሎ በሚገባበት የካቲት ቢከበር ሁሉን ነገር እንደልብ ማግኘት ይቻላል በሚል መስማማት የካቲት 10 መከበር ጀመረ፡፡

## 4. የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በአል ስርአተና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ

በዚህ ምእራፍ ስር የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በአል ስርአተ ክዋኔና ቃላዊ ግጥሞች ገጽታን ለስርአተ ክዋኔው ዝግጅት ከሚከውኗቸው ድርጊቶች ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ ያለው ሂደት በስፋት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ክዋኔውን አጅበው የመጡትን ቃላዊ ግጥሞች ለክዋኔው ሙሉነት ያላቸው ፋይዳ ተዳሷል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ከመውሊድ ባህሉ እና ስርአቱ ጋር የሚገናኙ ነጥቦችን ከመቃኘት ባሻገር በክዋኔው ወቅት የመጡ ትእምርታዊ ጉዳዮች ተተርጉመዋል/ ተፈክረዋል፡፡

### 4.1 የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በአል ስርአተ ክዋኔ

የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በአል ስርአተ ክዋኔ ራሱን የቻለ ሒደት ያለውና በሁነቶች (events) የተሞላ ነው፡፡ ሁነቶቹ ክዋኔው ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የየራሳቸው ዓላማ ያላቸውና አንዱ ሁነት ለሌላው መነሻ የሆኑ የተለያዩ ክንዋኔዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ ክፍልም የበዓሉን ስርዓተ ክዋኔ የሚያካትታቸውን ሁነቶች ከፋፍሎ በማስቀመጥ እንደሚከተለው ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

#### *4.1.1 የሥርዓተ ክዋኔው ቅድመ ዝግጅት*

ክብረ በዓል ላይ ትኩረት ያደረጉ የፎክሎር ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ማንኛውም ክብረ በዓል ሒደቱን የሚጀምረው ከክብረ በዓሉ በፊት በሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓል ስርአተ ክዋኔም በዋዜማው በሚደረጉ ልዩ ልዩ ቅድመ ዝግጅቶች ይጀምራል፡፡ ይህ የስርአተ ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት ደግሞ መውሊዱ ሥርአቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን የሚያስችሉ ስራዎች የሚከናወኑበት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ለምግብ ማብሰያ የሚያገለግል የማገዶ እንጨት ዝግጅት፣ የአካባቢ ጽዳት፣ የምግብ ዝግጅት (ጤፍ የማበጠር፣ ቅመማቅመሞችን የማዘጋጀትና ማስፈጨት)፣ የዳስ (ድንኳን) ስራ እና የቁሳ ቁስ አቅርቦት የሚያካትት ነው፡፡

ይህንኑ ቅድመ ዝግጅት በተመለከተም የክብረ በአሉ የረጅም ጊዜ ተሳታፊ የሆኑት ሼህ ሙሐመድ አብዱላሒ ባደረኩላቸው ቃለ መጠይቅ[12] እንደገለጹልኝና እኔም በቦታው ላይ በነበረኝ አስተውሎት እንዳረጋገጥኩት፣ የሥርዓተ ክዋኔው ቅድመ ዝግጅት የሚጀምረው

[12] በ08/06/2005 ዓ.ም የተደረገ ቃለ መጠይቅ፡፡ በትንተናው ከዚህ በኋላ ቃለመጠይቅን ቃ.ለ እያልኩ እጠቀማለሁ፡፡

ዋናው በዓል ከመድረሱ ከሁለት ወራት በፊት ነው፡፡ በዚህ ጊዜም የሚኖረው የስራ ድርሻ እንደ እድሜ ደረጃና ጾታ የተለያየ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ በቀላሉና በተቀላጠፈ መልኩ ቅድመ ዝግጅቱ እንዲቋጭ በመታሰቡ እንደሆነ ከሼህ ሙሐመድ ጋር ባደረኩት ቃለ ምልልስ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ይህንንም ቅድመ ዝግጅት የወንዶች፣ የሴቶች እና የታዳጊዎች ሚና (በሁለቱም ጾታ) ብሎ በመከፋፈል እንደሚከተለው መመልከት እንችላለን፡፡

***ሀ. በቅድመ ዝግጅቱ የወንዶች ሚና፡-*** በዚህ ቅድመ ዝግጅት ወንዶች ያሏቸው የስራ ድርሻዎች ብዙ ጉልበትን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በሚናቸው ቀዳሚ የሆነው ደግሞ ለምግብ ማብሰያ የሚያገለግል የማገዶ እንጨት መግዛት፣ ወደ ከበራው ቦታ ማጓጓዝ እና ለማገዶ በሚያመች መልኩ ማዘጋጀት እንደሆነ ወጣት ሙሀመድ በድሩ ጋር በቀን 07/05/2005 ዓ.ም ባደረኩት ቃለ ምልልስ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ይህ የወንዶች ስራ ለዳስ ተከላ በግብአትነት የሚያገለግሉ ቋሚና ወራጅ እንጨቶችንም ማዘጋጀት ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ ስራዎች የሚፈጸሙት ደግሞ ክብረ በአሉ ከመድረሱ ከሁለት ወር በፊት ይጀመሩና አንድ ወር እስኪቀረው ድረስ ሙሉ ለሙሉ ይጠናቀቃል፡፡

እነዚህን ስራዎች በዋናነት የሚያስተባብረው የመውሊዱ አዘጋጅ ኮሚቴ ሲሆን ስራውን ሚሰራው የአካባቢው ህብረተሰብ በራሱ ፍላጎት መሆኑን ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ይህንን የሚያደርጉት ደግሞ የሼሆቹን በረካ ለማግኘት መሆኑን በቃለ ምልልስ ወቅት ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ከዚህ ላይ በመስኩ የተጠኑ ቀደም ያሉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ የኡለማ መውሊድ ሲከበር ምእመኑ የሚፈጽማቸውም ሆነ የሚሰራቸው ድርጊቶች መውሊዱ የሚከበርላቸውን ኡለማ በረካ ለማግኘትና የእሳቸውን ስራ እውቅና ለመስጠት መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡[13] በዚህ ጥናትም በተመሳሳይ መልኩ በዚህ ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት ተሳታፊ የነበሩት ግለሰቦች ይህንንኑ ጉዳይ አረጋግጠውታል፡፡

***ለ. በቅድመ ዝግጅቱ የሴቶች ሚና፡-*** በሼህ አለሙ የመውሊድ ስርአተ ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት በሴቶች የሚከናወን መሰረታዊ ነገር የምግብ ዝግጅት ነው፡፡ የዚህም ዝግጅት የሚጀመረው እንደ ማገዶ እንጨቱ ዝግጅት ሁሉ ቀደም ብሎ ነው፡፡ የአካባቢው ተወላጅና የክብረ በአሉ

---

[13] ፅጌ ንጋቱ አስጨናቂ (1982) "የሼህ ሰይድ ቡሽራ ታምራት አፈታሪክና የመውሊድ በዓል አከባበር በገታ/ወሎ"፣ኪሩቤል ሽንቁጤ (1986) "የቃጥባሬው ሼህ ህይወት ታሪክና የበዓላቸው አከባበር"፣ መሐመድ ሁሴን (1997) "የገበሮች ሼህ የህይወት ታሪክና የበዓላቸው አከባበር"፣ የሚሉ ጥናቶች የተነሳውን ሀሳብ የደገፉ ጥናቶች ናቸው፡፡

የረጅም ጊዜ ተሳታፊ የሆኑት ወይዘሮ አሚነት ሙሳ[14] እንደገለጹልኝ፤ የምግብ መሰናዶ የሚጀመረው ለወጥ ፍጆታና ለእንጀራ ዝግጅት የሚውሉ የተለያዩ ቅመማ ቅመሞችን በማዘጋጀት ነው።

በዚህም መሰረት በሴቶች በኩል በርበሬ የመልቀምና የማስፈጨት፣ ጤፍ የማበጠርና የማስፈጨት እንዲሁም የተለያዩ ማጣፋጫዎችን የማዘጋጀት ስራ ይከናወናል። በዚህ ጊዜም የሴቶቹ የቅድመ ዝግጅት ስራ የሚከናወነው እንደ ወንዶቹ ሁሉ በፈቃደኝነት ሲሆን ሴቶቹም አስበው እንደሚፈጽሙ ከአቶ ኡስማን ሰኢዱ (የመውሊዱ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊቀ መንበር) ጋር በእለቱ በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ችያለሁ።

***ሐ. በቅድመ ዝግጅቱ የታዳጊዎች ሚና፡-*** በቅድመ ዝግጅቱ የታዳጊዎች ሚና (እድሜያቸው ከ15 እስከ 20 የሆኑ ወንድና ሴቶችን ያጠቃልላል።) ለክብረ በአሉ የሁለት ሳምንት ጊዜ ሲቀር የበአሉ መከበሪያ ቦታ የሆነው የዳንግላው ሼህ ሁሴን አለሙ መስጊድ አጥር ግቢውንና አካባቢውን የማጽዳት ስራ ይፈጽማሉ። ይህ አካባቢውን የማጽዳት ስራ የሚፈጸመው በአብዛኛው በሴቶች ሲሆን የተመነጠረውን ቆሻሻ የማስወገድ ስራ ደግሞ በወንዶች የሚፈጸም ነው። ይህ የሚደረገው ደግሞ ከተለያዩ አካባቢ የሚመጡ እንግዶች ጤና እንዳይታወክና ስርአቱን በሚገባ ፈጽመው እንዲሔዱ ለማድረግ መሆኑን በቃለ መጠይቅ ያገኘሁት መረጃ ያመለክታል።

### *4.1.2 የሥርዓተ ክዋኔው ዋዜማ*

የስርአተ ክዋኔው ዋዜማ የካቲት 08 2005 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን ዋናው የመውሊድ ከበራ ከመጀመሩ በፊት የሚፈጸሙ ልዩ ልዩ ክንዋኔዎችን አካቶ የያዘ ነው። በዚህ ጥናት እነዚህ ክንዋኔዎች ለአቀራረብ እንዲያመች ሲባል ***የዳስ ተከላ*** እና ***የምግብ ዝግጅት*** በሚሉ ሁለት ዋና ዋና ሁነቶች ተከፋፍለው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

---

[14] በ08/06/2005 ዓ.ም በባኣሉ ማክበሪያ ቦታ ላይ የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ እኚህ ግለሰብ ይህን የመውሊዱን በዓል ላለፉት 30 አመታት የተሳተፉ ናቸው።

### ሀ. የዳስ ተከላ

በክብረ በዓሉ ቅድመ ዝግጅት፣ ከላይ የተጠቀሱትን ክንውኖች መጠናቀቅ ተከትሎ የዳስ ተከላና ለእንግዳ ማረፊያ የሚሆኑ ቦታዎች የማመቻቸት እንዲሁም ምግብ የማዘጋጀት ስራ ይከናወናል፡፡ የቦታ ዝግጅቱ በበአሉ ማክበሪያ ቦታ በሶስት አቅጣጫ የተመቻቸ ሲሆን ከትልቁ አዳራሽ በስተግራ በኩል ለሴቶችና በፊት ለፊት ለወንዶች የሚሆኑ ሁለት ትላልቅ ዳሶች ተጥለዋል፡፡ ከዋናው የቅጥር ግቢው መግቢያ ትይዩ ደግሞ ከሩቅ አካባቢ የሚመጡ እንግዶች የሚያርፉበትና ለክርስትና እምነት ተከታዮች የሚመገቡበት ሁለት የተቀጣጠሉ ድንኳኖች ተጥለዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ለምግብ ዝግጅት የሚያገለግሉ ሶስት በመጠናቸው ትንንሽ የሆኑ ዳሶችም ከመስጊዱ በስተጀርባ ተዘርግተዋል፡፡ ይህንን ስራ የሚፈጽሙት በአብዛኛው ወንዶች ናቸው፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ደግሞ የዳሱ ተከላ ከጉልበት ስራ ጋር ስለሚገናኝ እና ዳሱ በሚሰራበት ተመሳሳይ ወቅት ሴቶች የእንጀራ ጋገራ ስርአት ስለሚያከናውኑ ነው፡፡

በጥናቱ በምልከታ ወቅት እንደተስተዋለው በዚህ ሁነት በርከት ያሉ የአካባቢው ሰዎች (የክርስትና እምነት ተከታዮችም ጭምር) በመተባበርና በመተጋገዝ የዳስ ተከላ ሒደቱን ይፈጽማሉ፡፡ በመሆኑም የጥናቱ አቅራቢ የአካባቢው ማህበረሰብ የአኗኗር ባሕል ማህበራዊ ግንኙነቱን በማጠናከሩ የተነሳ የሀይማኖታዊ ከበራውን የሚያሳኩ ስራዎችን በጋራ ለመፈጸም ችለዋል የሚል ግላዊ እምነት አለው፡፡ ይህ ክንውን እየተፈጸመ ጎን ለጎን የእንጀራ ጋገራና የስጋ እርድ ይፈጸማል፡፡

### ለ. የምግብ ዝግጅት

እንጀራ ጋገራ ከዋናው ክብረ በአል አንድ ቀን ቀደም ብሎ የካቲት 08 የሚከናወን ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ የእርድ ስነ ስርዓቱም ጎን ለጎን ይካሔዳል፡፡ በዚህ የምግብ ዝግጅት ሒደት እንጀራ መጋገር፣ ሽንኩርት መክተፍ እና ለመጠጥ የሚሆን ውሀና ቡቅር[15] ማዘጋጀት የሴቶች ሚና ሲሆን ለእርድ የተዘጋጁ በሬና ግመሎችን ማረድና መቆራረጥ፣ መክተፍና ወጥ መስራት የወንዶች ሚና መሆኑን ለማስተዋል ችያለሁ፡፡ በሁሉም ጾታዎች ሚናቸውን በሚገባ

[15] ቡቅር ከገብስ የሚዘጋጅ ከአልኮል ነጻ የሆነ መጠጥ ነው፡፡ የአዘገጃጀት ሒደቱ እንደ ጠላ በተመሳሳይ መልኩ ከብቅል የሚዘጋጅ ቢሆንም የሚለየው ግን ጌሾ አይገባበትም፡፡ እንዳስፈላጊነቱ ለማጣፈጥ ሲባል ስኳር ሊጨመርበት ይችላል፡፡ በዚህ ክብረ በአልም ይህ መጠጥ በስፋት ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

እንደሚዎጡ ተረድቻለሁ፡፡[16] እዚህ ላይ በዋዜማው በነበረኝ ምልከታ ከላይ የጠቀስኳቸውን ክንውኖች ከእስልምና እምነት ተከታዮች በተጨማሪ ክርስትና እምነት ተከታዮች በጋራ ይከውናሉ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ማህበረሰቡ ባለው የጋራ ኑሮ አንዱ የአንዱን በአል የማክበር ልምድ በማህበራዊ ኑሮ የተገነባ በመሆኑ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ በዋዜማው የእንጀራ ጋገራ ላይ የተሰማራችው በለጠች ሙጨ በእለቱ በተደረገላት ቃለ መጠይቅ የሚከተለውን ብላለች፡-

> በሼሆቹ መውሊድ አመት ካመት እንጀራ እንጋግራለን፣ በጤፍ ማበጠሩም ቢሆን እንሳተፋለን… በቃ አብረን እየኖርነ እንተጋገዛለን… እነሱም በኛ ድግስም ሆነ በአል ላይ ይሳተፋሉ፡፡… ያው ከዝግጅቱ እስከፍጻሜው እንሰራለን፣ ለኛ የሚዘጋጀውን ምግብ እንበላለን፣ የሚመጡት እንግዶችን በጋራ እናስተናግዳለን፡፡….

እዚህ ላይ ከበለጠች ሙጨ በተጨማሪ ሌሎች በእንጀራ ጋገራው ወቅት የሚሳተፉ የክርስትና እምነት ተከታዮችን ለማስተዋል ችያለሁ፡፡ ይህ ሁኔታ ከሴቶች በተጨማሪ በወንዶችም በኩል የዳስ ተከላው ላይ በስፋት ተስተውሏል፡፡[17] ከዚህ በመነሳትም የዚህ ጥናት አቅራቢ ይህ የመውሊድ ክብረ በዓል በአካባቢው ያለውን ማህበራዊ ትስስር መገለጫ ነው የሚል እምነት አለው፡፡

በተጨማሪም የዚህ ጥናት የትኩረት ነጥብ የክዋኔ ሒደቱን ፎክሎራዊ ገጽታ መመልከት ቢሆንም፤ የጥናቱ አቅራቢ በምልከታ ያስተዋለውን የመውሊዱን ማህበራዊ መስተጋብር ማንሳት ተገቢ ነው ብሎ ስለሚያምን፤ ለአቶ ኡስማን ሰኢዱ በ08/06/2005 ዓ.ም በዚህ መውሊድ የክርስቲያንና የሙስሊሙ መስተጋብር ምን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ፡፡ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

> ይህ እንግዲህ በዳንግላ ዙሪያ ላይ እስልምና ክርስትና ወይም ኦርቶዶክስ ምን ምን ተብሎ ልዩነት የለም፡፡ በድግስም፣ በመውሊድም፣ በሰርግም ያንድ እናት ያንድ አባት ልጅ ሆኖ ነው የሚኖረው ፣ አዎ በልቅሶም በሐዘንም በእድርም ማህበራዊ ኑሮው ይኸ ነው የሚባል ልዩነት የለም እስላም ክርስቲያን የሚባል ነገር የለም ያ ባለመኖሩ ነው ተቻችሎ የሚኖር ወንድም በመሆኑ፤ ሙስሊሙ ሀብረተሰብ ተደግሶለት እየበላ እየታየ ወንድሞቻችን ለምንድን ነው ታዛቢ የሚሆኑት? እራሳቸውም

---

[16] ከአቶ ኡስማን ሰኢዱ ጋር በ08/06/2005 ዓ.ም በበአሉ ማክበሪያ ቦታ ላይ የተደረገ ቃለ መጠይቅ፡፡ እነዚህን ሚናዎች በመወጣት ሒደት ለእያንዳንዱ የስራ ድርሻ የተመደቡ አስተባባሪዎች አሉ፡፡ አስተባባሪዎች ደግሞ በተመደቡበት የስራ ድርሻ ክፍተት እንዳይኀደል፣ ስራ ለማገዝ የሚመጣውን ምዕመን በማስተባበር ያሰራሉ፡፡ ከአቅማቸው በላይ የሆነ ችግር ሲገጥማቸው፣ ለመውሊዱ ዋና አስተባባሪ አቶ ኡስማን ሰኢዱ ያሳውቃሉ፣ በጋራም መፍትሔ ይፈልጋሉ፡፡

[17] በምልከታ ካስተዋልኩት በተጨማሪ ከአቶ ኡስማን ሰኢዱና ሼህ ጣሒር ሙሳ በ08/06/2005ዓ.ም ባካሔድኩት ቃለ መጠይቅ በአካባቢው የሚገኙት የክርስትና እምነት ተከታዮች በጉልበት ከሚያደርጉት ድጋፍ በተጨማሪ ለልዩ ልዩ ግልጋሎት የሚውሉ ቁሳቁሶችን ለምሳሌ፡- ለዳስ የሚሆን ሼራ፣ ድንኳኖች ፣ብረት ድስቶች ወዘተ. እንደሚያቀርቡ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

> የበዓሉ ተካፋይ ናቸው፡፡ በሚል ነው ይኸ ድግስ እምታዩት የሚስተናገዱት፡ እነሱ የመውሊዱንም ስርአት ያግዛሉ ከአዲስ አበባም ከሌላም የሚመጡ ክርስቲያን ወንድሞቻችን አሉ፡፡ እስላም ነው ክርስቲያን ነው የሚባል ነገር የለም፡፡ ለምሳሌ የክርስቲያኑን የሚያዘጋጁት ክርስቲያኖች ናቸው፡፡ እኛ የሚፈለገውን ነገር ሰጠናቸው እንጅ በጉልበት እራሳቸው ሰርተው ነው የሚያስተናግዱት፡፡ የዳንግላ ህዝብ ሙስሊም ክርስቲያኑ አንድ ነው፡፡ ልዩነት የለውም፡፡

በማለት ከበራው ከእስልምና እምነት በተጨማሪ ሌሎች የእምነት ተከታዮችን እንደሚያሳትፍ ነገሩኝ፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢም ለዚህ ጥናት ዝግጅት ከሚያደርግበት ጊዜ ጀምሮ በመረጃ ስብሰባ ወቅትም፣ ሼህ ሁሴን አለሙ በህይወት በነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ከክርስትና እምነት ተከታዮች ጋር ጠበቅ ያለ ግንኙነት እንደነበራቸው ለማወቅ ችሏል፡፡ (ይህንን የአጥኝውን ሀሳብ ለማስተንተን በምዕራፍ ሶስት የተገለጸውን የህይወት ታሪካቸውን መመልከት ልብ ይሏል፡፡)



ምስል፡- የከበራው ቅድመ ዝግጅት ላይ የእንጀራ ጋገራ ሲካሔድ፤

ከላይ የምትመለከተቱት ምስል በከራው ዋዜማ የእንጀራ ጋገራ እየተካሔደ ሲሆን በምስሉ ፊት ለፊት የምትመለከቷቸው ሁለት ሴቶች የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡



ምስል ፡- የከበራው ቅድመ ዝግጅት ላይ የእርድ ስነ ስርአት ሲካሔድ፤

ከላይ የቀረቡት ሁለት ፎቶዎች በተመሳሳይ ቀን ሐሙስ እለት በ08/06/2005 የተወሰዱ ናቸው፡፡

ካትሪን ቤል (1997) ላይ በፎክሎር ጥናት መስክ ሰፋ ያለ ቦታ ያለውን ክብረ በዓል በተመለከተ በጻፈችው መጽሐፍ ላይ፤ አብዛኞቹ ክብረ በዓላት አንድ የሚያደርጋቸው መሰረታዊ ጉዳይ ድግስ መሆኑን ትገልጻለች፡፡ ይህም ክብረ በዓል በተመሳሳይ መልኩ ድግስን ዋነኛ መሰረት አድርጎ የሚከወንና ምግቡና መጠጡ ከሌለ ክዋኔው ሙሉ እንደማይሆን ለማስተዋል ችያለሁ፡፡ ይህም ለምን እንደሆነ ስጠይቅ አቶ ኡስማን ሰኢዱን የሚከተለውን ምላሽ ሰጠኝ፡-

> ይህ መውሊድ የሚከበረው በአካባቢው ለእስልምና ታላቅ ስራ ሰርተው ያለፉትን ሼህ ሁሴን አለሙን ለማሰብ እና ለመዘከር ነው፡፡ ይህ በዓል ሲከበር ግን ኡመቱ[18] መዘያየሩና ዳዕዋ ማድረጉ ጎን ለጎን እስኪጠግቡ በመብላት ይከበራል፡፡ ይህም ማለት ምዕመኑን እስኪጠግብ ማብላት የመውሊዱ አንዱ አላማ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ዓመቱን ሙሉ በቤታቸው ምግብ እንደፈለጉ የማያገኙትን፣ የቲም[19] ልጆችንና ስጋ በልተው የማያውቁትን እስኪጠግቡ እንዲበሉ ለማድረግ ነው፡፡ (ቃለ.08/06/2005)

ይህም ማለት መውሊዱ ሲታሰብ ከክዋኔ ሒደቱ ጋር አብሮ የሚታሰበው መሰረታዊ ነገር ድግሱ ነው፡፡ በጉዳዩ ላይ በተለያዩ አካባቢዎች ቀደም የተጠኑ ጥናቶች ማለትም ፅጌ ንጋቱ

[18] ኡመት ማለት ተከታይ ማለት ሲሆን (የእምነቱ ተከታዮችን ለመግለጽ ይጠቀሙበታል)፡፡

[19] የቲም ማለት ወላጆቻቸውን በሞት የተነጠቁ ልጆች ማለት ነው፡፡

አስጨናቂ (1982)፣ ኪሩቤል ሽንቁጤ (1986)፣ መሐመድ ሁሴን (1997)፣ አሸናፊ ምስጉን (1998) መውሊድና ምግብ ተነጣጥለው የማይታዩ ጉዳዮች መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡[20] እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚያስፈልገው መሰረታዊ ጉዳይ የኡለማ መውሊድ ቀዳሚው ተግባሩ ኡለማውን ማሰብ (መዘከር) ሲሆን በዚህ መዘከር ሒደት ውስጥ ድግስ አይቀሬ ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም በሼህ ሁሴን አለሙ መውሊድ ክብረ በዓል ላይ ለመታደም የመጡትን ከ 30-40 ሺ ምዕመን ለማስተናገድ 21 በሬዎችና 5 ግመሎች ታርደዋል፡፡ እነዚህ ከብቶች የተገኙት በጀባታ[21] ነው፡፡ ይህ ጀባታ የተገኘው ደግሞ በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው በቀጥታ ከብቶቹን በመጀባት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ገንዘብ በመስጠት ነው፡፡[22] በዚህ መልክ የሚገኘው ገቢ ከማን ምን ያህል እንደተሰበሰበና ማን ምን ያህል እንደጀባ አይታወቅም፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ደግሞ ምእመኑ የሚጀባው ካለው ስለተረፈው ምስኪኖች እንዲበሉ በማለትና ከአላህ አጅር አገኛለሁ ብሎ በማሰብ ነው፡፡[23] ይህን በማድረጉም ምዕመኑ ልቡ ፌሽታን ያገኛል፣ ለፈጣሪው ምስጋና ያቀርባል፣ ለቀጣዩ ስኬት ይለምናል፡፡ እንዚን ሁነቶች ደግሞ ከዋዜማው ቀጥለው በሚመጡት በመውሊዱ ዋና የከበራ ሒደት ይፈጽማል፡፡

### 4.1.3 የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓል አከባበር ስርዓት

በፎክሎር ጥናት መስክ ቀደም የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ ክብረ በዓል ራሱን የቻለ ተደጋግመው የሚመጡ ስርዓቶች አሉት፡፡ ይህ ስርዓትም የራሱን ማዕቀፍ መሰረት አድርጎ የሚከወንና መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚጨርስ የሚታወቅ ነው፡፡[24] በዚህ ንኡስ

---

[20] እነዚህ ጥናቶች በተጠቀሱባቸው አመታት በተለያዩ አካባቢዎች የኡለማ መውሊድን መሰረት በማድረግ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የተጠኑ ሲሆኑ ያነሷቸውን ጉዳዮችና የደረሱባቸውን መደምደሚያዎች በተመለከተ በምዕራፍ ሁለት መመልከት ይቻላል፡፡

[21] ጀባታ ማለት ስጦታ ማለት ነው፡፡ ይህ ስርአት ለቀጣዩ መውሊድ መሰረት የሚጥልና ባለፈው በተገባው ቃል መሰረት አሁን ላይ የሚፈጸም ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ራሱን ችሎ ሊጠና እንደሚችል የግል እምነት አለኝ፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ተመራማሪዎች ለምን? እንዴት? ቃል ገብተው ባይፈጽሙስ? የአፈጻጸሙ ሒደት ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎች ተነስቶ ሊጠና ይችላል፡፡

[22] ከመውሊዱ አስተባባሪ ሼህ ኡስማን ሰኢዱ እንዱሁም ከበአሉ ተሳታፊ ሼህ ጣሒር ሙሳ በክብረ በአሉ ላይ በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ፡፡

[23] ጀባታን በተመለተ እንዴት ይሰጣል? ለአንድ ምዕመን ጀባታ መስጠቱ ምን ጥቅም ያስገኝለታል? በሚሉ ጉዳዮች ላይ የመውሊዱን ዋና አስተባባሪ አቶ ኡስማን ሰኢዱን ጨምሮ ሼህ አብዱልቃድር ፈድሉ፣ ሼህ ሲራጅ ጀማል፣ ሐጅ ሙሐመድ ከማል እና ሼህ ዳውድ ፋሪስ ጋር በ09/06/2005ዓ.ም ጠዋት በባዕሉ ማክበሪያ ቦታ በተደረገ የቡድን ውይይት የተገኘ መረጃ፡፡

[24] ይህንኑ ጉዳይ በማስመልከት Sims እና Stephens (2005፣95) ላይ (Myerhoff 1977, 200) በመጥቀስ የሚከተለውን ሀሳብ ያሰፍራሉ፡- "*Rituals are performances that are repeated, patterned, and frequently include ceremonial actions that incorporate symbols, action, repetition; and perhaps most significant to our being able to recognize rituals, they have a frame that indicates when the ritual begins and ends.*"

ክፍልም ይህን ሐሳብ መነሻ በማድረግ፤ የዳንግላው ሼህ ሁሴን አለሙን የመውሊድ በዓል አከባበር ስርዓት፣ በክዋኔው ድርጊትና ትዕምርቶች ላይ በመመስረት በሁነቶች ተከፋፍሎ ተተንትኖ ቀርቧል።

በዚህም መሰረት ከዋዜማው ቅድመ ዝግጅት ቀጥሎ በከበራው ላይ የተስተዋሉትን የክዋኔ ሁነቶች ዝየራ፣ ዱኣ (ምርቃት) እና መንዙማ በማለት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

#### 4.1.3.1 ዝየራ

በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓል ከበራ ዕለት በመጀመሪያ የሚከወነው ሁነት ዝየራ[25] በመባል ይጠራል። ይህ ሁነት የሚከወነው ከከበራው ማግስት ጀምሮ ቢሆንም በዋናነት ግን አርብ 08/06/2005 በርካታ የበአሉ ታዳሚዎች "ዝየራ" ሲያካሒዱ አስተውያለሁ። ይህ የሆነበትን ምክንያት ዋናው ከበራ ሌሊቱን ስለሚካሔድ አብዛኞቹ እንግዶች የሚገቡት በዕለቱ በመሆኑ ነው[26]። በዚህ ክብረ በዓል የዚህ ሁነት አላማ ደግሞ ተራርቀው የከረሙ ዘመዳማቾች ("ሙስሊም መንድማማቾች") እንዲገናኙ እና ሰላምታ እንዲለዋወጡ ማድረግ ነው።[27] በምልከታየም ወቅት ይህን ሁነት በሁለት መንገድ እንደሚፈጸም ለማስተዋል ችያለሁ። የመጀመሪያው ከሩቅ ስፍራ የመጡ እንግዶች ሼሆቹን የሚዘይሩበት ሲሆን ይህ ሲካሔድ ስርአት ባለው መልኩ የዝየራ ክፍል ተዘጋጅቶ በአስተናጋጁ (በሼህ አዘያሪ) አማካኝነት እንግዶቹ የሐጅ ሁሴን አለሙን ቤተሰቦች (ታላቅ ልጃቸውን ሐጅ ሲራጁዲን ሁሴን) የሚዘይሩበት ነው።

በዚህ ሒደት በነበረኝ አስተውሎት ምዕመናኑ ጫማቸውን አውልቀው ወደ ዝየራ ክፍል በመግባት "አሰላም አለይኩም የሼሆቹ ልጅ እንደምን አሉ?" ፣ "አፊያዎት ምን ይመስላል?" በማለት ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ የመጡበትን ጉዳይ ለሼሆቹ ልጅ ያቀርባሉ። ሐጅ ሲራጁዲን ሁሴንም ለሁለም ዘያሪዎች በተመሳሳይ መልኩ ሰላም መሆናቸውንና የናንተስ አፊያ፣ ቤተሰብ እንዲሁም አገር ሰላም መሆኑን ይጠይቃሉ። ከዚያም በኋላ እንደየመጡበት ጉዳይ መፍትሔ

---

[25] ዝየራ ማለት (ቃለ መጠይቅ 3) ባደረኩበት ወቅት ለመረዳት እንደቻልኩት፣ ሰላምታ መለዋወጥ፣ መገናኘት፣ መጨባበጥ የሚል ትርጓሜ አለው። በእስልምና እምነት ዝየራ በመውሊድ በዓልም ሆነ በሌሎች ክብረ በአላት ቀዳሚ ተግባርም ነው። ይህም የሚፈጸመው ከተለያዩ አካባቢ የሚመጡ ሰዎች ናፍቆታቸውን እንዲወጡና ፍቅራቸውን እንዲገላለጹ ለማድረግ ነው።

[26] የመውሊዱ አስተባባሪ ከሆኑት አቶ ኡስማን ሰኢዱ ጋር አርብ 08/06/2005 ጠዋት ላይ በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ።

[27] ከመውሊዱ አስተባባሪ ሼህ ኡስማን ሰኢዱ እንዱሁም ከበአሉ ተሳታፊ ሼህ ጣሒር ሙሳ በክብረ በአሉ ላይ በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ።

የሚሉትን ይጠቁማሉ፣ መድሐኒት ይሰጣሉ። እዚህ ላይ በዋናነት የሚሰጡት ተህሊል[28] ሲሆን አልፎ አልፎም ከእጽዋት ተቀምሞ የሚጨስ መድሀኒት እንደየጉዳያቸው አስፈላጊነት ያድላሉ።

ይህ ዝየራ ሐጅ ሁሴን አለሙ በህይወት በነበሩበት ወቅት መከናወን እንደተጀመረና ምእመኑ የሳቸውን ፊት በሚያይበት ወቅት ይፈወስ እንደነበር ከሐጅ ሙሀመድ ሐሰን ጋር በዕለቱ በተደረገ ቃለ ምልልስ ለመረዳት ችያለሁ። ከዚህ ላይ እሳቸው ካለፉ በኋላ ትልቁ ልጃቸው የሳቸውን ቦታ ተክቶ የዝየራውን ሁነት የሚያስፈጽምበትን ምክንያት ሐጅ ሙሀመድ ሐሰን ሲገልጹ፦

> ሼሆቹ ከሞቱ በኋላ ልጆቻቸው የሳቸውን በረካ (ጸጋ) ይወርሳሉ ተብሎ ስለሚታመን ለበዓሉ የሚመጣው ምዕመን ልጆቻቸውን ይዘይራሉ (ይገናኛሉ)። በዋናነት ግን የሚዘየሩት የቤተሰቡ ታላቅ ልጅ የሆኑትን ሐጅ ሐጅ ሲራጁዲን ሁሴንን ነው።…

ከዚህ ላይ ቀደም በተጠኑ ጥናቶች (ፅጌ ንጋቱ አስጨናቂ (1982) "የሼህ ሰይድ ቡሽራ ታምራት አፈታሪክና የመውሊድ በዓል አከባበር በገታ/ወሎ" እና ኪሩቤል ሽንቁጤ (1986) "የቃጥባሬው ሼህ ህይወት ታሪክና የበዓላቸው አከባበር") ላይ የተመለከትኩት የሼሆቹን **መቃብር የመዘየር[29] ሒደት (ዚያራ)** አይከወንም። ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ የነሼህ ዳንግላ መቃብር የሚገኘው መካ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሊሆን እንደሚችል የአጥኝው ግምት ነው። በጥናቱ ለመረዳት እንደተቻለውና የሼሆቹን ታሪክ በቅርብ የሚያውቋቸው ግለሰቦች (ሐጅ ሙሀመድ የሱፍ፣ ሐጅ ሙሐመድ ከማል እና አቶ ኡስማን ሰኢዱ) በቀን 08/06/2005 ዓ.ም የተደረገ ቃለ መጠይቅ እንደገለጹት፦

> እነሼህ ዳንግላ ላይ ቀብራቸው ቢሆን ህብረተሰቡ ቀብሬ ላይ ያልተገባ ድርጊት ወይም ሽርክ የሆነ ስራ በመስራት ከአላህ ትዕዛዝ ይወጡብኛል በሚል ስጋት ሞታቸውና ቀብራቸው ዳንግላ ላይ እንዳይሆን

[28] ተህሊል ማለት የመፈወስ አቅም አለው ተብሎ የሚታመን ውሀ ነው። ይህም ውሀ የሚቀዳው በምዕራፍ 3 በንኡስ ርዕስ 3.4 የነሼህ ዳንግላ (ሐጅ ሁሴን አለሙ) መስጅድ አመሰራረት በሚለው ክፍል የተብራራውን ውሀ መሆኑን ልብ ይሏል።

[29] በርግጥ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ከነዚህ ጥናቶች በተጨማሪ Terimingham (1952, 249) "Islam in Ethiopia" በሚለው መጽሀፉ "The practice involved *ziyar'a* to these shrines, although its own unique local usages, follows normal Islamic practice. Worship at the shrine takes two forms: visites in honour of the saint and visits to secure his aid. The word *ziyar'a* is especially attached to the annual pilgrimage, whose practices involve the procession round the tomb, visit inside, with the appropriate prayers, eulogies chanted in his honour (sometimes performance of *mulid* with a *dhikr* and recitation of Qur'an)," በማለት ገልጾታል።

> ይመኙ ነበር። ….በተለይም መካ ላይ ቢቀበሩ ይወዱ እንደነበር ይናገሩ ነበር። አላህም ይወዳቸው ስለነበር የተመኙትን ፈጸመላቸው፤ ቀብራቸውም ሳውዳረቢያ መካ ውስጥ ሆነ።

በማለት ጠቅለል ያለ መልስ ሰጥተውኛል። ከዚህ መረዳት የምንችለው ሼሆቹ በዝየራ ስም በቀብር ላይ የሚደረግን "ዚያራ" እንዲፈጸም አለመፈለጋቸውን ነው።

በዚህ ሒደት ሁለት ምላሾችን ከአጠቃላይ ምልከታየ ለማስተዋል ችያለሁ። የመጀመሪያው የአላህን ታላቅነትና በሱ ፈቃድ ሰላም መሆናቸውን የሚገልጹ መላሾች ሲሆኑ በሁለተኛው መልክ ደግሞ በሼሆቹ በረከት ሰላምና ጤና እንዳገኙ የሚገልጹ መሆናቸውን ነው። ከዚህም በመነሳት የሼሆቹ መልካም ስራና በረከት ለኛ ህይወት ሰላምና ጤና መሆን መሰረት አለው የሚሉ ምዕመናን መኖራቸውን ለማስተዋል ችያለሁ።




*ምስል 1፦ ወደ ዚያራ ክፍል ለመግባት የሚጠባበቁ ምዕመናን የሚያሳይ ምስል።*

ከላይ የሚታየው ምስል፡ በስተግራ በኩል መለያ ጋወን ያደረገው ሼህ አዘያሪው ሲሆን፣ በስተቀኝ በኩል የሚታዩት ወጣቶች ደግሞ ወደ ዝየራ ክፍል ለመግባት ተራ በመጠባበቅ ላይ የሚገኙ ወጣቶች ናቸው። በቃለ መጠይቅ ከወጣቶቹ ጋር በነበረኝ ቆይታም የሼህ ሁሴን አለሙ መልካም ስራና በረካ እነሱንም እንዲደርሳቸው እንደሚፈልጉ ተረድቻለሁ።

የዚያራ ሒደት የሚፈጸምበት በሁለተኛው መንገድ ደግሞ ዱኣው (በክብረ በዓሉ ከዚያራው ቀጥሎ የሚመጣው ሁነት) ከመጀመሩ በፊት ከሩቅ የመጡ ምእመናንና ዘመዳማቾች እርስ በእርስ የሚፈጽሙት ነው። ይህን ሒደት ሲከናወን ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታ የማይጠይቅና ዱኣው እስኪጀመር ድረስ የሚዘልቅ ነው። በክዋኔውም ምእመናኑ በተለይ ከተለያዩ ቦታወች ለሚመጡ ታላላቅ  ሼሆች ቅድሚያ እየሰጡ የሚዘያየሩበትና የሚተዋወቁበት ነው።

በዚህ ሒደት ምልከታዬ ላይ ለማስተዋል እንደቻልኩት፣ ከአካባቢው ሰዎች በተጨማሪ በክብረ በዓሉ ላይ ተሳታፊ የነበሩትና ከተለያዩ ቦታዎች (ከትግራይ፣ ከወሎ፣ ከአፋር፣ ከአዲስ አበባ፣ ከጎንደር፣ ከሶማሌ፣ ከኦሮሚያ እዲሁም ከሱዳን፣ ከሳውዲ አረቢያና አሜሪካ) የመጡ እንግዶች (በሁለቱም ጾታዎች ከህጻን እስከ አዛውንቶች) እርስ በእርስ ከመዘያየራቸው ባለፈ ከበዓሉ ተሳታፊዎች ጋር ረዘም ላለ ጊዜ ሰላምታ ሲለዋወጡ አስተውያለሁ። ይህም ሂደት በሐጅ ሙሀመድ የሱፍ፣ ከተገለጸልኝ የበአሉ ክንዋኔዎች ዋና አላማዎች መካከል አንዱ የሆነውን ምእመናኑን የማገናኘትና የማስተዋወቅ ሚና በተግባር ለማረጋገጥ ችያለሁ።

ይህ ሁነት አዲስ እንግዶች በገቡ ቁጥር በዚህ መልኩ እየተከናወነ እስከ ዳእዋው ጅማሬ ይዘልቃል። በእርግጥ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ “ዚያራ” እስከ በዓሉ ፍጻሜ ድረስ አዲስ እንግዶች በመጡ ቁጥር የሚቆይ ክንውን መሆኑን ነው። ነገር ግን አጠቃላይ ከክዋኔው ሒደት አንጻር ሥንመለከተው ቀዳሚው የሆነ ሁነት ነው ማለት ይቻላል።

#### 4.1.3.2 ዱኣ (ምርቃት)

በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓል ከበራ ዕለት ከዚያራ በመቀጠል የሚከወነው ሁነት ዱኣ[30] በመባል ይጠራል። ይህ ሁነት የክብረ በዓሉ (የመውሊዱ) ዋነኛው ክፍል ነው።  ሁነቱ የሚጀመረው ምሽት የኢሻ ሶላት (የምሽት ስግደት) ከተፈጸመ በኋላ ሲሆን ቀኑን ሙሉ ወደ ከበራው ቦታ ሲገባ የዋለውን እንግዳ በተዘጋጀለት ቦታ ከታደመ በኋላ ነው። በዚህ ሁነት የሚከናወኑት ዋና ዋና ሒደቶች መካከል የመጀመሪያው ቡድን ሰርቶ በመቀመጥና የጫት

[30] በእምነቱ ይህ ስርአት በሁለት መንገድ ይፈጸማል። አንደኛው በግል የሚፈጸም ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በቡድን የሚፈጸም ነው። እንደ ሼህ አብዱልቃድር ፊድሉ ገለጻ ከሆነ የኡለማ መውሊድ ላይ የሚደረገው የዱኣ ክዋኔ በአብዛኛው (ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ) በቡድን የሚፈጸም ነው። ለዚህ የሚቀርበው ምክንያት ደግሞ መውሊድ በባህሪው ሰዎችን የማሰባሰብና የማገናኘት ዓላማ ስላለው ነው።

እደላውን መጠባበቅ ነው፡፡ በመቀጠል ደግሞ ከዳሚዎቹ[31] በቡድኖቹ ውስጥ እንደሚገኙት አባላት ብዛት እየመጠኑ ጫት የማደል ሒደት ያከናውናሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በመውሊዱ አስተባባሪ ኮሚቴዎች የሚመደቡ ናቸው፡፡ የዚህ የቡድን ክዋኔ አላማም ጸሎትና ተለማምኖ ነው፡፡ በምዕመናን ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጠው የከበራው ሁነትም ነው፡፡[32] ለዚህ በምክንያትነት የሚጠቀሰው ደግሞ ምዕመኑ በየዕለቱ የሚያጋጥሙትን አንገብጋቢ ችግሮች የሚያነሳበት፣ ላለበት ስኬት ደግሞ ለፈጣሪ (ለአላህ) ምስጋና የሚቀርብበት እና የወደፊቱን ህይወት ብሩህ እንዲሆን ልመና የሚቀርብበት በመሆኑ ነው፡፡



*ምስል 2 በዳንንግላው ሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓል ጫት በመቃም የሚደረግ ዳዕዋ (የጸሎት ሥነ ሥርአት) በ 10/06/05 ዓ.ም ምሽት 3፡20 ላይ፡፡*

በከበራው ወቅት በምልከታየ ለማስተዋል እንደቻልኩትም የዳዕዋው ክዋኔ በሚካሄድበት ወቅት በአሉን ለመታደም የመጣው ምዕመን ለበዓሉ ማክበሪያ በተዘጋጁት ትላልቅ ዳሶች ውስጥ በክብ በክብ (እንደየፍላጎታቸው በአራት በአምስት እስከ አስር ሊዘልቅ ይችላል) ቅርጽ ሰርቶ

[31] ከዳሚ ማለት አስተናጋጅ እንደማለት ሲሆን የዱኣው ክዋኔ በሚካሔድበት ወቅት ማንኛውንም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የሚያሟላ ነው፡፡ በዚህ ሒደትም የከዳሚው ሚና ጫት የማደል፣ ላለቀባቸው የመጨመር፣ ጭስ የማጨስ፣ ለጫት ማቃቃሚያ የሚሆኑ እንደ ለውዝ፣ ውሀና ለስላሳ የመሳሰሉ ነገሮችን ማቅረብ ነው፡፡

[32] ሐጅ ሙሀመድ የሱፍ፣ ሐጅ ሙሐመድ ከማል እና አቶ ኡስማን ሰኢዱ በዕለቱ በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ፡፡

በመቀመጥ እግራቸውን አጣጥፈው ይቀመጣሉ፡፡ በየአንዳንዱ ቡድን አባላት ውስጥ በታላቅነታቸው የሁሉንም ፈቃድ ባገኙ አንድ ግለሰብ ፊት የተዘጋጀው ጫት ይቀርባል፡፡ ይህ ሰው የዳዕዋው ክዋኔ ፍጻሜውን እስኪያገኝ ድረስ ለቡድኑ አባላት እንዳስፈላጊነቱ እየመጠኑ ጫት የማደል ሐላፊነት አለባቸው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ በአንድ ቡድን ውስጥ የሚገኝ አባል የጫት ቀንበጥ[33] እንደፈለገ አያነሳም፡፡ ሲያስፈልገው የቡድኑ መሪ "ጀባ" ይለዋል፡፡ አባሉም "መርሐባ" ይላል፡፡ የቡድኑ መሪ በሚያስፈልገው ሰአት ለቡድኑ አባል የጫት እደላ ካላካሔደ የቡድኑ አባል ጫት መፈለጉን ለመግለጽ ሁለት እጆቹን በማሳበቅ ያሻል፡፡ ወዲያውኑ የቡድኑ መሪ "አብሽር" በማለት የጫት ቀንበጥ ሁለት እጆቹ ላይ ያስቀምጣል፡፡ የቡድኑ አባልም ጮክ ባለ ድምጽ **"መርሐባ"** ይላል፡፡ የቡድኑንም መሪ እጅ ይስማል፡፡ ይህ የቡድን ክዋኔ ለበአሉ ማክበሪያ በተዘጋጁ ሶስት ትላልቅ ዳሶችና አንድ ትልቅ መስጊድ በቡድን በቡድን ይከወናል፡፡ በዚህ ክብረ በአል ከመስጊዱ በስተግራ በኩል የሚገኘው ዳስ ለሴቶች የተዘጋጀ ሲሆን በዚህ ውስጥም ከላይ የገለጽኩት ክዋኔ በተመሳሳይ መልኩ ይፈጸማል፡፡

በዚህ ሁነት ክዋኔ ላይ በየቡድኑ ካሉ መሪዎች በላይ ደግሞ በመስጊዱ ውስጥ በተዘጋጀው መድረክ ላይ ያሉ (የታደሙ) የሼህ ሁሴን አለሙ ቤተዘመዶችና ከተለያዩ የሐገሪቱ ክፍል የመጡ የዕምነቱ ኡለማዎች በሶስቱም ዳሶችና በትልቁ መስጊድ ውስጥ የሚካሔደውን አጠቃላይ የዳዕዋ ክዋኔ ይመራሉ፡፡ በዚህም መሰረት ከላይ የገለጽኩት የየቡድን ክዋኔ መጠናቀቁን ተከትሎ የክዋኔው መሪ የሆኑት የሼህ ሁሴን አለሙ ልጅ ሐጅ ሲራጁዲን ሁሴን "ቢስሚላሒ ሮህማን ሮሒም" በማለት፡፡ ለ43ኛ ጊዜ የሚከበረው የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓል የዳዕዋ (የጸሎት) ስርአተ ክዋኔ መጀመሩን ገለጹ፡፡ በዚህን ጊዜ በየቡድን የነበረው ክዋኔ ወደ ህብረት ተቀይሮ በጋራ "አላህምዱሊላሒ ረቢል አለሚን ላኢላ ሐኢለሏህ ሙሐመድ ረሱለሏህ" ከተባለ በኋላ "ስለላ አለይ ሙሀመድ ስለላ አለይ ወሰላም" በሚል የጋራ መንዙማ ተከተለ፡፡ ይህ ሲሆን የክዋኔው መሪ የሆኑት ሐጅ ሲራጁዲን ሁሴን ከመስጊዱ መድረክ ላይ የሚያደርጉትን እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ሁሉም ምዕመን በያለበት በሶስቱም ዳሶች ውስጥ ሆኖ በኤል.ሲ.ዲ ፕሮጀክተር እየተከታተለ እንቅስቃሴውን አብሮ ይጋራል፡፡

[33] ቀንበጥ ማለት የጫት ዘለላ ማለት ነው፡፡



*ምስል 3 የዳዕዋው ማስጀመር ስነስርአት ምዕመናኑ ከዳስ ውስጥ ሆኖ በኤል.ሲ.ዲ ፕሮጀክተር ሲከታተሉ (ከወንዶች ዳስ የተወሰደ ምስል)*

በጥናቴ ሒደት ይህ ክዋኔ በሴቶች ዳስ ተመሳሳይ አንደምታ እንዳለው (በወንዶች የሚፈጸሙ ሁነቶች በሴቶችም እንደሚፈጸሙ) በምልከታየ ማስታዋል ችያለሁ፡፡ ነገር ግን በምሽቱ ክዋኔ በወንዶች ዳስ በቪዲዮና በፎቶግራፍ የታገዙ መረጃዎችን መሰብሰብ የቻልኩትን ያህል በሴቶቹ ለማሰባሰብ ፈቃድ አላገኘሁም፡፡ ቢሆንም ግን ባሰማራዋቸሁ መረጃ ሰብሳቢዎች አማካይነት ቀጥተኛ ያልሆነ የምልከታ በመረጃ አግኝቻለሁ፡፡ በተጨማሪም በሴቶቹ በኩል ተሳታፊ የነበሩትን ወ/ሮ ከድጃ ኢሳ እና ወ/ሮ በለጡ ጀማል ጋር በ10/05/2006 ቀጥተኛ የሆነ ቃለ መጠይቅ አድርጊለሁ፡፡

በዚህም መሰረት ሴቶቹ በወንዶቹ ዳስ እንደሚፈጸመው በተመሳሳይ መልኩ በየቡድን ተቀምጠው ጫት እየቃሙ የዳዕዋ (ጸሎት) ክዋኔን ይፈጽማሉ፡፡ በንኡስ ቡድኑም ውስጥ በኢማን[34] እና በእድሜ በለጥ ያለችው የቡድኑ መሪ በመሆን የጫት ቂምሐውንና የዱኣውን ስነ ስርአት ትመራለች፡፡ በክዋኔውም ወቅት ሴቶቹ የሚያስቡትንና እንዲሆንላቸው የሚፈልጉትን ጉዳይ ለንኡስ ቡድኑ አባላት ይናገራሉ፡፡ አባላቱም በየተራ የተናገረችውን ግለሰብ

[34] ኢማን ማለት የሐይማኖቱን ህግጋቶች በስርአት ማወቅና መፈጸም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የንኡስ ቡድን መሪም ካሉት አባላት የተሻለ የእምነቱ እውቀት ሊኖረው ይገባል ማለት ነው፡፡

ስም እየጠሩ "እንግዲህ ሼሆቹ መጀን፣ ያልሽው ሁሉ ይሳካልሽ፣ ያሰብሽው ይሙላልሽ… እንግዲህ እናቴዋ ቤተሰቦችሽን፣ ልጆችሽን፣ ቤትሽን ሰላም ያድርግልሽ፡፡" እያሉ ይመርቋታል፡፡ እሷም ሁለት እጆቹዋን ወደ መራቂዋ የቡድን አባል ዘርግታ "አሜን…አሜን…አሜን…" ትላለች፡፡ ሌሎቹ የቡድኑ አባላት ደግሞ "ይሁን…ይሁን…ይሁን…" በማለት ምርቃቱ እንዲደርስ መስማማታቸውን ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ የዳዋ ክዋኔው በንኡስና በትልቅ ቡድን ከሚደረጉ ጸሎቶች በተጨማሪ መሐል መሐል ላይ የምርቃትና የመንዙማ ሁነቶችን አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ሒደት ሁሉም የመውሊዱ ተሳታፊዎች በናፍቆት የሚጠብቁትና ሳያልፉቸው የሚከውኑት ነው፡፡

በቃለ ምልልስ ያገኘሁት መረጃ እንደሚያመላክተው በዚህ ዱኣ ክዋኔ በሃይማኖታዊው እምነትና በማኅበራዊ ህይወታቸው የሰመረ ግንኙነት ያላቸው፣ በአንድ የአስተሳሰብ አድማስ የሚገናኙ በአንድ ዓላማ የተሰባሰቡ የበዓሉ ዋና ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ የማኅበራዊ ችግረቻቸውም ሆነ የግል ብሶታቸው የመፍትሄ ቁልፍ የሚገኝበት የሰመረ ዱኣ የሚከወንበት በመሆኑ በዚህ ሁነት ንቁ ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ የመውሊዱ ዋና ክዋኔ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍበት ጠንካራ የእምነት ሰንሰለትም የሚገኘው በዚህ ሁነት ውስጥ ነው፡፡

በዚህ በዱኣው ክዋኔ **ምርቃት** ዋና እና አብይ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሁነት የሚከወነው በዳዕዋው መሐል መሐል ላይ ሲሆን የሚከወንበትም ዋና አላማ መልካም ምኞትን ለመገላለጽና የተሻለ ነገር እንዲገጥም በመመኘት ነው፡፡ የዚህ ክዋኔ ሚፈጸመው በቡድን ሲሆን የዚህ ክዋኔ የሚመራው በ "በረክ ባይ" (መራቂ) ነው፡፡ ይህ መራቂ ከተሳታፊዎቹ መሐል በዲንና በእድሜ ከፍ ያለ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ብቻ ለመመረቅ መስፈርት አይደለም፡፡ መራቂው ምኞቱንና ሐሳቡን ቶሎ ቶሎ የማመንጨትና የማለት ተፈጥሯዊ ተሰጥኦ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህን ሁነት በተመለከተም የክብረ በአሉ የረጅም ጊዜ ተሳታፊ የሆኑት ሼህ አህመድ ሀሚድ በ 11/05/2005 ዓ.ም ባረኩላቸው ቃለ መጠይቅ፡-

> ምርቃት የመልካም ምኞት መግለጫ ነው፡፡ መራቂው በምረቃው ላይ የሚገኙትን ሰዎች (ተመራቂዎች) ወደፊት እንዲሆንላቸው የፈለገውን ነገር የሚገልጽበት ነው፡፡ ይህ ሲፈጸም ግን የራሱ የሆነ ስርአት አለው፡፡ ትላንት ማታ እንዳየሽው መራቂው ሲጀምርም ሆነ ሲጨርስ ሰለዋት (ነብዩን በማወደስና በመዘከር) ነው፡፡ መሐል ላይ ደግሞ መራቂው ምኞቱን ሲገልጽ ተመራቂወቹ አሚን…አሚን…አሚን… በማለት መቀበላቸውን ይገልጻሉ፡፡ ይህ እንደዲህ የሚፈጸመው ኸመህል ሐድራው ሲደራ ነው፡፡

በማለት ነግረውኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በምልከታ ወቅት እንዳስተዋልኩት የመራቂውና ተመራቂው የሐይል ግንኙነት ተዋረዳዊ (የሰጭና ተቀባይ) ሲሆን መራቂው የሚለው ነገር ሁሉ እንዲፈጸምና እንዲሆን ተመራቂዎቹ "አሚን፣ ይሁን" በማለት ማረጋገጫ ይሰጣሉ፡፡ የዚህን ሁነት ክዋኔ ስንመለከት በመጀመሪያ ሊመርቅ የተነሳው ሰው "በረክ ባይ" (መራቂ)፡

*"ቢስሚላህ አላህምዱሊላሒ" (በጌታየ ስም እጀምራለሁ)*

*"አሏሁመሶሌ ወሰሊ ማአላ ሰይዲና ሙሐመዲን" (በነብያችን ላይ እዝነትና ረሀመት ይውረድላቸው)*

በማለት በሰለዋት (ነብዩን በማወደስና በመዘከር) ከጀመረ በኋላ በቀጥታ ወደ ምርቃቱ በመግባት፡-

**መራቂ (በረክ ባይ)፡-**

"ዱኣችንን መቅቡል አላህ ያርግልን" ............................ ሲል

**ተመራቂዎች፡-** (ሁለት እጅን ወደፊት ዘርግቶ የፊት ለፊት ጣቶችን ወደ ፊት በመዘርጋትና በማጠፍ)

"አሚን" ...................................................... ይላሉ፡፡

በመቀጠልም በተመሳሳይ መልኩ፡-

| *መራቂ* | *ተመራቂዎች* |
|---|---|
| አላህ ያስደሳን.................................................................................. | አሚን |
| ለምነው ከማያፍሩት አላህ ያድርገን ............................................................ | አሚን |
| ያልቀጠነ የወፈረ፣ ያላጠረ የረዘመ የሆነውን ዱኣ አላህ ያርግልን............................ | አሚን |
| እዱኒያም ከኪስህ እንጅ ከቀልብህ የማትገባ አሏህ ያርግልህ ................................ | አሚን |
| አሁን ሠአህ[35] በርከት ......................................................................... | አሚን |
| አንተን እንደወተት እዱኒያን እንደ ድመት አሏህ ያርግልህ ................................... | አሚን |
| መደሰት እንጅ መከፋት የሌለው ማግኘት እንጅ ማጣት የሌለበት................................ | አሚን |
| ስንኖር በአላህምዱሊላህ ስንሞት በሻሀዳ አላህ ያርግልን፡፡ ....................................... | አሚን |
| እሜትን ፣ ውሽትን፣ ገፍላን ፣ ትግትናን (ድብርት) አላህ ያላቅልን .............................. | አሚን |
| ቁርአን ሐዲስ ነሲባችን አላህ ያርግልን ...................................................... | አሚን |
| እጣችን ተፈሪ አላህ ያርገው .................................................................... | አሚን |
| በገባንበት ሁላ ውጤታማ አላህ ያርግልን ....................................................... | አሚን |
| ሒታማችንን[36] አላህ ያሳምርልን ............................................................... | አሚን |
| ጠባያችንን፣ አህላቃችንን እንደረሱል የምንሆንበትን እጣ አላህ ይደለን ........................ | አሚን |
| ሰዎችን የማሳንከፋ፣ የመንከፋ ሙሐባችን ዘለቄታ ያለው አሏህ ያርግልን ......................... | አሚን |
| ወጣት አይወድም ማጣትንና አያሳጣን ............................................................ | አሚን |

**"አሏሁመሶሌ ወሰሊ ማአላ ሰይዲና ሙሐመዲን" (በነብያችን ላይ እዝነትና ረሀመት ይውረድላቸው)**

በማለት ምርቃቱን ይቋጫል፡፡ የዚህን ምርቃት (የአንድ መራቂ ምርቃት) መቋጨት ተከትሎ በዱኣው ክዋኔ በተሰራው ንኡስ ቡድን መካካል የመዘያየር ስርአት ይከተላል፡፡ ይህ የሚደረገው

---

[35] ሰአት (በዚህ ይሁንበት ወይም አሁን በተገናኘንበት ሰአት ይሁንበት)

[36] እልፈተ ህይወታችንን፣ በሻሀዳ የምንሞት አላህ ያድርገን ማለት ነው፡፡

"በረክ ባይዩ" (መራቂው) ከላይ ያቀረባቸው ምርቃቶች ለንኡስ ቡድኑ እንዲደርስ በተናጠል "አሚን፣ ይሁን" በማለት የሰበሰቡትን ለቡድን አጋሮቹም እንዲደርስ ምኞት ሚገላለጹበት መሆኑን ለመረዳት ችያለሁ። ይህ ክንዋኔም በየተራ እየተነሱ የሚመርቁት "በረክ ባይዩች" በጨረሱ ቁጥር ይፈጸማል።

በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ ክብረ በአል የቀረቡትን ምርቃቶች ስንመለከት በአብዛኛው ኢማን፣ መልካም ስነምግባር፣ ጤና እና ሐብት እንዲኖረን የሚጠይቁ ሲሆኑ ወቅታዊ ጉዳዮችም እንደሚነሱ በቃለ መጠይቅ ያገኘሁት መረጃ ያመላክታል። በዚህ ጉዳይ ላይ እኔም በቦታው ላይ በነበረኝ ምልከታ በሌሊቱ የዱኣ ክዋኔ ከወቅቱ እስላማዊ እንቅስቃሴ ጋር በተገናኘ "ሐገራች ሰላም፣ ኑሯችን ገራም፣ አካባቢያችን ለም እና የተጀመሩ ልማቶች በሰላም የሚጠናቀቁ አላህ ያድርግልን" የሚሉ ምርቃቶች ከላይ በቀረበው የምርቃት ክዋኔ በተመሳሳይ መልኩ ሲፈጸሙ አስተውያለሁ። ጉዳዩን በተመለከተም ከሼህ ሙሀመድ አብዱላሂና እና ከሼህ ኡስማን ሞላ ጋር ባደረኩት የቡድን ውይይት በምርቃት ሁሌም ወቅታዊ ማህበራዊ ጉዳዮች እንደሚነሱ ለመረዳት ችያለሁ። ይህ ሚሆነው ደግሞ ሁሌም በማህበራዊ ህይወት የሚገጥሙ ችግሮን ፈጣሪ እንዲያቀል መልካም ምኞት ለመግለጽ ነው። ይህን ጉዳይ በተመለከተም ፅጌ ንጋቱ አስጨናቂ (1982) "የሼህ ሰይድ ቡሽራ ታምራት አፈታሪክና የሞሊድ በዓል አከባበር በገታ/ወሎ" በሚል ርዕስ ባቀረበችው ጥናት፤ በመውሊድ በዓሉ ላይ የቀረቡ ምርቃቶችን በሚያይበት ክፍሉ ካቀረበችው ምርቃቶች መካከል "በወቅቱ በአካባቢው የነበረውን የደርግና የኢሀዲግ ጦርነት በሰላም እንዲተካ" የሚመኙ ምርቃቶች መተንነኑን ልብ ይሏል።

#### 4.1.3.3 መንዙማ

በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ ከበራ የመንዙማ ግጥሞች የሚከወኑት በዱኣው መሀል መሀል ላይ ነው። በዚህ ሁነት የሚቀርቡት መንዙማዎች አጠቃላይ ይዘት የአላህን ታላቅነት የሚገልጹና የነብዩ ሙሀመድን መልዕክተኛነትና ለሙስሊሙ ህብረተሰብ ያበረከቱትን ድንቅ ስራ የሚዘግቡ ሲሆን፡ የሚቀርብበት ድምጸት እኛም እንደሳቸው ደግና መልካም ባደረገን የሚል ነው። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ከበአሉ ተሳታፊ ሼህ ጣሒር ሙሳ በ11/06/2005 ዓ.ም በክብረ በአሉ ፍጻሜ ላይ በተደረገ ቃለ መጠይቅ፡-

> የመንዙማ ዝማሬ የእስልምና ሃይማኖት የሚሰበክበት ነቢዩ መሐመድና ሌሎች ነቢያት፣ ከሊፋዎች የሚወደሱበት፣ ማኅበራዊ ችግሮች የሚነሱበትን ግጥሞች የሚይዝ ነው። የመንዙማ ግጥሞች የሚቀርቡባቸው ቋንቋዎ አረብኛና አማርኛ ነው።

በማለት ይገልጻሉ፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ ሼህ ጣሒር በተጨማሪ የመውሊዱ አስተባባሪ ሼህ ኡስማን ሰኢዱ የሚከተለውን ብለውኛል፡-

> *እንግዲህ…መንዙማ ማለት እየፈለጉ እሚሉበት ቦታ ያጡ አሉ፡፡ ይህንን ሲያገኙ ግን ያ ናፍቆታቸው ይወጣላቸዋል፡፡ ከሚያስቡት በላይ አቀባበሉ፣ ድቢው፣ ጭብጫቦው፣ ሁለመናው ሶፋውን ሲያዩት ሌላ ሐድራ ውስጥ ነው ሚገቡት፡፡ እና ያንን ናፍቆታቸውን ተወጥተው የሚሔዱበት ቦታ ነው ባጠቃላይ፡፡*

ከነዚህ ሀሳቦች በመነሳት መንዙማ መውሊድን አንድ የመከወኛ አጋጣሚ አድርጎ የሚከወንና አላህን፣ ነቢዩ መሐመድን፣ ሌሎች ነቢያትና ከሊፋዎችን የሚወደሱበት፣ ማኅበራዊ ችግሮች የሚነሱበት፣ በድቢና ጭብጨባ እንዲሁም በእንጉርጉሮ የሚቀርብ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መንዙማ በሚባልበት ጊዜ በፍጹም ሊነጣጠል የማይችለው ጉዳይ መንዙማውን ለማድመቅ የሚመጡት እንደ በድቤና ከበል የመሳሰሉት ቁሳዊ ባህሎች መሆናቸውን ከላይ ከተጠቀሱት መረጃ አቃባዮቼ ጋር በነበረኝ ቆይታ ለመረዳት ችያለሁ፡፡[37]

እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ደግሞ ለክብረ በዓሉ የሚሰጡት ድምቀት ከፍተኛ ከመሆኑ ባሻገር ከሙስሊሙ ህብረተሰብ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ስለዚህ የመንዙማውን ቃል ግጥም ይዘት ስንመለከት አያይዘን እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች እንመለከታለን፡፡ (እዚህን ቁሳዊ ባህሎች ለመንዙማዎች ክዋኔ የሚኖራቸው ሚና በቃላዊ ግጥሞቹ ክዋኔ ክፍል (4.2.2) ሰፋ ያለ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡)

በአጠቃላይ በዚህ ሁነት ክዋኔ ላይ ተሳታፊው ከፍተኛ ፌሽታ የሚያደርግበት፣ የእምነቱን ውስጣዊ ግለት የሚተነፍስበትና ህብራዊ ቅብብሎሽ ሚስተዋልበት ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የዚህን ክዋኔ ሒደትና ድርጊት በቃላዊ ግጥሞቹ ክዋኔ ክፍል (4.2.1) በስፋት መመልከት ይቻላል፡፡

### 4.1.4 የክዋኔው ማግስት

ክብረ በዓል ላይ ትኩረት ያደረጉ የፎክሎር ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ማንኛውም ክብረ በዓል ሒደቱን የሚጨርሰው ለራሱ በሚደረጉ ዝግጅቶች መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ በተመሳሳይ

[37] በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ በቀጣዩ ንኡስ ክፍል እነዚህን የመንዙማ ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ በተመለከተ ሰፋ ያለ ትንታኔ ቀርቧል፡፡ ነገር ግን በዚህ ክፍል ስለ መንዙማ ማንሳት ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ቃላዊ ግጥሞች የዳዕዋው አንዱ ሁነት መሆናቸውን ለማሳየትና መሀል የሚመጡበትን ምክንያት ለመግለጽ በመፈለግ ነው፡፡

መልኩ የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓል ስርአተ ክዋኔም በዋዜማው በሚደረጉ ልዩ ልዩ ቅድመ ዝግጅቶች እንደመጀመሩ ሁሉ የራሱ የሆነ ማጠቃለያ አለው፡፡

ይህ የስርአተ ክዋኔ ማግስት ደግሞ መውሊዱ ሥርአቱን በጠበቀ መልኩ እንዲፈጸም የሚያስችሉ ስራዎች የሚከናወኑበት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል ደግሞ የሸኙት ስርአት በዋናነት ይጠቀሳል፡፡ ይህ ሁነት ለበአሉ የመጡ እንግዶች ወደመጡበት የሚመለሱበት ሲሆን የካቲት 9 ለ 10 ሌሊት ያደረው አብዛኛው ምዕመን በዕለቱ (የካቲት 10) የመውሊዱን ምግብ ተመግበው ወደየመጡበት ይመለሳሉ፡፡ በዚህ ቀን ያልተመለሱትና በዕለቱ ከበራውን የሚቀላቀሉት ደግሞ የካቲት 10 ለ 11 ሌሊት አክብረው የካቲት 11 ወደየመጡበት ይመለሳሉ፡፡ ይህንንኑ የሸኙት ስርአት በተመለከተ ምንያህል ምዕመን ወደ ከበራው መጥቷል እንዴትስ ተስተናገደ ከአቶ ኡስማን ሰኢዱ ጋር በ10/06/2005 ዓ.ም በተደረገ ቃለ ምልልስ ፡-

> ..እንግዲህ እኛ የመዝገብ መረጃ ባይኖረንም፣ ሲጀመር በአንድ ከብት ነበር እና አሁን ላይ የታደረውን ስትመለከት የሰውን ብዛት መገመት ትችላለህ፡፡ ትላንት በግምት ከ20 እስከ 30 ሽ የሚሆን ሰው አስተናግደናል፣ እንግዲህ ዛሬ ይህ ሰው የለም ወደቤቱ ሒዷል ዛሬ ደግሞ በተመሳሳይ የዚህኑ ያህል ቁጥር እያስተናገድን እንገኛለን፡፡ ከእንግዶች በተጨማሪም የከተማውን ሰው ስትመለከት የትላንቱ ወደቤት ሔዶ ይጠብቃል ትላንት ቤት የጠበቀው ዛሬ ይመጣል፡፡ ዛሬ ሚሔደውም ሆነ ነገ ሚሄደው የተህሊል ውኃ እያየዘ ይሄዳል፡፡ እንግዶቹም በሰላም እንዲመለሱ የማስተባበር ስራ ይሰራል፡፡

በማለት ነገረኝ፡፡ ከዚህ ላይ ከሸኙት ሁነቱ ጋር ተያይዞ በነበረኝ ምልከታ በርካታ የበአሉ ተሳታፊዎች በመስጊዱ ውስጥ ካለው የውሀ ጉድጓድ እየቀዱ ወደየቤታቸው ሲሔዱ በማየቴ፤ ምእመኑ ወደመጣበት ሲመለስ ለምን የተህሊል ውኃ እየያዘ ይሄዳል? ውሀው በክብረበአሉ ተሳታፊዎች የሚሰጠውን ትርጓሜ ምንድን ነው? የሚሉ ነጥቦችን ምክንያቶች ለማወቅ ለአቶ ኡስማን ሰኢዱን ጠየኩ፡-

> ይኸ እንግዲህ፣ አላሀምዱሊላህ ሼሆቻችን ከሳውዲአረቢያ መካ ለሐጅ በሔዱበት ወቅት ላይ ማኡ ዘምዘም አምጥተው በቃ ከዚህ በኋላ እኔን ልታገኙኝም ላታገኙኝም ስለምትችሉ ተህሊል ብላችሁ ሌላ ነገር ለማግኘት ከምትንገላቱ እራሱን ተህሊል አድርጌላችኋለሁ ብለው ያንን ማኡ ዘምዘም ደብልቀው ነው፣ በአካል ጉድጓዱ ውስጥ እንደዚያ አድርገው ነው የመሰረቱት፡፡ አሁን ከዚህ በኋላ ምንድን ነው ወላ ችፌም ይያዘው፣ እከክም የያዘው፣ ምንም የያዘው ይጠጣል ይታጠባል ከዛ ወሰላም፡፡ ከሌ ስጠኝ ከሌ ስጠኝ ብሎ ነገር የለም፡፡ ይህን የመሰለ አድያ አድለውን ነው ያለፉት፡፡

በማለት መለሰልኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከበአሉ ተሳታፊዎች መካከል ከወ/ሮ ዘምዘም ከድር፣ ከወ/ሮ ከድጃ ግርማ እና ከአቶ ሐሽም ኢብራሒም ጋር በ10/06/2005 ዓ.ም በበአሉ ማክበሪያ ቦታ በነበረኝ ቃለ ምልልስ በባዕሉ ፍጻሜ በግቢው ውስጥ የሚገኘውን የጉድጓድ ውሀ እንደ

ማኸ ዘምዘም (የዘምዘም ውሀ) በልዩ ልዩ እቃዎች እየቀዱ እንደሚመለሱ ተረድቻለሁ፡፡ ይህን የሚያደርጉበትም ምክንያት ደግሞ ውሀው ለልዩ ልዩ በሽታዎች ፈውስ (መድሐኒት) ነው ተብሎ ስለሚታመን ሲሆን ስለውሀው የሰማው ሁሉ አቅሙ በፈቀደለት መጠን ይዞ ወደቤቱ ይመለሳል፡፡ ቤቱ ውስጥ በማስቀመጥም ባስፈለገው ሰዓት የውስጥ ደዌም ይሁን ቆዳ በሽታ ሲያጋጥመው እየቀነሰ ይጠቀምበታል፡፡ በዚህም ፈውስን ያገኛሉ፤ ደስተኛም ይሆናሉ፡፡ (በዚህ ነጥብ ላይ ከላይ ከአቶ ኡስማን ሰኢዱ ጋር የተደረገውን ቃለ መጠይቅ ልብ ይሏል፡፡)

በአጠቃላይ ከላይ በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓል ስርአተ ክዋኔ የተመለከትናቸው እያንዳንዱ ሁነቶች እርስ በዕርስ የተያያዙና አንዱ ለአንደኛው መሰረት ያለው ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ Rappaport (1992, 249) "ክብረ በዓል ከአብዛኞቹ የመግባቢያ አይነቶች አንዱ ሳይሆን ለሌሎች (በቋንቋ ጭምር ለማይገለጹት) ተግባቦቶች መነሻ የሆነ፤ ግልጽ የሆነ ቅርጽ ያለው፤ የተለያዩ ገጽታዎችና ባህሪያት ያሉት ከመሆኑም በላይ እነዚህ ባህሪያቶቹ አነሰም በዛም እርስ በእርስ የተያያዙ ናቸው፡፡" በማለት ገልጾታል፡፡

## 4.2 በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ ክብረ በአል ላይ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞችና ቃላዊ ግጥሞቹን ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች

### 4.2.1 በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ ክብረ በአል ላይ የሚቀርቡ መንዙማዎች ክዋኔ

በመውሊድ በዓል ላይ የሚቀርቡት ቃል ግጥሞች መንዙማ በመባል ይታወቃሉ፡፡[38] እነዚህ መንዙማዎች በዓሉን ለማክበር በመጡ ምዕመናን የሚባሉ ሲሆን አጠቃላይ ይዘታቸውም የነብዩን ሙሀመድ ታላቅነት የሚነግሩና በሳቸው ታላቅነት ሁላቸውም (የበዓሉ ታዳሚዎችም ሆኑ ምዕመናኑ) ከዚህ መድረሳቸውን የሚገልጹ ናቸው፡፡[39] በዳንግላው ሼህ ሁሴን አለሙ

---

[38] ብርሃኑ ገበየሁ በ1990 ዓ.ም "የወሎ ሙስሊሞች ቃል ግጥም" በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናት፣ በምዕራፍ ሁለት መንዙማዎች የሚቀርቡባቸውን ማህበራዊ አውዶችና የከበራ ሂደት ሲገልጽ፡- ኢድ-ኣል- አድሃ፣ ኢድ-ኣል-ፈጥር፣ ራመዳን፣ መውሊድና ወዳጃ ናቸው፡፡ ብርሀኑ በነዚህ ሁሉ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ተሳታፊ ምልከታ አካሂዶ በቦታው ያየውን የመቼት ሁኔታ ሲገልጽ፤ በሁሉም አጋጣሚዎች ሃድራ የሚባል ዝግጅት እንዳለና በመንዙማ በመታጀብ ደስታንና ሀዘንን ለመግለጽ የሚያገለግልና ለህክምናም የሚጠቀሙበት ዝግጅት መሆኑን አበክሮ ያስረዳል፡፡

[39] በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ "መንዙማ" በእምነቱ ስርዓት ውስጥ ያስፈልጋል፡ አያስፈልግም በሚሉ ወገኖች መካከል ያለው ሙግት እንዳለ ሆኖ እነዚህ የኢትዮጲያዊያን ሙስሊሞች ብቸኛ ጥበባዊ የውዳሴ ስርዓት (አላህና ነብዩ ሙሀመድ ሚሞገሰባቸው) እንደመሆናቸው መጠን እንደ አንድ ፎክሎራዊ ቅርስ መጠናት አለባቸው የሚል ጽኑ እምነት አለኝ፡፡ (አጽንኦቱ የኔ ነው፡፡)

የመውሊድ በዓል ስርአተ ክዋኔ ላይ የመንዙማ ቃላዊ ግጥሞች ዱኣ ስርአት እየተካሔደ ባለበት የሌሊት ወቅት ይከወናሉ፡፡

በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍም የቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ከማሳየቴ በፊት መንዙማ ምንድን ነዉ? ከመውሊድ በአልስ ጋር ምን ቁርኙት አለው? እንዴትስ ተጀመሩ?[40] የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል፡፡ የዚህን ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት በበዕሉ ላይ ተሳታፊ ከነበሩት ሐጅ ሐሩን ሙሳ (የታላቁ አኑዋር መስጊድ ኢማም) ፣ ሼህ አብዱልቃድር ፊድሉ (የእምነቱ ሊቅ) እና ሐጅ ሙሀመድ ኑር አብደላ (በአኑዋር መስጊድ መንዙማ በመክተብ (በመጻፍ) የሚተዳደሩ ግለሰብ ጋር ባደረኩት ቃለ መጠይቅ የሚከተለውን ምላሽ ለማግኘት ችያለሁ፡፡

> ‹‹መንዙማ›› ቃሉ የአረብኛ ሲሆን፣ በጥሬትርጉሙ ‹‹ቃላትን በጥሩ ሁኔታ ማስቀመጥ›› የሚል ፍቺ ይሰጣል፡፡ ጥሬ ትርጉሙ በደንብ ሲብራራ ደግሞ ቆንጆ መልዕክትን ለማስተላለፍ የሚያገለግል ግጥም ይሆናል፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ መንዙማ ከግጥምም በላይ ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ ምክንያቱም መንዙማ ዜማ ተጨምሮበት አላህ የሚመሰገንበት፣ ነብዩ መሐመድ የሚሞገሱበትና የእስልምና ትምህርት የሚሰጥበት ጥበብ በመሆኑ ነው፡፡ በመውሊድ በዓል ከበራ በስፋት ከሚስተዋሉ ኹነቶች ውስጥ ደግሞ አንዱ መንዙማ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ በመውሊዱ ሚሳተፈው ምዕመን በጋራ በመሆን ቀደም ሲል ላጋጠመው ስኬት የልቡን ፌሽታ የሚገልጽበት፣ ለፈጣሪው ምስጋና የሚያቀርብበት፣ ለቀጣዩ እቅዱ ስኬትን የሚለምንበት ከመንዙማ የተሻለ ቡድናዊ ክዋኔ ባለመኖሩ ነው፡፡ የዚህ ቃላዊ ግጥም ክዋኔ በኢትዮጵያ የጀመረው የእስልምና መግባትን ተከትሎ ነው፡፡[41] ይላሉ፡፡

---

[40] *መንዙማዎቹ ኢትዮጲያ ውስጥ የት ቦታ ተጀመረ? በሚለውን ጥያቄ ላይ የመውሊዱን ዋና አስተባባሪ አቶ ኡስማን ሰኢዱን ጨምሮ ሼህ አብዱልቃድር ፊድሉ፣ ሼህ ሲራጅ ጀማል፣ ሐጅ ሙሐመድ ከማል እና ሼህ ዳውድ ፋሪስ ጋር በ09/06/2005ዓ.ም ጠዋት በባዕሉ ማክበሪያ ቦታ ባካሔድኩት የቡድን ውይይት፤ አብዛኛው ሰው ወሎ አካባቢ ተጀምሮ ይሆናል የሚል መላምት እንዳለውና አንዳንድ ኢትዮጵያውያንና የውጭ አገር ጸሐፊዎች የመንዙማን መነሻ ለማወቅ የተለዩ ጥናቶችን ቢያደርጉም መነሻው ኢትዮጲያ መሆኑን ከመግለጽ ውጭ በትክክል ከዚህ ቦታ በሚል ለመናገር ግን በቂ መረጃ አለማግኘታቸውን ተረድቻለሁ፡፡ እኔ ግን ወደፊት ሰፊ ጥናት የሚያደርግ የፎክሎር ወይም የባህል ተመራማሪ ከ4ኛው መቶ ክፍል ዘመን (እስልምና ወደ ኢትዮጲያ ከገባበት) አንስቶ በሀገር ውስጥም ሆነ ተሰርቀው ወደ ውጭ ሀገር የሄዱትን እስላማዊ መረጃዎች በሰፊ ጥናት ትኩረት ተሰጥቶት ቢፈትሽ የመንዙማን ትክክለኛ መነሻ ማወቅ ይቻላል ባይ ነኝ፡፡*

[41] *መንዙማን በተመለከተ ያገኘሁት ተጽፎ የተገኘ መረጃ ባይኖርም ከሐጅ ሐሩን ሙሳ (የታላቁ አኑዋር መስጊድ ኢማም) እና ሐጅ ሙሀመድ ኑር አብደላ (በአኑዋር መስጊድ መንዙማ በመክተብ (በመጻፍ) የሚተዳደሩ ግለሰብ) በተመሳሳይ ቀን በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት እንደቻልኩት የመንዙማና የኢትዮጵያ ቁርኙት የሚጀምረው ከእስልምና የመጀመሪያዎቹ ዓመታት አንስቶ መሆኑን ነው፡፡ ነብዩ መሐመድ በሕይወት በነበሩበት ወቅት በሳዑዲ አረቢያ መካ የነበሩ ሐበሾች (ኢትዮጵያዊያን) የአላህን መልዕክተኛ በመንዙማ ያወድሱ ነበር፡፡ ይህ ውዳሴም ይቀርብ የነበረው ሐበሾቹ በራሳቸው ቋንቋ ነበር፡፡ ስለዚህ መንዙማ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች የውዳሴ ስልት ነው በማለት ይገልጹታል፡፡ ሐይማኖታዊ ክዋኔን በመንዙማ በማጀብ የሚታወቁት ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች እንጂ በሌሎች ክፍላተ ዓለም ያሉ የእስልምና ተከታዮች አለመሆናቸውን ለመረዳት ችያለሁ፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ቃለ. ከአትዮጵያ ውጪ ያሉ ሙስሊሞች ሐይማኖታዊ ክዋኔዎቻቸውን የሚያጅቡት ‹‹ነሺዳ›› በተባለ ዝማሬ መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡*

*ከዚህም በተጨማሪ ነሺዳ ቋንቋው አረብኛ ነው፡፡ መንዙማ ግን በኦሮምኛ፣ አደርኛ፣ አማርኛ፣ ስልጢኛ ወዘተ ሲገለጽ ይስተዋላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንዙማ በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያየ ስያሜ እንዳለው ለመረዳት ችያለሁ፡፡ በዚህም መሰረት በሐረር ‹‹ዚክሪ››፣ በባሌናአርሲ ‹‹ባሮ/ሰርመዴ›› በሚሉ መጠሪያዎች እንደሚታወቅ ይገልጻሉ፡፡*

እዚህ ላይ በግርጌ ማስታወሻ ከተገለጹት ነጥቦች በተጨማሪ ልብ ሊባል የሚገባው አንድ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም የመውሊድ በዓል አከባበር ስርዓቱን ባየንበት ንኡስ ክፍል መጀመሪያ ላይ ያነሳነው "ዝያራ" የመንዙማ ሌላኛው ስያሜ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ለጥናቴ ባደረኩት ቃለ መጠይቅ ይህ ግንዛቤ የተሳሳተ እንደሆነና "ዝየራ" ሰላምታን መለዋወጥን ብቻ የሚወክል እንጅ የመንዙማ አቻ ተደርጎ መወሰዱ ስህተት መሆኑን ለማስተዋል ችያለሁ፡፡

ከዚህ ቀደም በጉዳዩ ላይ ቀረቡ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት[42]፣ መንዙማ የመውሊድ ክብረ በዓል ሲዘጋጅ እንደ መውሊዱ አይነት (የነብዩ ሙሀመድም ይሁን የኡለማ) ጥበባዊነት ባለው መልኩ አላህ እየተመሰገነ፣ ነብዩ መሐመድ እተሞገሰ የእስልምና መሰረታዊ አስተምሮዎች እየተሰበኩ የሚከወን ሒደት ነው፡፡ በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ ከበራም ይህን ቃላዊ ጥበብ የዳዕዋው ስነ ስርአት እየተፈጸመ ባለበት የሌሊቱ ክዋኔ ማህል ማህል ላይ ሲፈጸም አስተውያለሁ፡፡ አንድ የፎክሎር ዘርፍ ደግሞ ለመከወን ከዋኝ እና ታዳሚ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ለመከወን ሰበብ የሚሆነው የመከወኛ ምክንያት ሊኖረው ይገባል፡፡[43] ይህ ቃላዊ ጥበብ የክዋኔ ሂደት ደግሞ መውሊዱን ሰበብ አድርጎ ይከወናል፡፡ ሲከወንም ራሱን የቻለ አንድ ጥበባዊ ገጽታ ያለው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በዚህ ጥናትም ከቃላዊ ግጥሞቹ ጋር በተገናኘ በዋናነት የምመለከተው በክብረ በዓሉ ወቅት የተከወኑትን ቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ከክዋኔ ሒደታቸው በመነሳት እንዴት ይከወናሉ? ፣ ሲከወኑ የተሳታፊዎቹ (ከዋኙና ተቀባዩ) ሚና ምን ይመስላል? ፣ የቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ክዋኔ ሒደት በቀረቡበት ደረጃ እንዲከወኑ የሚያስችሉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? ፣ ተሳታፊዎቹ በዚህ የክዋኔ ሒደት መሳተፋቸው ሚያስገኝላቸው ፋይዳ ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስ ላይ አተኩሪያለሁ፡፡

---

[42] አብዱልናስር ሐጅ ሀሰን (1982) "የአውተራህም እና የአሽሪፍ ስርአተ አምልኮ በደደር"፣ ኡመር ዳውድ (1982) "በአዲስ አበባ እስላሞች ዘንድ በመስጊድ ላይ የሚባሉ እንጉርጉሮዎች ጥናት"፣ ሙሐመድ ጀማል (1984) "በወሎ ክፍል ሐገር የሼህ ጫሌ የመውሊድ ግጥሞች (መንዙማዎች) ትንታኔ ከቅርጽና ከይዘት አንጻር"፣ አሊ የሱፍ (1995) "የሼህ ሙሐመድ የህይወት ታሪክ ሐድራቸው ክዋኔያቸውና ግጥሞቻቸው"፣ ሰይድ ሙሐመድ (1997) "የሼህ ሙሐመድ አወል መንዙማዎች ይዘት ትንተና"፣ ሙሐመድ በረሁ (2002) የሼህ ኡመር አብራር መንዙማዎች ፎክሎራዊ ጥናት"፣ፅጌ ንጋቱ አስጨናቂ (1982) "የሼህ ሰይድ ቡሽራ ታምራት አፈታሪክና የሞሊድ በዓል አከባበር በገታ/ወሎ"፣ኪሩቤል ሽንቁጤ (1986) "የቃጥባሬው ሼህ ህይወት ታሪክና የበዓላቸው አከባበር"፣ መሐመድ ሁሴን (1997) "የገበሮች ሼህ የህይወት ታሪክና የበዓላቸው አከባበር"፣ አሸናፊ ምስጉን (1998) "የሼህ አሊ ጎሬ ታምራት አፈታሪክና የበዓላቸው አከባበር በጅጅጋ አካባቢ"፡፡ የሚሉ የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች በተመሳሳይ መልኩ ጉዳዩን አንስታውታል፡፡ (ሁሉም ጥናቶች በአደስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ቤተ መጽሐፍት ውስጥ ይገኛሉ፡፡)

[43] (ፊኔጋን፣1992፣91-92 እና ቦውማን፣1975፣290)፡፡ የፎክሎራዊ ጉዳይ ባህርይ በሚል ስር ካስቀመጡት የመከወኛ አጋጣሚውን በተመለከተ ከገለጹት ሀሳብ የተወሰደ፡፡

በዚህ ክፍልም እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስና የመንዙማዎችን ክዋኔ ለመተንተን እንዲያመቸኝ በማለት በክብረ በአሉ ላይ የቀረቡት የመንዙማ ግጥሞች በተከወኑበት የክዋኔ ሒደት (በሐድራው ላይ በሚቀርቡበት መንገድ) በመመስረት በድቤና በእንጉርጉሮ የሚባሉ በማለት እንደሚከተለው ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

### ሀ. በድቤ የሚባሉ መንዙማዎች

በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓል ስርአተ ክዋኔ ላይ በነበረኝ የቀጥታ ተሳትፎ ምልከታ ላይ ለመረዳት እንደቻልኩት፡ በድቤ የሚባሉ መንዙማዎች በተሳታፊዎች መካከል ከፍተኛ የሆነ መነቃቃትን የሚፈጥሩ፣ በከዋኑ (መንዙማ ባዩ) እና ተቀባዮቹ መካከል ስርአት ያለው ቅብብሎሽ የሚያስከትሉ፣ ክዋኔያቸው ደግሞ ራሱን የቻለ የመክፈቻና የመዝጊያ ቀመር ያላቸው ናቸው፡፡

እነዚህን የመንዙማ አይነቶችን በተመለከተ ሼህ አብዱልቃድር ፈድሉ (የእምነቱ ሊቅ) እና ሐጅ ሙሀመድ ኑር አብደላ (በአኑዋር መስጊድ መንዙማ በመክተብ (በመጻፍ) የሚተዳደሩ ግለሰብ ጋር ባደረኩት ቃለ መጠይቅ ብዙ ሰዎች “ዝያራ”ን ለመንዙማ አቻ መጠሪያ ማድረጋቸው ስህተት ቢሆንም በአብዛኛው በድቤ ለሚቀርቡት መጠሪያ በመሆን እንደሚያገለግሉ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ይህም ማለት እነዚህ መንዙማዎች፡ አብዛኛው ጊዜ በአረብኛ አንዳዴ አማርኛ ቅልቅል ያለባቸው ግጥሞች የሚኖሩትና በአንድ ድምፃዊ አቀንቃኝ እየተመራ በአጠቃላይ ታዳሚዎች ድምፃዊነት በመታጀብ የዜማ ቅብብሎሽ ያለበት ዝማሬ ነው፡፡ በማለት ማጠቃለል እንችላለን፡፡ ይህንንም እንደሚከተለው ለአብነት በቀረበው የመንዙማ ግጥም ማስተዋል እንችላለን፡-

አሏሁም መሶሌ አላ ሙሀመዴ..................... 2 ጊዜ
ሙሀመድ ፣ሙሀመድ የአለሙ ዘውድ
አጀብ[44]፡ ተቆጥሮ የማያልቀው የሱማ ገለታ
ለሙሀመድ ኡመት ያደረገን ጌታ
መሻሪያ ሰጥቶናል ከወንጀል በሽታ
ሰላምና ሶላት ይጉረፉ ጠዋት ማታ
በአህመድ በኛ ጌታ በአዘሉ ውድ
ሙሀመድ ፣ሙሀመድ የአለሙ ዘውድ

---

[44] አጀብ የአረበኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ይገርማል እንደማለት ነው፡፡ (መገረምን፣ መደነቅን ለመግለጽ)

በዚህ ከላይ የቀረበው ግጥም ከረጅም መንዙማ ግጥም ተቀንጭቦ የወጣ ነው፡፡ ይህ ቃላዊ ግጥም በሚባልበት ወቅት “ቅብብሎሽ” ዋነኛ የመቅረቢያ መንገዱ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ስንኞች የመንዙማው አቀንቃኝ ከመድረኩ ሆኖ ይላል፡፡ ልክ እሱ ባለበት ተመሳሳይ ድምጸት ሁሉም ታዳሚ ይደግማል፡፡ የታዳሚውን መጨረስ ተከትሎ አቀንቃኙ ከስንኝ ሶስት እስከ አምስት በእንጉርጉሮ ይላል፡፡ ይህኔ የተሳታፊው ሚና የሚሆነው በጽሞና (በመመሰጥ፣ እራስን በማወዛወዝ) ማዳመጥ ይሆናል፡፡ በዚህ ሒደት ውስጥ ተሳታፊው በጥሞና ያዳምጥ እንጂ ፍዝ ተሳታፊ አይደለም፡፡ ልክ ግጥሞቹ በሚንጎነጎሩበት ጊዜ በጣም የተመሰጠበትና የተገረመበት ቦታ ላይ ሲደርስ “አጀብ” ይላል፡፡ ይህ ድምጽ በክዋኔው ወቅት በተለያዩ ጊዜያት ከተለያዩ ተሳታፊዎች ሞቅ ብሎ ይሰማል፡፡

ይህንኑ የመንዙማ ግጥም ከክዋኔው ሂደት ባሻገር የተነሳውን ይዘት ስንመለከት ከዋኙ “አሏሁም መሶሌ አላ ሙሀመዴ፣ ሙሀመድ ፣ሙሀመድ የአለሙ ዘውድ” በማለት ነብዩ ሙሀመድ የአለም ዘውድ ናቸው በማለት ያውጃል፡፡ ታደሚው ይህን መቀበሉን በመድገም ሲያስተጋባ ከዋኙ አጀብ! በማለት የሙሐመድ ተከታይ በመሆናችን ጌታ ሆነናል፣ ከወንጀላችን ለመጽዳት እድል አግኝተናል፣ ይህን ለማግኘት ደግሞ በጌታችን ስም ሶላት ጠዋትም ማታም እንስገድ ሲል ያንጎራጉራል፡፡ ታዳሚውም ይህን ሐሳብ መጋራቱን ለመግለጽ እራሱን ከወገቡ ጀምሮ ወደ ግራና ቀኝ እያወዛወዘ፣ አንዳንዴም አጀብ (ይገርማል) እያለ ይከተላል፡፡ ልክ የነዚህን ስንኞች መጠናቀቅ ተከትሎ ከዋኙ አዝማቹን በመድገም፡-

*አሏሁም መሶሌ አላ ሙሀመዴ፣*
*ሙሀመድ ፣ሙሀመድ የአለሙ ዘውድ፡፡*

ሲል ታዳሚውም በድጋሚ፡-

*አሏሁም መሶሌ አላ ሙሀመዴ፣*
*ሙሀመድ ፣ሙሀመድ የአለሙ ዘውድ፡፡*

በማለት ይቀበሉታል፤ ወይም የከዋኙን ሐሳብ መጋራታቸውን ይገልጻሉ፡፡ ይህን ብለው ሲጨርሱ ከዋኙ እስካሁን ያንጎራጎረው እንደጸደቀ በመቁጠር ወደቀጣዩ አዝማች ይሻገራል፡-

*አጀብ ሙሀባው አይበርድም እያደር ይብሳል፣*
*አደብ የተባለ በሱ ዲን ይለብሳል፣ ሙሐባ ያለብሳል፡፡*

ካለ በኋላ፤ ልክ እንደመጀመሪያው ስንኞች ሁሉ ያንጎራጎረው የመንዙማ ግጥም ጸድቆለት በድጋሚ ወደቀጣዩ የመንዙማ ግጥም እንዲሻጋገር ፈቃድ ይጠይቃል፡፡ ይህንምም አዝማቹን በመድገም፡-

ሙሀመድ ፣ሙሀመድ የአለሙ ዘውድ

አሏሁም መሶሌ አላ ሙሀመዴ

ሙሀመድ ፣ሙሀመድ የአለሙ ዘውድ

ማለት ሲጀምር እኩል አብራውት ማለት ይጀምራሉ፡፡ ይህኛው አዝማች ከላይኞቹ ተመሳሳይ ቢሆንም በላይኞቹ አዝማቾች ከዋኙ ካለ በኋላ ታዳሚው የሚል ሲሆን በዚህ ጊዜ ግን እሱ ሲጀምር አብረውት እኩል ማለታቸውን አስተውያለሁ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ከሼህ አብዱሰመድ ሙሀመድ እና ሼህ ኡስማን ሞላ (ከወሎ የመጡ መንዙማ አቀንቃኞች) በቀን በ09/06/2005 ዓ.ም በተደረገ ቃለ መጠይቅ የሚከተለውን ሐሳብ አጋርተውኛል፡-

> የመንዙማ ግጥሞቹ በአብዛኛው በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በስፋት መታወቃቸውና ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል እየተላለፉ በተለዩ ቦታዎች በተመሳሳይ መተረካቸው፣ በተጨማሪ በማንና በምን አጋጣሚ እንደሚዜሙ ተመሳሳይ ቅርጽ ማሳየታቸው፣ በትክክል ግጥሞቹ የትኛው ቦታ ላይ በጋራ መባልና የትኛው ቦታ ላይ የመንዙማ አቀንቃኙ ብቻውን ማለት እንዳለበት የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሌም ተሳታፊው እኩል ግጥሞቹን ይከውናል ማለት አይደለም፡፡ እስኪገቡትና አዝማቹ የሚደገምበትን ቦታ እስከሚረዱት ድረስ ከዋኙ የመሪነት ሚና ወስዶ ይከውናል፡፡ ልክ ተሳታፊዎቹ የእሱን እንጉርጉሮ ቅላጼ መሰበርና የአዝማች መድረስን ሲረዱ አብራውት አዝማቹን ይላሉ፡፡ እንዲያውም በደንብ መግባባት ሲጀምሩ ከዋኙ አዝማችን እየጠበቀ የማረፍና ለቀጣዩቹ እንጉርጉሮዎች ለመዘጋጀት እድል ያገኛል፡፡

በላይኛው የመንዙማ ግጥም የክዋኔ ሒደት የተስተዋለውም በቃለ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በቦታው በነበረኝ አስተውሎት ከላይ ለአስረጅነት የቀረበው ግጥም ሲከወን ተሳታፊዎቹ የመንዙማው ግጥም እስኪገባቸውና አዝማቹ የሚደገምበትን ቦታ እስኪያውቁት ድረስ ከዋኙ የመሪነት ሚና ወስዶ ከውኗል፡፡ ልክ ተሳታፊዎቹ የግጥሙ አካሔድ እየገባቸው ሲመጣ አዝማቾቹን አብረው ማለት ጀመሩ፡፡ በዚህም እየቀጠሉና ሲሔዱና ሐድራው እየደራ ሲመጣ ደግሞ ተሳታፊዎቹ በቀላሉ የመንዙማ ባዩን ድምጸት በማድመጥ ብቻ አዝማቹን ማለት ይጀምራሉ፡፡ በዚህ ሒደትም በክዋኔው ላይ እንዳስተዋልኩት ከዋኙ የአዝማቹ መጠናቀቁን ተከትሎ፡-

ጌታየዋ፣ የልቅና እክሊል የረጋው ባናቱ

ጥሩ የጥሩ ልጅ ባባቱም በናቱ

ሙሐባና ረሀመት ይወርዳል በቤቱ

ይላል፡፡ ይኸኔ ታዳሚው የከዋኙ ድምጸት መቀየርንና የድቢው ድምጽ መጀመሩን ምክንያት በማድረግ እኩል በአንድ ላይ ፡----

ሙሀመድ ፣ሙሀመድ የአለሙ ዘውድ

አሏሁም መሶሌ አላ ሙሀመዴ ………………2 ጊዜ

በማለት ያዜማሉ። ክዋኔውም በዚህ መልኩ የመንዙማውን ፍጻሜ እስኪያገኝ ይቀጥላል።

እዚህ ላይ በድቤ የሚባሉት የመንዙማ ግጥሞች ላይ ያስተዋልኩት መሰረታዊ ነገር እንደየመንዙማ ባዮቹና እንደመንዙማዎቹ አይነት የክዋኔው አይነት እንደሚለያይ ነው። ለአብነት ያህል ከላይ የቀረበው የመንዙማ ግጥም ረዘም ያለውን ስንኞች ከዋኙ ሲል ተቀባዮቹ አዝማቹን ለማለት የሚጠብቁት የጊዜ ፍጆታ ረዘም ያለ ሲሆን ቀጥለን በምንመለከተው የመንዙማ ክዋኔ ግን የከዋኙና የተሳታፊዎቹ ሚና እኩል እሱ ሁለት ስንኝ ሲል እነሱ ፈሱሉን (አዝማቹን) እያሉ በእኩል ሚና የሚከውኑበት ነው። ይህንንም በሚቀጥለው የመንዙማ ክዋኔ ስንመለከት፡-

**ቢስሚላሂ ረህማን ረሂይም (2 ጊዜ)** …………….ፈሱል (መለያ)/ አዝማች
**አላሁመ ሶሊ ዐላ ዘይኒል ውጁድ**

በማለት ከዋኙ መንዘማውን ይጀምርና የተቀባዮቹ አዝማቹን ማለታቸውን ረጋግጣል፣ በዚህ ጊዜ ቀጥታ ወደ መንዙማው በመግባት፡-

አልሀምዱ ሊሏሂ ዚይል ጀዋድ፤ዩዕጢይ ወምነዑ ማዩሪይድ፤
ማሊክል ሙሉውኪ ዳኢመን ሙሰርመድ።

**ሲል እነሱ** **ቢስሚላሂ ረህማን ረሂይም (2 ጊዜ)** …………….ፈሱል (መለያ)/ አዝማች
**አላሁመ ሶሊ ዐላ ዘይኒል ውጁድ**

**ከዋኙ**

ያአሏህ ያረህማን ያረሂይም፤ ቀልባችንን አርገው ረሂምይ፤
እሚያዝን የሆነ ለባዳ ለዘመድ።

**ተቀባዩቹ** **ቢስሚላሂ ረህማን ረሂይም (2 ጊዜ) …………….ፈሱል (መለያ)/ አዝማች**
**አላሁመ ሶሊ ዐላ ዘይኒል ውጁድ**

**ከዋኙ**

ያአሏህ ያማሊክ ያቁዱውስ፤ ቀልባችን ያረቢ አይደፍርስ፤
አንችለውምና ያረቢይ ያሶመድ።

**ተቀባዩቹ** **ቢስሚላሂ ረህማን ረሂይም (2 ጊዜ) …………….ፈሱል (መለያ)/ አዝማች**
**አላሁመ ሶሊ ዐላ ዘይኒል ውጁድ**

**ከዋኙ**

ያአሏህ ያከሪይም ያጀዋድ፤ ሸልመን ዘይነን በአውራድ፤
እሚያደርስ የሆነ ከሀድረተ ሹሁውድ።

**ተቀባዩቹ** **ቢስሚላሂ ረህማን ረሂይም (2 ጊዜ) …………….ፈሱል (መለያ)/ አዝማች**
**አላሁመ ሶሊ ዐላ ዘይኒል ውጁድ**

**ከዋኙ**

ያአሏህ ያወሓብ ያሀናን፤ ቀልባችንን ሙላው በኢማን፤
እንዲያምር ስራችን በቀጥታው መንገድ።

…

እያሉ የመንዙማውን ክዋኔ እስከፍጻሜው ይጨርሳሉ፡፡ በዚህ መንዙማ ከመጀመሪያው በተሻለ ፍጥነት (እኩል በሚባል ደረጃ) ከዋኙና ተቀባዮቹ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ በሚከወንበትም ሰዓት ከፍተኛ የሆነ ጭብጫቦና የድቢ ድምጽ ከእንቅስቃሴ ጋር ያጅቡታል፡፡ በክዋኔ ወቅትም ሁሉም ተሳታፊዎች ቆመው የሚፈጸም ሲሆን በዚህን ጊዜ "ሐድራው ደራ" ይባላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ቤት መምታቱን ተከትሎ ሚደረገው የከዋኝና ታዳሚ ቅብብሎሽ ሌላ የመንዙማው ግጥም ስንኝ እኩሌታ (ሐረግ) ላይ ተሳታፊዎቹ እየገቡ ፈሱል (መለያ)/ አዝማች የሚሉበትንም ክዋኔ ለመስተዋል ችያለሁ፡፡ ለዚህም ማስረጃነት የሚከተለውን የመንዘዙማ ግጥም መመልከት ልብ ይሏል፡፡

*ሶለአሏሁ ዐላ ሙሀመድ፤*
*ሶለአሏሁ አለይሂ ወሠለም፡፡*...........**ፈሱል (መለያ)/ አዝማች**
አልሀምዱ ሊሏሂል ሀሊይም፤/ ወኒዕመል ጀዋዲ ረሂም፡፡
አልሀምዱ ሊሏሂል ከሪይም፤/ ወኒዕመል ወሓቡል ዐሊይም፡፡
አልሀምዱ ሊሏሂል ሙንዒይም፤/ ወኒዕመል መናኒል ሀኪይም፡፡
ነሥኣሉ ሪዷ  ያዐሊይም፤/ ቢፈድሊን ሚንከ የረሂይም፡፡
ለመነህ ኣንተ ያከሪይም፤/ ዲይነን ወዱንያ ሁሉንም፡፡

ከዋኙ በዚህ የመንዙማ ግጥም ክዋኔ ልክ ድርብ ሰረዞቹ ላይ ሲደርስ ታዳሚዎቹ "ሶለአሏሁ ዐላ ሙሀመድ፤ ሶለአሏሁ አለይሂ ወሠለም፡፡" የሚለውን ፈሱል (መለያ)/ አዝማች ይላሉ፡፡ ይህም እስከ መንዙማው ፍጻሜ የሚዘልቅ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ ከላይኖቹ ሁለቱ መንዙማዎች በተለየ መልኩ ቅብብሎሹ በእጅጉ ይፈጥናል፡፡ ተሳታፊዎቹም ከከዋኑ በላይ ክዋኔውን ይቆጣጠሩታል፡፡

### ለ. በእንጉርጉሮ የሚቀርቡ መንዙማዎች

በእንጉርጉሮ የሚቀርቡት መንዙማዎች ብዙ ጊዜ በአንድ ሰው የሚባሉ (የሚከወኑ) ሲሆን አልፎ አልፎ ግን በጋራ ይከወናሉ፡፡ ይህንንም በተመለከተ የመውሊዱ ተሳታፊ ነበሩት ሼህ ሲራጅ ጀማል ጋር በ09/ 06/2005 ዓ.ም ባደረኩት ቃለ መጠይቅ፡-

> በእንጉርጉሮ የሚቀርቡ መንዙማዎች ብዙ ጊዜ "ሃዬ" በመባል ይጠራሉ፡፡ ይህ የሚባለው በአንድ መልካም ድምፃዊ እንጉርጉሮ ብቻ የሚከናወን መንዙማ ነው፡፡ ድምፃዊው ሃይማኖታዊ ስብከት፣ የነቢያት ውዳሴና የማህበራዊ ችግር ብሶቶችን የሚያንፀባርቁ ግጥሞችን በአማርኛ ቋንቋ ሲያዘንብ ሌላው ታዳሚ በተመስጦ በማዳመጥ ይሳተፋል፡፡

ብለውኛል። ይህን ጉዳይም ብርሐኑ ገበየሁ የወሎ እስላማዊ ግጥሞችን አይነት በአራት[45] በከፈለበት ምዕራፍ፡-

> *አራተኛው የግጥም ዘር ሃዩ ሲሆን ራስን የመግለጽ እንደሆነ ያስረዳል። ይህ ዘር መድሃኒትነት ያለው፣ ተከታታይ ሙዚቃዊና ግለሰብን የሚገልጽ ግጥም የሚቀርብበት ነው። ግጥሙ በሴቶችም በወንዶችም ይቀርባል። የዚህ ግጥም የታወቁ አጋጣሚወች ወዳጃና ሃድራት ናቸው።አንዳንዴ በሌሎች እስላማዊ አጋጣሚዎች ሊቀርብ ይችላል። ሃያ በአንድ ከዋኝ ብቻ የሚቀርብ የግጥም አይነት ነው።የዚህ ግጥም ታዳሚዎች ከዋኙን በጽሞና ከማድመጥ ያለፈ ሚና የላቸውም።ይህ የግጥም አይነት እንደሌሎቹ የመክፈቻና የመዝጊያ ቀመርም የለውም።*

በማለት ይገልጸዋል። እዚህ ላይ በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በአል ስርአተ ክዋኔ ይህ ዘር ሲወን ባስተውልም መውሊድ ላይ ግን በሴቶች እንደማይባል ለማረጋገጥ ችያለሁ። ይህንን ክዋኔ ለአብነት በሚከተለው የመንዙማ ግጥም ውስጥ እንመልከት፡-

ቢስሚ፝ሂ ብለን ብዙ እናመስግን፤ ለኣለሙ ሺፋ ኡመት ላረገን።
…
ብታመሰግኑኝ ልጨምር አለን፤ እንዲህ ያለ ሲሆን ምን ዝም አሰኘን።
…
በሙልክህ በቁድራህ አርቅ ሠታሪን፤ ዐዱው ሸይጧንን ውድቅ አድርግልን።
…
ያረህማን ያረሂይም አሁን አርግልን፤ በኸለቅከው ነቢይ አድርገህ መዕዲን።
…
ያማሊክ ያቁዱውሥ በረህመት ሙላን፤በሙሀመድ ኣሚይን ባረከው አማን።
…
ያሠላም ያሙውእሚን ሰሊይም አድርገን፤በላይም በውስጥም እማንኸይን።

---

[45] የነዚህ አራት የቃል ግጥም ዘሮች ትንታኔም ተሰጥቷል።በዚህ መሰረትም **ታውህድ** የተሰኘው የግጥም ዘር ከሌሎቹ አንጻር ተዘውታሪ የግጥም አይነት ነው።ይህ ግጥም ሲከፈት ፈጣሪን በማመስገን ነው።ተዋህድ የተሰኘው የግጥም ዘር ጎላ ያለ ፈጠራዊነት እና ምናባዊነት የሚታይበት ነው። ገጣሚው አብዛኛዎቹን ምእናባዊ ገለጻዎች የሚያመጣው ከቁርአን ነው።ሁለተኛው ዘውግ **ማልክ ወይም ማልህ** ሲሆን ይህ ዘውግ ገላጭ የግጥም አይነት ነው። ማልክ የተሰኘው የግጥም ዘር የአላህን፣ የነብዩ ሙሃመድን ወይም አውሊያን ስም እየጠራ በነሱ የተገኘውን ነገር የሚያትት ነው። ይህ ዘውግ ባጫጭር ቅርጽ የሚቀርብ ነው። በተጨማሪም የቅዱሳንን አካላዊ ገለጻ በሚያሳዩ በርከት ባሉ ምስሎች የሚቀርብ የግጥም አይነት ሲሆን በውስጠ ታዋቂነት ግን ምግባር የሚገልጹ ግጥሞች የሚቀርቡበት መሆኑን ነው። ሶስተኛው የግጥም ዘር "**ቂሳ**" ሲሆን ተውኔታዊ ትረካ የሚታይበት ነው።ይህ የነብይና የአውሊያ ተአምራት የሚቀርብበት ነው።በዚህ ዘር የሚቀርቡት ለማመን የሚያዳግቱ ተጋድሎዎች እንደ ቅዱስና እውነት የሚወሰዱ ናቸው።ይህ ዘውግ ቅዱሳን ታሪኮች የሚቀርቡበት በመሆኑ የሚቀርበውም በቅዱስ ቦታዎችና ጊዜ ነው።ለምሳሌ መውሊድ፣ ኢድ-አል-አድሃ፣ አመታዊና መደበኛ ዝያራትና ወዳጃ ናቸው።ይህ ግጥም አቀንቃኞች ሲያቀነቅኑ ሊሎች ተቀባዮች በመከተል የሚያስኬዱት ነው። አራተኛው የግጥም ዘር **ሃያ** መሆኑን በመግለጽ ከላይ ያቀረብኩትን ማብራሪያ ያቀርባል። እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚገባው ጉዳይ ብርሐኑ ገበየሁ ከይዘት አንጻር አይነታቸውን የመደበ ሲሆን የኔ ጥናት ደግሞ ከመቅረቢያ (ከመነወኛ ስልታቸው) አንጻር የተጠና ነው። በመሆኑም በብርሐኑ የተነሱት ሶስቱ ይዘቶች በድቤ ይቀርባሉ።

እያለ ቀስ ባለ ድምጸት ያንጎራጉራል። ታዳሚውም በመሐል በመሐል “አጀብ”፣ “እህህህ……” (በግርምት ድምጸት) የመንዙማውን ክዋኔ ይከታተላል። በዚህ ክዋኔም በቀጥታ በነበረኝ ምልከታ እንዳስተዋልኩት ታዳሚዎቹ ከዋኙን በጽሞና ከማድመጥ ያለፈ ሚና የላቸውም። ከዚህ በተጨማሪም ይህ ክዋኔ በድቤ እንደሚቀርቡት መንዙማዎች የመክፈቻና የመዝጊያ ቀመርም የለውም።

በአጠቃላይ የነዚህን የቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ በቦታው ተገኝቼ ስከታተልና ከመረጃ አቀባዮቸ ካገኘሁት መረጃ በመነሳት የቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ በተመለከተ ሶስት ነገሮች ለመጠቆም እወዳለሁ። የመጀመሪያው የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓል ላይ የሚቀርቡ ቃላዊ ግጥሞች መወድስነታቸው አላህንና ነብዩ ሙሀመድን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቃላዊ ግጥሞቹ በአብዛኛው ማንነትን የሚገልጹና “እኛ” በሚል ድምጸት የቀረቡ ናቸው። ሶስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ በድቤ የሚቀርቡት የመንዙማ ግጥሞቹ ቃላዊ ክዋኔ በየአዝማቾቹ መጨረሻ ላይ ከዋኙ ከታዳሚዎቹ ማረጋጫ የሚፈልግና የነሱን መስማማት በጋራ ካልገለጹለት ወደ ቀጣዩ ስንኝ የማይሻገር ሲሆኑ በእንጉርጉሮ በሚቀርቡበት ግን የታዳሚው ሚና በጽሞና ማዳመጥ መሆኑን ነው።

ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ነብዩ ሙሀመድን ለማወደስ በመውሊድ ክብረ በዓል ላይ  የቀረቡት የመንዙማ ግጥሞች በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ  ከማኅበራዊ፥ ታሪካዊ፥ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ጠቀሜታ በተጨማሪ ያላቸው ባህላዊ፣ ፎክሎራዊና ሥነ ጥበባዊ ዋጋ እጅግ ከፍተኛ ነው:: ምናልባት ግጥሞቹ ማን ደረሳቸው የሚለውን በእርግጠኝነት መናገር አይቻል ይሆናል:: ይሁን እንጂ የተለያዩ የታሪክ፣ የሥነቃልና የፎክሎር መረጃዎችን በመሰብሰብና በጥንቃቄ በማጥናት፣ ታዋቂ ሼሆችንና የእስልምና ሊቃውንትን በማነጋገር ግጥሞቹ በነማን ስለመገጠማቸውና ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ስለመተላለፋቸው ሰፊ ጥናት በማካሄድ በርግጠኝነት መናገር ይቻል ይሆናል::[46]

---

[46] ይህ ግላዊ አስተያየቴ የመነጨው በጽሑፉ ውስጥ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ሰፋ ባለ ጥናት ታሪክን፥ ባህልን፥ ልማድንና እምነትን መሠረት ያደረጉ ክፍለ ሀገራዊና እምነታዊ፤ ፎክሎራዊና ታሪካዊ ሁናቴዎችን በመመርመርና በማገናዘብ ስለ ግጥሞቹ አጠቃላይ ፍንጭ ማግኘት ይቻላል። ከሚለው ከመምህሬ ዶ/ር ባይለየኝ ጣሳው በክፍል ውስጥ ገለጻ ካገኘሁት እውቀት በመነሳት ነው።

በፎክሎር ጥናትና ምርምር፣ በተለይም ክዋኔን መሰረት ያደረጉ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት፤ እያንዳንዱ የክዋኔ ሒደቶች ምንነትና ለምን እንደተከወኑ ጭምር መገለጽ እንዳለበት ትኩረት ሰጥተው ያትታሉ። በዚህ መውሊድ በዓልም የቃላዊ ግጥሞችን ክዋኔ ባስተዋልኩበት ወቅት መንዙማውን በዋናነት ሲሉት (ሲያቀነቅኑት) የሰማሁት ወንዶች በመሆናቸው መንዙማን ለማቀንቀን (የክዋኔው መሪ ለመሆን) ምን ያስፈልጋል? የመንዙማዎቹ ደረሳ መቼና እንዴት ይከናዎናል? የተፈቀደውስ ለማነው? የሚሉ ጥያቄዎችን አንስቼ ጠይቄ ነበር። ከዚህም ለመረዳት እንደቻልኩት መንዙማ ራሱን የቻለ ጥበብ እንደመሆኑ መጠን የተለያዩ ተሰጥዖዎችን ይፈልጋል። የመጀመሪያውና ወሳኙ መንፈሳዊ መሆንና ግጥም ማፍለቅ ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ በግሩም ሁኔታ የተሰናዳውን ግጥም ጆሮ ገብ በሆነ ድምፅ አሳምሮ ማዜም ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአሁኑ ሰዓት የሚደመጡት ግጥማቸው የተፃፈው ከክ/ዘመናት በፊት ነው።[47] እነዚህ ጸሀፊያን ደግሞ በሁሉም የሐገራችን ክፍሎች የሚታወቁ ነበሩ።[48] ግጥሙንም የሚፅፉት ገግሞ የሆነ ነገር ሲበራላቸው (ሲገለጽላቸው) መሆኑን ለመረዳት ችያለሁ። የተደረሱት ግን ከዚህ ቦታ ነው ብሎ ለመናገር እንዳላስቻለ የተለያዩ የእምነቱ ሊቆችን ባነጋገርኩበት ወቅት ለመረዳት ችያለሁ።

የመንዙማ ቃላዊ ግጥሞችን ለማቀንቀን የተፈቀደውስ ለማነው? በሚለው ጥያቄ ላይ ሐጅ ሙሀመድ ኑር አብደላ ከሰጡኝ ገለጻ እንደተረዳሁት ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ ተደባልቀው ማዜም አለመቻላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መንዙማ "የወንድ" / "የሴት" ተብሎ የተከፈለ አይደለም። የተወሰኑ መስመሮችን ከፍ ብሎ እንደሰፈረው መንዙማ በአብዛኛው የሚባለው ‹‹ወዳጃ››[49] ላይ እንደመሆኑ መጠን ሴቶች የራሳቸው በሆነው ‹‹ ወዳጃ›› ላይ ከወንዶች ባልተናነሰ ሁኔታ መንዙማን ያንቆረቁሩታል። (በነገራችን ላይ ‹‹ዱበርቲ›› ማለት በኦሮምኛ ሴት ማለት መሆኑን ልብ ይሏል)

---

[47] ከሼህሐጅ ሙሀመድ ኑር አብደላ፣ ከሼህ አብዱልቃድር ፈድሉ፣እና ከሼህ ኡስማን ሞላ በዕለቱ በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ።

[48] በጣም ታዋቂ ከነበሩ የመንዙማ ገጣሚዎች ውስጥ በራያ አካባቢ በ19ኛው ክ/ዘመን የኖሩት ዘመን አይሽሬ ግጥሞችን በአረብኛ ያበረከቱት ሼህ ጀማል አል ዲን አል አኒና ተማሪዎቻቸው ሼህ ሲራጅ ውዲን እንዲሁም ሼህ አህመድ አመዲን፣ በ20ኛው ክ/ዘመን ደግሞ ሼህ ጫሊና ሼህ አደም ደርቃ የወሎ ኗሪ የነበሩ በአማርኛ ቋንቋ መንዙማ የገጠሙ ሊቆች መሆናቸውን በቃለ መጠይቅ ወቅት ከገለጻቸው ለመረዳት ችያለሁ።

[49] ሌላኛው የዱአ ወይም ሐድራ መጠሪያ ነው።

### 4.2.2 በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ ክብረ በአል ላይ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች

በዚህ ንኡስ ርዕስ የመውሊድ ክብረ በዓልን ክዋኔ ለማጀብ ወይም ለማድመቅ ከሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች መካከል የቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎችን ለመዳሰስና ማህበራዊ ፋይዳቸውን ለመግለጽ እሞክራለሁ፡፡ እነዚህን ቁሳዊ ባህሎች መመልከት ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ደግሞ ክብረ በዓል ሲታሰብ ከበራውን ሙሉ ከሚያደርጉት አላባዊያን መካከል አንዱ በመሆናቸው ነው፡፡[50] ስለ ቁሳዊ ባህል ሲነሳ በመጀመሪያ በአዕምሯችን የሚመጣው ቁሳዊ ባህል ዋና ትኩረቱ የሰው ልጅ የፈጠራ ችሎታውን ተጠቅሞ የሚያመርታቸውን ተጨባጭ የሆኑ የመገልገያ መሳሪያዎችን የአሰራር ቴክኒክ በተለይም በባህላዊ መንገድ የተበጁትን ቁሶች የሚያመለክት መሆኑን ነው፡፡

እርግጥ ነው የቁሳዊ ባህል ጥናት መሰረታዊ ጉዳይ ቁስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቁሱን ብቻ ተመልክቶ ቁሱ የተሰራበትን ንጥረቁስ እና አገልግሎት መግለጽ ብቻውን በቂ አይሆንም፤ የጥናት መስኩ አላማም አይደለም፡፡ ዋና ጉዳዩ ቁሱን ስለሰሩት የሰው ልጆች ማህበራዊ፥ ባህላዊ፥ ሀይማኖታዊ፥ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ. ጉዳዮች እያነሱ መፈከር ነው፡፡ ስለዚህ በመውሊድ ክብረ በአል ካስተዋልኳቸው በርካታ ቁሳዊ ባህሎች መካከል **የቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች** (ድቤ፣ የድቤ መምቻና ከበልን) ለመዳሰስ እሞክራለሁ፡፡

#### ሀ. ድቤ

ድቤ በመውሊድ በዓሉ ላይ የቃላዊ ግጥሞችን ክዋኔ ለማድመቅ ከሚገለገሉበት ቁሳዊ ባህል ውስጥ በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡ ይህ መሳሪያ በተለያዩ የእስልምና ክብረ በዓሎች ላይ በስፋት ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን በመውሊድ በዓል ደግሞ የተለየ ስፍራ ይሰጠዋል፡፡ ለዚህ የሚጠቀሰውን ምክንያት በተመለከተ ከሼህ ከሼህሐጅ ሙሀመድ ኑር አብደላ፣ ከሼህ

---

[50] ይህን ሀሳብ በተመለከተም Sims እና Stephens (2005፣95) እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

*…Rituals are frequently highly organized and controlled, often meant to indicate or announce membership in a group. Most rituals bring together many types of folklore: verbal, such as chants, recitations, poems or songs; customary, such as gestures, dance or movements; and material, such as food, books, awards, clothing and costumes…*

አብዱልቃድር ፈድሉ፣እና ከሼህ ኡስማን ሞላ በቀን 09/06/2005 ዓ.ም በነበረኝ ቃለ መጠይቅ የሚከተለውን ምላሽ አግኝቻለሁ፡፡

> ድቤ የእስልምና እምነትን ከሚወክሉ ቁሳቁሶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ልክ ገና ድቤ ሲመታ ስትሰማ (በሩቅ እንኳ ቢሆን) በቀጥታ አዕምሮህ ውስጥ የሚመጣው የእስልምና እምነት ነው፡፡ በቅርብ ሆነህ ስትሰማው ደግሞ ውስጥህ የሚፈጠረው ደስታና ሀሴት እንዲህ ነው ብዬ ልነግርህ አልችልም፡፡ ልብህ ድረስ ዘልቆ ይሰማል፣ እንድትዘል ያደርገሀል፣......

ድቤ እንጨት ተቆርጦ ተጠርቦ ይሰራል፡፡ የእንጨቱ አይነት ባህር ዛፍ፣ ዋንዛ... ሊሆን ይችላል፡፡ አሰራሩንም በአጭሩ ለመግለጽ ያህል፡፡ በመጀመሪያ የተቆረጠው እንጨት እንደ “ቆሪ” (ባህላዊ የሊጥ ማቡኪያ ገንዳ) ከሰፊው የእንጨት ክፍል ወደ ጠባቡ አናቱ/ጭንቅላቱ ይፈለፈልና እንዲጎደጉድ ይደረጋል፡፡ በመቀጠል ይህን ገንዳ በከብት ቆዳ ይለበጣል፡፡ ከዚህ ላይ ግን ቆዳው የጭንቅላት ቢሆን ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም በቀላሉ ለመለበጥም ሆነ ለመስፋት ምቹ ስለሚሆን ነው፡፡ በመቀጠል ከቆዳ በሚዘጋጅ ጠፍር/ችንጋ ይሰፋል፡፡ ከዚያ ከ8-10 ቀን እንዲደርቅ ፀሀይ ላይ ይቆያል፡፡ በመጨረሻው ደርቆ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ሊጥ ይቀባል፡፡ ይህን የሚያደርጉት ጥሩ ድምጽ እንዲያወጣ በሚል እሳቤ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ለጥቅም ዝግጁ ስለሆነ መጠቀም ይቻላል፡፡ ከዚህ ላይ ሁልጊዜም ቢሆን ጥሩ ድምጽ እንዲሰጥ ድቤ ከመመታቱ በፊት ፀሀይ ወይም እሳት ይሞቃል፡፡

መንዙማ በሚባልበት ጊዜ ድቤ መችው ሰው የተመረጠና ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም አንዱ ሓድራ አራት አይነት ድምጽ ሲኖረው የከዋኙን የአፍ እንቅስቃሴና የድምፀት ቅየራ በቅጽበት በመረዳት/በመናበብ ምቱን መቀያየር መቻል አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ የክዋኔው ሂደት ስለሚስተጓጎል ተሳታፊዎቹ ፍዝ ይሆናሉ፡፡ ክዋኔ ደግሞ ንቁ ተሳታፊዎችን እንጂ ፍዝ ተሳታፊዎችን አይፈልግም፡፡

### ለ. የድቤ መምቻ

የድቤ መምቻ እነዚህ ሁለት አጫጭር ዱላዎች በቀላሉ ከባህር ዛፍ ሊዘጋጁ የሚችሉ ሲሆን ጫፋቸው በጨርቅ ይጠቀለላል፡፡ ይህ የሚሆነው በሁለት ምክንያት ሲሆን አንደኛው ዱላው ድቤውን እንዳይጎዳው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጥሩና ወፈር ያለ ድምጽ እንዲሰጥ ነው፡፡

### ሐ. ከበል

ከበል ከእንጨት የሚሰራ ማጨብጨቢያ ሲሆን ድቤውን በማጀብ መንዙማውን የሚያደምቅ ነው፡፡ አሰራሩም ሁለት ትናንሽ ጣውላዎችን ባላ በመሰለ ቅርጽ አጠላልፎ በማሰር ጫፍ ላይ በአንድ በእጃቸው ይዘው ሲያንቀሳቅሱት ደመቅ ያለ የጭብጨባ ድምጽ የሚፈጥር ባህላዊ መሳርያ ነው፡፡ ይህን መሳሪያ በከበራው ወቅት የተወሰኑ ሰዎች ብቻ (ከሐረር አካባቢ የመጡ) ይጠቀሙበታል፡፡ ከአቶ መህመድ ያሲን ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ "ይህን መሳሪያ በተለይ አደሬዎች በመውሊድ በአል በስፋት እንደሚጠቀሙበትና ምክንያታቸውም እጃቸው ስስ በመሆኑ ሓድራውን ለማድመቅ ለበለጠ ተመራጭ ስለሆነ ነው" በማለት ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በመውሊድ በአል ከበራ ላይ የቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎችን (ድቤ፣ የድቤ መምቻና ከበል) ከአሰራራቸው ግልጋሎታቸው ወጣ ብለን ማህበራዊ፥ ባህላዊ፥ ሀይማኖታዊ ጉዳይ ጋር አያይዘን ስንመረምር ቁሶቹ የሚከተሉትን ሶስት ባህሪያት ይዘው እናገኛቸዋለን፡-

የመጀመሪያው የተፈጥሮአዊና የተለጣፊ እሴት ባለቤትነት ይዘው እናገኛቸዋለን ፡፡[51] በዚህም መሰረት በማንኛውም አውድ ውስጥ ሆነን "ድቤ"ን፣ የድቤ መምቻና ከበልን ስናስብ በቀጥታ የሚመጣብን የእስልምና ሐይማኖት መንዙማ ክዋኔ መሆኑ አያጠራጥርም፤ ምክንቱም ቁሶቹ የተሰሩባቸውን ንጥረ ቁሶች እንደፈለግን በየትም ቦታ የማናገኛቸው መሆኑ የበለጠ እሴት ወይም ዋጋ እንድንሰጣቸው ያደርገናል፡፡ ይህ በተፈጥሮ እንደልብ ያለመገኘት ጉዳይ የቁሶቹን እሴት ቀጣይ ያደርገዋል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ታሪክ ነቃሽነት (Surviving Historical Events) ፡- ድቤ፣ የድቤ መምቻና ከበልን ተመልክተን (አጥንተን) በረጅም ዘመን ስለተፈጸመ  የእስልምና ታሪክ ወይም ድርጊት የሚነግሩን ቁም ነገር አላቸው፡፡ ምክንያቱም ቁሶች በአንድ በተወሰነ አካባቢና የጊዜ ገደብ ውስጥ መጠነኛ የሆነ ለውጥ በማሳየት ረጅም እድሜ ይቆያሉና ፡፡ በዚህም መሰረት ድቤ፣ የድቤ መምቻና ከበል  ስለአለፈው ወይም ስላልኖርንበት ዘመን የመውሊድ ክብረ በዓልን ክዋኔ

---

[51] ይህን ሐሳብ በተመለከተም (Prown, 1982፡3) "The most obvious cultural beliefs associated with material objects has to do with value". ብዙ ጊዜ ቁሶች የተለየ እሴት ባለቤት ሆነው ይገኛሉ፡፡ ይህንን እሴት አንድም በተፈጥሮ ወይም ሰው ራሱ ይጭንባቸዋል፡፡ በማለት ይገልጸዋል፡፡

ታሪክ ለማወቅ እድል ይሰጡናል፤ ዋቢ ምስክሮቻችንም ናቸው፡፡[52] በመሆኑም እነዚህ ድቤ፣ የድቤ መምቻና ከበልን በታሪክም ሆነ በቁሳዊ ባህል የጥናት መስክ ስለ እስልምና ሁለንተናዊ ባህልና ታሪክ ለማወቅ የሚያስችሉ መሳሪያዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ሶስተኛውና የመጨረሻው የበለጠ ተወካይነት (More Representativeness) የመውሊድ ክብረ በዓል ላይ የሚከወኑ መንዙማዎችን ለማጀብ ወይም ለማድመቅ ከሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች በጽሁፍ ከተገኘ መረጃ የበለጠ ተወካይነት አላቸው፡፡ ይህም ማለት ድቤ፣ የድቤ መምቻና ከበልን በአብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል የተማረውም ሆነ ያልተማረው፥ ደሀውም ሆነ ሀብታሙ፥ በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖረው ህዝብ ይገለገልባቸዋል ማለት ነው፡፡ ይህም ሲባል የሚነበቡት ወይም በቃል የሚባሉት መንዙማዎች ከቦታ ቦታ ሲለያዩ እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ግን ተመሳሳይ ናቸው ማለት ነው፡፡

### 4.3 የመውሊድ ክብረ በአል ተግባር (Function)

ፎክሎር በርካታ ተግባሮች ያሉት ሲሆን፡ ይህንንም በማስመልከት William R. Bascom (1965፣ 279—298) የፎክሎርን ተግባር (escape, validation, education, and social control) በማለት በአራት ይከፍላቸዋል፡፡ ከዚህም በመነሳት ሼህ ሁሴን አለሙን ምክንያት በማድረግ የሚከበረው የመውሊድ ክብረ በዓል ያሉትን ተግባራት (Functions) እንደሚከተለው ማስቀመጥ ያቻላል፡፡ የማጠናከር (የመትከል) ተግባር አለው፡፡ ይህንንም ከላይ ሐጅ ሐሩን ሙሳን ጠቅሽ እንደገለጽኩት በመውሊዱ የነብዩ መሐመድ ስራዎች በመንዙማዎች ስለሚወሱ የሳቸውን አርአያ በዓሉን ለመካፈል በመጡ ህጻናት ላይ እምነቱን የማስረጽና የመትከል ተግባር አለው፡፡

ከዚህም በተጨመሪ የመውሊድ ክብረ በዓል የማምለጥ (የማምለጫ) ተግባር አለው ማለት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ይህ ክብረ በዓል ድቤ፣ የድቤ መምቻና ከበልን በመጠቀም መንዙማ በመኖሩ የእምነቱ ተከታዮች ከአሠልችው የእለት ተዕለት የህይወት ወጣ ውረድ በማምለጥ ዘና ይሉበታል፡፡[53] ሌላውና የመጨረሻው የመውሊድ ክብረ በዓል የማስተማር ተግባር አለው፡፡

---

[52] ይህንን ሀሳብ በተመለከተ Prown፣ (1982፡3). የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝሯል፡፡
Objects created in the past are the only historical occurrences that continue to exist the present. They provide an opportunity by which we encounter the past at first hand; we have direct sensory experience of surviving historical events.

[53] ይህን ጉዳይ በተመለከተ ከላይ "4.1.2.4 መንዙማ" በሚለው ክፍል ከመውሊዱ አስተባባሪ ሼህ ኡስማን ሰኢዱ ጋር ያደረኩትን ቃለ. ልብ ይሏል፡፡

ይህን በተመለከተም ከሐጅ ሐሩን ሙሳ (የታላቁ አኑዋር መስጊድ ኢማም) ጋር ባደረኩት ቃለ መጠይቅ፡-

> በተለይ ከሰላማዊ ትምህርት ርቆ የሚገኙ ሰዎች (በንግድና በምርምር) በእንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ካልሆነ በስተቀር ስለሳቸው ብዙም ግንዛቤ ስለማያገኝ ዕለቱን በነብዩ ዙሪያ ላይ በማተኮር አስፈላጊውን ትምህርት እሚሰጥበት አጋጣሚ ነው።

በማለት ይገልጻሉ። ስለዚህ ከበራው በተለይ ከሰላማዊ ትምህርት ርቆ የሚገኙ ሰዎች እና ማንበብባ መጻፍ ለማይችሉ ሰዎች በነብዩ ዙሪያ ትምህርት እሚሰጥበት አጋጣሚ ነው።

## 5. ማጠቃለያና አስተያየት

ይህ የጥናቱ የመጨረሻ ክፍል ሲሆን የጥናቱ ግኝቶች እና ከግኝቶቹ በመነሳት የአጥኚው ይሁንታ የቀረበበት ነው፡፡

### 5.1 ማጠቃለያ

ጥናቱ በአዊ ዞን ዳንግላ ከተማ የሚከበረውን የሼህ ሁሴን ዓለሙ የመውሊድ በአልና ቃላዊ ግጥሞቹን (መንዙማዎቹን) ክዋኔ መተንተንን አላማ አድርጎ የተካሄደ ነው፡፡ ይህ ሲካሔድ ክዋኔውን በሆነቶች በመከፋፈል ለመመርመር ጥረት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ከቃላቂ ግጥሞቹ ክዋኔ ጋር ተያይዘው ሚነሱትን ቁሳዊ ባህሎች አሰራር፣ ጥቅማቸውና ትርጓሜያቸውን ለማየት ተሞክሯል፡፡

የጥናቱን አቢይ አላማዎች ከግብ ለማድረስም አጥኚው በመስክ ቆይታው ቃለመጠይቅን÷ ምልከታን እና ተተኳሪ ቡድን ውይይትን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተገልግሏል፡፡ መረጃዎቹም በተፈጥሮአዊ መቼት የተገኙ ሲሆን በቴፕ÷ በቪዲዮ ካሜራ እና በፎቶግራፍ ምስል ተቀርጸዋል፡፡ በሶስቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መስክ ላይ የተሰበሰቡት መረጃዎች በክፍል ሁለት በተከለሱት ትውሮች በመታገዝ ለመተንተን የተቻለ ሲሆን የትንተናው ውጤትም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በአል ስርአተ ክዋኔ በዋዜማው በሚደረጉ ልዩ ልዩ ቅድመ ዝግጅቶች ይጀምራል፡፡ ይህ የስርአተ ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት ደግሞ መውሊዱ ሥርአቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን የሚያስችሉ ስራዎች የሚከናወኑበት ነው፡፡ በዚህም ጊዜ ለምግብ ማብሰያ የሚያገለግል የማገዶ እንጨት ዝግጅት፣ የአካባቢ ጽዳት፣ የምግብ ዝግጅት (ጤፍ የማበጠር፣ ቅመማቅመሞችን የማዘጋጀትና ማስፈጨት)፣ የዳስ (ድንኳን) ስራ እና የቁሳ ቁስ አቅርቦት የሚያካትት ነው፡፡ ስራው ሲከናወን ደግሞ የአካባቢው ማህበረሰብ እስላም ከክርስቲያኑ ጋር በጋራ ይፈጽመዋል፡፡ ይህ ሆነው ደግሞ አካባቢው ህብረተሰብ ማህበራዊ መስተጋብር የጠነከረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመውሊድ በዓሉ የአከባበር ስርዓት ላይ በዋናነት የተስተዋሉትን የክዋኔ ሁነቶች ዚያራ፣ ዱኣ፣ ምርቃት እና መንዙማ ናቸው፡፡ የነዚህ ሁነቶች አጠቃላይ መጠሪያ "ሐድራ" ሲሆን "ዱኣ" የሚለውን ምትክ እንደሆነ በጥናቱ ተጠቁሟል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሁነቶቹ አንዱ ከአንዱ ጋር ጥብቅ የሆነ ቁርኝት ያላቸው እንደመሆናቸው ተሳታፊዎቹም ይህንን አውቀው

ይፈጽሟቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ በዓል ስርአተ ክዋኔም በዋዜማው በሚደረጉ ልዩ ልዩ ቅድመ ዝግጅቶች እንደመጀመሩ ሁሉ የራሱ የሆነ ማጠቃለያ አለው፡፡ በዚህ ሽኝትም ምእመኑ ወደመጣበት ሲመለስ የተህሊል ውኂ ለመድሐኒትነት እየያዙ እንደሚሄዱና ፈውስን እንደሚያገኙ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሼህ ሁሴን አለሙ የመውሊድ ክብረ በአል ላይ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞችና ቃላዊ ጥሞቹን ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች በተመለከተ ‹‹መንዙማ›› ቃሉ የአረብኛ ሲሆን፣ በጥሬትርጉሙ ‹‹ቃላትን በጥሩ ሁኔታ ማስቀመጥ›› የሚል ፍቺ እንደሚተጥና ጥሬ ትርጉሙ በደንብ ሲብራራ ደግሞ ቆንጆ መልዕክትን ለማስተላለፍ የሚያገለግል ግጥም መሆኑን፤ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ መንዙማ ከግጥምም በላይ ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ ምክንያቱም መንዙማ ዜማ ተጨምሮበት አላህ የሚመሰገንበት፣ ነብዩ መሐመድ የሚሞገሱበትና የእስልምና ትምህርት የሚሰጥበት ጥበብ እንደሆነ ታውቋል፡፡ በመሆኑም መንዙማ ከኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ጋር ጠበቅ ያለ ቁርኝት አለው ማለት ይቻላል፡፡

በመውሊድ በአል ከበራ በስፋት ከሚስተዋሉ ኹነቶች ውስጥ ደግሞ አንዱ መንዙማ ነው፡፡ የመንዙማ ግጥሞች በተከወኑበት የክዋኔ ሒደት (በሐድራው ላይ በሚቀርቡበት መንገድ) አንጻር በሁለት መንገድ (በድቤና በእንጉርጉሮ) እንደሚባሉ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት በድቤ የሚቀርቡት ክዋኔያቸው አሳታፊ ሲሆን በእንጉርጉሮ በሚቀርቡት ላይ ግን ታዳሚዎቹ ከዋኙን ማድመጥ ሚናቸው መሆኑን ነው፡፡

ከመንዙማዎቹ ክዋኔ ጋር በተገናኘ የቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች (ድቤ፣ የድቤ መምቻና ከበል) በክዋኔው ሂደት ካላቸው ሚና አንጻር፤ ከአሰራራቸው ግልጋሎታቸው ወጣ ብለን ማህበራዊ፥ ባህላዊ፥ ሀይማኖታዊ ጉዳይ ጋር አያይዘን ስንመረምር ቁሶቹ ሶስት ባህሪያት ይዘው እናገኛቸዋለን፡፡ እነሱም የመጀመሪያው የተፈጥሮአዊና የተለጣፊ እሴት ባለቤትነት ናቸው፣ ሁለተኛው ደግሞ ታሪክ ነቃሽነት ናቸው ፣ ሶስተኛውና የመጨረሻው የበለጠ ተወካይነት ሆነው ተገኝተዋል፡፡

በመጨረሻም የመውሊድ ክብረ በአል ተግባር ስንመለከት  የማጠናከር (የመትክል) ተግባር አለው፡፡ ይህንንም የነብዩ መሐመድ ስራዎች በመንዙማዎች ስለሚወሱ የሳቸውን አርአያ በዓሉን ለመካፈል በመጡ ህጻናት ላይ እምነቱን የማስረጽና የመትከል ተግባር አለው፡፡ ከዚህም በተጨመሪ የመውሊድ ክብረ በዓል የማምለጥ (የማምለጫ) ተግባር አለው ማለት

እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ይህ ክብረ በዓል ድቤ፣ የድቤ መምቻና ከበልን በመጠቀም መንዙማ በመኖሩ የእምነቱ ተከታዮች ከአሠልችው የእለት ተዕለት የህይወት ወጣ ውረድ በማምለጥ ዘና ይሉበታል፡፡ ሌላውና የመጨረሻው የመውሊድ ክብረ በዓል የማስተማር ተግባር አለው፡፡ በተለይ ከሰላማዊ ትምህርት ርቆ የሚገኙ ሰዎች እና ማንበብባ መጻፍ ለማይችሉ ሰዎች በነብዩ ዙሪያ ትምህርት እሚሰጥበት አጋጣሚ መሆናቸው በጥናቱ ተመልክቷል፡፡

## 5.2 አስተያየት

ይህ የመውሊድ ክብረ በአል ለማህበረሰቡ እያበረከተው ያለው ማህበራዊ÷ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ግልጋሎት ላቅ ያለ መሆኑን በጥናቱ ለማመልከት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ከጥናቱ አጠቃላይ ውጤት በመነሳት የሚከተሉትን አስተያየቶች ለመሰንዘር እወዳለሁ፡፡

በአሁኑ ሰዓት (በመውሊዱ ክብረ በዓል እንዳስተዋልኩት) ምንም እንኳ በአብዛኛው የሚደመጠው መንዙማ እንደ ጥንቱ በድቤና ከበል ባሉ ባሕላዊ መሳሪያዎች የታጀበ ቢሆንም፣ አልፎ አልፎ በካሴትና በሲዲ በሚወጡ መንዙማዎች ላይ ግን በዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የታጀቡ መንዙማዎችም መደመጥ ጀምረዋል፡፡ ይህም ድርጊት ጥበቡን እንዳያዳክመውና ባሕላዊ ለዛውን እንዳያሳጣው የሚያሰጋ ጉዳይ መሆኑን ከጥናቱ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ነገር ግን የቀረቡት እነዚህ የመንዙማ ግጥሞች በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ከማኅበራዊ፥ ታሪካዊ፥ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ጠቀሜታ በተጨማሪ ያላቸው ባህላዊ፣ ፎክሎራዊና ሥነ ጥበባዊ ዋጋ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ወደፊት ሰፋ ባለ ጥናት ቢጠኑ መልካም ነው ባይ ነኝ፡፡

በአጠቃላይ በአረብኛና በተለያዩ ሀገራዊ ቋንቋዎች በኢትዮጲያዊን የሙስሊሞች የተፃፉ በርካታ የመንዙማ ኪታቦች (መፅሐፎች) በቂ ጥበቃ ተደርጎላቸውና ምሉዕ ሆነው ለአሁኑ ትውልድ አልተላለፉም፡፡ በመሆኑም እነዚህ ቅርሶች አስፈላጊውን ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል እላለሁ፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች

Abrahams, Roger. 1968. *Introductory Remarks to a Rhetorical Theory of Folklore*. Journal of American Folklore 8 l (320): 143-58

Assafa Mammo, (1987) "Some prominent Features of Menzuma in Wollo Region" Addis Ababa University M.A Degree.

Bauman, Richard. (1983). *Handbook of American Folklore*, Journal of American Folklore pp. 362-367. *Dorson R(Ed).*

Birhanu Gabayahu, (1990) "Islamic Oral poetry in Wollo a prelimainary Descriptive Analysis" Addis Ababa University M.A Degree.

Catherine Bell. (1997) Ritual: Perspectives and Dimensions. New Y ork: O x Ford U niversity press,

Dan Ben-Amos. (1993) "Context" in Context. Theorizing Folklore: Toward New Perspectives on the Politics of Culture. The Journal of American Folklore, Vol.52, No. 2/4, pp. 209-226. Published by American Folklore Society.

Goldstein, Kenneth S. (1974) A Guide for Field Workers in Folklore. By Folklore Associates, Inc. Hatboro, Pennsylvania; Republished by Gale Research Company, Book Tower, Detroit,

Jackson, Bruce. (1987) Fieldwork. Urbana and Chicago: University of Illinois Press,

MacDonald, Donald A. (1972) "Fieldwork: Collecting Oral Literature." In Folklore and Folk life: An Introduction. (Richard M. Dorson (Ed.)). Chicago and Landon; the University of Chicago Press,

Rappaport, Roy A. (1992) Folklore, Cultural Performances, and Popular

Ertainments, Ed. Richard Bauman, (249-260). New York, Oxford University Press. .

Sims, M. C and Stephens, M. (2005) Living Folklore: An introduction to the Study People and their Tradition. Logan; Utah state University press.

Terimingham, Spencer (1952) Islam in Ethiopia. Geoffrey Cumberlege; Oxford University Press, London.

Thomas A. Green (Ed). (1997) Folklore an Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art; Santa Barbara, California Denver, Colorado Oxford, England.

ሐሊማ ሙሐመድ (1974) "ለባሌው ሸህ ሁሴን የተገጠሙ ግጥሞች"፣ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

መሐመድ ሁሴን፣ (1997) ፣ "የገበሮች ሼህ የህይወት ታሪክና የበዓላቸው አከባበር"፣ ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ሙሐመድ በረሁ (2002) የሼህ ኡመር አብራር መንዙማዎች ፎክሎራዊ ጥናት"፣ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ሙሀመድ ጀማል፣ (1984) ፣ "በወሎ ክፍለ ሀገር የሼህ ጫሊ የሞሊድ ግጥሞች (መንዙማዎች) ትንታኔ ከቅርጽና ይዘት አንጻር" ፣ ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ሰይድ ሙሐመድ (1997) "የሼህ ሙሐመድ አወል መንዙማዎች ይዘት ትንተና"፣ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ቦጋለ ተፈሪ (1972) "ሼህ ሁሴንና ግጥሞቻቸው"፣ ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አሊ የሱፍ ፣ (1995) ፣ "የሼህ ሙሀመድ ነጃ የህይወት ታሪክ ሐድራቸው ክዋኔና

ግጥሞቻቸው"፣ ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አሸናፊ ምስጉን፣ (1998) ፣ "የሼህ አሊ ጎሬ ታምራት አፈታሪክና የበአላቸው አከባበር በጅጅጋ አካባቢ"፣ ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አብዱልናስር ሐጅ ሀሰን (1982) "የአውተራህም እና የአሽሪፍ ስርአተ አምልኮ በደደር"፣ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ኡመር ዳውድ (1982) "በአዲስ አበባ እስላሞች ዘንድ በመስጊድ ላይ የሚባሉ እንጉርጉሮዎች ጥናት"፣ ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::

ኪሩቤል ሽንቁጤ፣ (1982) ፣ "የቃጥባሬው ሼህ ህይወት ታሪክና የበዓላቸው አከባበር"፣ ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ጥበቡ ሽፈራው (1976) "የሐጅ ነሚድ መንዙማዎች ይዘት"፣ ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ፅጌ ንጋቱ አስጨናቂ ፣ (1982) ፣ "የሼህ ሰይድ ቡሽራ ታምራት አፈታሪክና የሞሊድ በዓል አከባበር በገታ/ወሎ"፣ ዲ.ማ.ጽ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

## ሙዳዬ ቃላት

| | |
|---|---|
| ሀለቷ | ፀባዩዋ |
| ሀምድ | ምስጋና |
| ሃያት | እድሜ |
| ሐላል | የተፈቀደ |
| ሐራም | ክልክል |
| ሒይታም | መጨረሻ |
| መላኢካ | መላእክ |
| መሽሉቅ | ፍጡር |
| መዕፊራ | ምህረት |
| ሙሒቦች | ወላጆች |
| ማህሹር | ቀውጢ |
| ማዕና | ትርጉም |
| ረህመት | ፀጋ |
| ረሱሊላህ | የአላህ መልክተኛ |
| ሪህላ | ነፋስ |
| ሴህረኛ | ሟርተኛ |
| ሰብር | ትዕግስት |
| ሽፍአ | አማላጅ |
| ቀዷ ቀድር | ቀድሞ የተፈረደ (በአላህ) |
| ቀድራ | ሐይል (ችሎታ) |
| ቂያማ ቀን | የምፅአት ቀን |
| በላ | መአት |
| ቢስሚላ ሂ | በአላህ ስም |
| ኑር | ብርሐን |
| አሁዋል | ሁኔታ |
| አሊም | አዋቂ |

| | |
|---|---|
| አልሐምዱሊላሒ | ለአላህ ምስጋና ይግባው |
| አልመጅዲ | ታላቁ (የአላህ ስም) |
| አል ቀዩሙ | የተብቃቃው |
| አል ቁዱሱ | ቅዱስ የሆነው |
| አሙዋት | ሙታን |
| አምቢያ | ነቢያት |
| አረሂሙ | አዛኙ |
| አሪህማኑ | ሩህሩኑ |
| አኸይራ | የመጨረሻው ዓለም |
| አዛን | የስግደት ጥሪ |
| አጀል | የዕድሜ ገደብ |
| ኡለማ | አዋቂዎች |
| ኢማን | እምነት |
| ኤብሊስ | ዳቢሎስ |
| ኪታብ | መጽሐፍ |
| ኬኔ | ምስጢር |
| ዘካ | ግዴታ የሆነ ምጽዋት |
| ዘካሪ | አወዳሽ |
| ዙልም | በደል |
| ዚና | ውዳሴ |
| ያሀቢቡላሂ | አንተ የአላህ ወዳጅ |
| ዲን | ሐይማኖት |
| ጀሀነም | ገሃነም |
| ጀምአ | ሕብረት |
| ጀሳድ | አካል |
| ጃሂል | መሐይም (የማያውቅ) |
| ጅስም | ሰውነት (ገላ) |

## አባሪ አንድ፡ በቃለ መጠይቅ ወቅት የቀረቡ ዋና ዋና ጥያቄዎች

1. የመውሊድ ክብረ በዓል ለምን ይከበራል? ታሪካዊ አጀማመሩ ምን ይመስላል?
2. የመውሊድ ክብረ በዓል የእምነቱ ተከታዮች መቼ እንዴት ያከብሩታል? በምን አውድ?
3. የከበራው አጠቃላይ የክዋኔ መዋቅር ምን ይመስላል?
4. በክብረ በዓሉ ላይ የሚስተዋሉ ዋና ዋና ሁነቶች ምን ምን ናቸው?
5. በመውሊድ ክብረ በዓል መንዙማን ለማቀንቀን (የክዋኔው መሪ ለመሆን) ምን ያስፈልጋል?
6. መንዙማ ከመውሊድ በአልስ ጋር ምን ቁርኝት አለው?
7. የመንዙማዎቹ ደረሳ መቼና እንዴት ይከናዎናል? የተፈቀደውስ ለማነው?
8. የመከበሩ አጠቃላይ ማህበራዊ (ለእምነቱ ተከታዮች) ፋይዳውስ ምንድን ነው?

## አባሪ ሁለት፡ መረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | እድሜ | ጾታ | መኖሪያ አካባቢ | የስራ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐጅ ሐሩን ሙሳ | 56 | ወ | አዲስ አበባ፡ መርካቶ | የታላቁ አኑዋር መስጊድ ኢማም |
| 2 | ሐጅ ሙሀመድ ኑር አብደላ | 39 | ወ | አዲስ አበባ፡ ጎጃም በረንዳ | (በአኑዋር መስጊድ መንዙማ በመክተብ(በመጻፍ) የሚተዳደሩ ግለሰብ) |
| 3 | አቶ ሙሀመድ ያሲን | 41 | ወ | አዲስ አበባ፡ ከወሎ የመጣ | ለተፍሲር ትምህርት ከክፍለ ሀገር የመጣ ደረሳ |
| 4 | ሼህ ሙሐመድ አብዱላሒ | 47 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | በንግድ የሚተዳደር |
| 5 | ወይዘሮ አሚነት ሙሳ | 55 | ሴ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | በንግድ ስራ የምትተዳደርና መውሊዱን በዓል ላለፉት 30 አመታት የተሳተፈች |
| 6 | አቶ ኡስማን ሰኢዱ | 42 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | በንግድ ስራ የምትተዳደርና መውሊዱን በዓል ላለፉት 25 አመታት የተሳተፈች |
| 7 | ሼህ አብዱልቃድር ፈድሉ | 54 | ወ | የጎንደር ከተማ ነዋሪ | በንግድ የሚተዳደርና ላለፉት 17 ዓመታት በበአሉ ላይ የተሳተፈ |
| 8 | ሼህ ሲራጅ ጀማል | 48 | ወ | የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ | መንግስት ሰራተኛና ላለፉት 6 አመታት |
| 9 | ሐጅ ሙሐመድ ከማል | 38 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | ላለፉት 18 አመታት በበአሉ ላይ የተሳተፈ |
| 10 | ሼህ ዳውድ ፋሪስ | 46 | ወ | የመተከል ከተማ ነዋሪ | በንግድ ስራ የሚተዳደርና መውሊዱን በዓል ላለፉት 24 አመታት የተሳተፉ |
| 11 | ከሼህ አብዱሰመድ ሙሀመድ | 52 | ወ | የደሴ ከተማ ነዋሪ | (ከወሎ የመጣ መንዙማ አቀንቃኝ) |
| 12 | ሼህ ኡስማን ሞላ | 49 | ወ | የቆቦ ከተማ ነዋሪ | (ከወሎ የመጣ መንዙማ አቀንቃኝ) |
| 13 | አቶ አሳየ አንተነህ | 52 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | የዳንግላ ከተማ አስተዳደር ቅሬታ ሰሚ (ይህ ሰው ለረጅም በባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ያገለገለ ነው) |
| 14 | ወ/ሮ ጸደኒያ ግርማይ | 28 | ሴ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | የዳንግላ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ኮምንኬሽን ጽ/ቤት ሀላፊ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 15 | ዶ/ር ሲዳጅ ጡሐ | 32 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | የዳንግላ አንድነት ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የአካዳሚክስና ምርምር ምክትል ዲን |
| 16 | አቶ ዋለ አለም ቀረ | 30 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | የዳንግላ ከተማ አስተዳድር የገንዘብና ኢኮነኖሚ ልማት ጽ/ቤት ሀላፊ |
| 17 | ወ/ሪት ፋጡማ አስፋው | 27 | ሴ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | በዳንግላ ከተማ አስተዳድር የገንዘብና ኢኮነኖሚ ልማት ጽ/ቤት ኦፊሰር |
| 18 | አቶ ሱሌማን ጠሀ | 26 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | ነጋዴ (በፊት በዳንግላ መሰናዶ ት/ቤት ለ7 አመታት ያስተማረ) |
| 18 | አቶ መኳንት ብርሀኑ | 38 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | የዳንግላ ከተማ አስተዳድር ከንቲባ ጽ/ቤት ኃላፊ |
| 19 | አቶ ጀማል ፈንታው | 27 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | የዳንግላ ከተማ መሰናዶ መምህር |
| 20 | አቶ በየነ መርሻ | 76 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | በንግድ ስራ በግሉ የሚተዳደር |
| 21 | ሐጅ ሙሀመድ ሐሰን | 79 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | በግል ስራ የሚተዳደር |
| 22 | አቶ ከድር ቢሻው | 35 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | በንግድ ስራ የሚተዳደር |
| 23 | አቶ ሙሀመድ አሊ | 42 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | በመንግስት ስራ የሚተዳደር |
| 24 | ወ/ሮ ከድጃ ኢሳ እና | 52 | ሴ | የባህር ዳር ከተማ ነዋሪ | በንግድ ስራ የምትደዳደር |
| 25 | ወ/ሮ በለጡ ጀማል | 41 | ሴ | የጎንደር ከተማ ነዋሪ | በመንግስት ስራ የምትተዳደር |
| 26 | ወጣት ሙሀመድ በድሩ | 29 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | በንግድ ስራ የሚተዳደር |
| 27 | ወ/ሮ በለጠች ሙጨ | 44 | ሴ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | በንግድ ስራ የምትተዳደር |
| 28 | ሼህ አህመድ ሀሚድ | 56 | ወ | የጎንደር ከተማ ነዋሪ | በንግድ ስራ የሚተዳደር |
| 29 | ወ/ሮ ዘምዘም ከድር | 39 | ሴ | የባህር ዳር ከተማ ነዋሪ | በመስግስት ስራ የምትተዳደር |
| 30 | ወ/ሮ ከድጃ ግርማ | 28 | ሴ | የዱርቤቴ ከተማ ነዋሪ | በንግድ ስራ የምትተዳደር |
| 31 | አቶ ሐሽም ኢብራሒም | 25 | ወ | የዳንግላ ከተማ ነዋሪ | በንግድ ስራ የሚተዳደር |

## አባሪ ሶስት፡ በሼህ ሁሴን አለሙ መውሊዱ ላይ ከሚባሉት የመንዙማዎቹ ግጥሞች፣

### *ግጥም 1*

*ቢስሚላሂ ረህማን ረሂይም (2 ጊዜ)*

*አላሁመ ሶሊ ዐላ ዘይኒል ውጁድ*

አልሀምዱ ሊሏሂ ዚይል ጀዋድ፤

ዩዕጢይ ወምነዑ ማዩሪይድ፤

ማሊከል ሙሉውኪ ዳኢመን ሙሰርመድ፡፡

ያአሏህ ያረህማን ያረሂይም፤

ቀልባችንን አርገው ረሂምይ፤

እሚያዝን የሆነ ለባዳ ለዘመድ፡፡

ያአሏህ ያማሊክ ያቁዱውስ፤

ቀልባችን ያረቢ አይደፍርስ፤

አንችለውምና ያረቢይ ያሶመድ፡፡

ያአሏህ ያከሪይም ያጀዋድ፤

ሸልመን ዘይነን በአውራድ፤

እሚያደርስ የሆነ ከሀድረተ ሹሁውድ፡፡

ያአሏህ ያወሓብ ያሀናን፤

ቀልባችንን ሙላው በኢማን፤

እንዲያምር ስራችን በቀጥታው መንገድ፡፡

ያአሏህ ያሙውእሚን ያሠላም፤

እባክህ አኑረን በሠላም፤

ሸሪዐውን ለቀን እንዳንወጣ መንገድ፡፡

ኣንተ ዙልጀላሊ ወልኢክራም፤

አርገው ኑሮአችነን በሰላም፤

በሶፋ በወፋ ሰፋ ባለው መንገድ፡፡

ያአሏህ ያዐዚይዝ ያጀባር፤

ነዊርና መቲዕና ቢልአሥራር፤
ቢለይሊ ወነሓር ያረቢ ያሶመድ።
ያአኋህ ያከቢይር ያኻሊቅ፤
ኢሽረህ ሱዱውረና ቢተውፊይቅ፤
ቢጦዐህ ወልቀቡውል ወቡሉውጊልመራም።
ነሥአሉከል ዐፍወ ወልሀያት፤
እግፊር ዙኑወበና ወዘ ላት፤
ወኣንተ ዳኢሙ ዙውልሙልኪ ወልአበድ።
ማላዐይኑን ረኣት ኣዕጢይና፤
ኢላ አኺሪሂ ረበና፤
ጁድ ለና ሐብ ለና ያፊያዶል መደድ።
ያኻሊቀ ለይሊ ወናሐር፤
እምላእ ቁሉበና ቢልአሥራር፤
ኣንተል ሙቀዲሩ ፊዱኒያ ወፊል ገድ።
ያገኒይ ያሙግኒይ ኣግኒና፤
ቢጃሂ ሙሀመድ ዙኸሪይና፤
ወአንተል ሙጅይቡ ላቱህሊፉል ሚይዓድ።
ያአኋህ ያገፋር ያቀሓር፤
ኢግፊር ሀውበተና ያሠታር፤
ቢሣትሪከል ጀሚይል ያረቢ ያኣሀድ።
አንተል ሙሶዊሩ ያባሪይ፤
ኣኽሪጅ ፊይ ቀልቢነል አግያሪ፤
ኣለዚይ ዩሽጊሉ ዐን ጦዓቲል ወዱውድ።
ያአኋህ ያለጢይፍ ያረዛቅ፤
ሐብለና ወርዙቅና ያኸላቅ፤
ወኣንተል ሙዒይኑ ዐላ ኩሊ ኣሀድ።
ያአኋህ ያፈታህ ያዐሊይም፤
ዐሚር ቁሉበና ቢልዑሉውም፤

ዒልመን ሀቂይቂየን ያረቢይ ያማጅድ።

ክፈትልን ደጉን ጥሩውን፤

ያረቢይ ያረቢይ ቀቡውሉውን፤

ካልተገኘ ቀቡውል የለም የሚፈይድ።

ያአሏህ ያቃቢድ ያባሢጥ፤

ውስጣችንን አርገው ሙንበሢጥ፤

የተሞላ በኢሽቅ የለለበት ነከድ።

ያአሏህ ያኻፊድ ያራፊዕ፤

እጅዐልና ኢላሒይ ዙውልቃኒዕ፤

ቀናዓን ካሚለን ለይሠ ፊይሂ ነፋድ።

ያአሏህ ያሙዒዝ ያሙዚል፤

አርቅልን ከኛ ጅላጂል፤

ነፍሥያና ሐዋ ከሸይጣንም ማሪድ።

ለኛ ጠላታችን ነፍሢያ፤

ጠቃሚዋን አትወድ ውድመኛ፤

ያረቢይ መልሣተ ሣትገባ ከለህድ።

ያሠሚይዕ ያበሢይር ወልውለን፤

ወንጀልን አላቀህ ሰው አርገን፤

በዛ ብሏልና የሸይጧኑ ጁኑውድ።

ያአሏህ ያሀኪይም ያዐድሉ፤

እባክህ አሽረን በሙሉ፤

ፍርሻ የለለበት ለመንገዱ ስንሄድ።

ያአሏህ ያዃሒር ያኸቢይር፤

ምላሳችን ይሁን ለዚክር፤

አይሁን ሠበህለላ ላረባ ለፈሣድ።

ያአሏህ ያሀሊይም አስችለን፤

በመቻል ከራማ ሸፍነን፤

አንተ የሰተርከው የለበት መዋረድ።

ያአሏህ ያገፉር ያሸኩውር፤

አዱንያም አኺይራም አርገው ገር፤
ኢላሒይ መውላየ ያኻሊቀል ዒባድ።
ያአሏህ ያዐሊይ ያከቢይር፤
ዐይሻችንን አርገው ገር በገር፤
ያማገረ ሆነ የለለበት ከሠድ።
ያሀፊይዝ ያሙቂያት ጠብቀን፤
ከሣሂርም ሁላ ከኩሓን፤
ያረቢይ አትፈትነን በክፉ በሃሲድ።
ያሀሚይብ ያጀሊይል ያአሏህ፤
ጠብቀን ከፊትናህ ከበላህ፤
ስለማንችለው ቀድርህን በመውደድ።
ያረቂይብ ያከሪይም ዘይነን፤
ቢኹሉቂን ዐዚይም ቀምቅመን፤
ያአሏህ ያአሏህ ያፈታህ ያሶመድ።
ሠርተው እንዳልሠሩ ከመሆን፤
ያሄሒር ያባጢን ጠብቀን፤
በየወቅቱ ሁላ በሰው ከመናደድ።
ያሙጅይብ ያዋሂዕ አስፋፋን፤
በጥቅል በጅምላ ሣይጎለን፤
በልጅ በልጃችን አድርገው ያጀዋድ።
ያሀኪይም ያወዱድ ውደደን፤
ወደህ አስወድደህ አጋጥመን፤
ከወንድማችን ጋር እንድንፈያየድ።
ውጼታው ፋይዳውም ከሡ ነው፤
በአምሩ መስራትን ለመነው፤
በቁርኣን በሀዲይስ አስታውቆናል መጅይድ ።
የባዒስ ያሀቁ ሀቂቅና ፤
ቢልአምር ወነሕይ አቂምና ፤

ኣንተልሙደቢሩ ያአኳህ ያሽሒይድ።
ዐላ ጧአቲከ ቀዊይና ፧
ወሚን ዒስያኒከ ጀኒብና፧
ወኣንተል ሙቀዊይ ዐላ ኩሊ ኣሀድ።
ያወኪይል ያቀዊይ ያዋሊይ፧
ኣልቢስና ሊባሰን ኑውራኒይ፧
ቢሁርመቲ ነብይ ቢመቃሚል መህሙውድ።
ዓፊየተን ካሚል እደለን ፧
ከዘመን ከወቅቱ አጋጥመን ፧
ሣታረገን ዘንበል ከሀቂቃው መንገድ ።
ያሀሚይድ ያሙህሲይ ያመቲይን ፧
ኢህፊዝና ያሣቲር ሚን ኻኢን፧
ወሚን ኩሊ ሸሪ ወኩሊል ሙዓኒድ።
ያሙብዲእ ያሙዒድ ያሙሚት፧
ያሙህይ ጠብቀን ከውሸት፧
ከገሽም ከሜትም ነገር ከማዋሠድ።
ከነዚህ ነገሮች ከኒህ ጉድ፧
ጠብቀን ያዋጅድ ያማጅድ፧
ቢጃሂል ሙስጦፋ ቢሠይዲል ውጁውድ።
ወሙውአሊፉሁ ሁሠይን፧
ሙሪይዱል ሙካሽፍ ቢልየቂን፧
ያረቢይ ኣሒልሁ ሊፊይዷቲል መደድ።
ሶላት ሰላም ይውረድ በኣህመድ፧
ሹመቱ የሁነ ለአበድ፧
በኛ ረሡውል ነቢይ ሙሀመድ ሙሀመድ።
ደግሞም በአስሀቦች በጀግኖች፧
ሸሪዓን ሀቂይቃን መሥራቾች፧
መሠረተ ትልቅ ሁለዚየ እሚጀደድ።

## *ግጥም 2*

*ሶለአ<u>ሏ</u>ሁ ዐላ ሙሀመድ፤*

*ሶለአ<u>ሏ</u>ሁ አለይሂ ወሠለም።*

አልሀምዱ ሊ<u>ሏ</u>ሂል ሀሊይም፤
ወኒዕመል ጀዋዲ ረሂም።
አልሀምዱ ሊ<u>ሏ</u>ሂል ከሪይም፤
ወኒዕመል ወሓቡል ዐሊይም።
አልሀምዱ ሊ<u>ሏ</u>ሂል ሙንዒይም፤
ወኒዕመል መናኒል ሀኪይም።
ነሥኣሉ ሪዷ ያዐሊይም፤
ቢፈ<u>ድ</u>ሊን ሚንከ የረሂይም።
ለመነህ ኣንተ ያከሪይም፤
ዲይነን ወዱንያ ሁሉንም።
ያረቢይ ኣንተ ያቀዲይም፤
አርገነ ከመጅሊስ ግጥም።
ያረቢይ ኣንተ ያዐ<u>ዚ</u>ይም፤
አርገነ ሁለዚያ ሠሊይም።
ከኒፋቅ ከዚና ከ<u>ዙ</u>ልም፤
ከሂስድም ደሞ ከሜየትም፤
አበራ ኑውሩል ሙ<u>ስ</u>ጦፋ፤
በኸልቁ ሁላ ዘላለም።
ወንተሸር ሂሩል ሙ<u>ስ</u>ጦፋ፤
ዐላ አህሊ<u>ሏ</u>ሂል ኪራም።
ኣንተ ባቡእ<u>ሏ</u>ሂል አዕ<u>ዘ</u>ም፤
የሁሉ መውጫ ነው ሡለም።
መንበዑል ዒ<u>ዚ</u> ወተከሪይም፤

ካሳንቱ ኒዟም አያምርም፡፡

ባንቱ ነው ያስገኘው ሀኪይም⁝

ሠማይ መሬቱን ሁሉንም፡፡

ያበድሩል ያሚሩል ዓለም⁝

ፈይዱከ የሠዑል ዓለም፡፡

መን ሶለ ቢቀልቢን ሠሊይም⁝

የሐቡ ዐለይሂ ነሚይም፡፡

መን ሶለ ዐለል ሙከረም⁝

ወሶለ ሀድረተል ኪራም፡፡

መን ሶለ ዐለል ሙዐዘም⁝

ቀልቡሁ የኩውኑ ሠሊይም፡፡

ከይፈ ላየኩውኑ ሠሊይም⁝

መህቡውቡ ነቢዩል ዐዚይም፡፡

ቢዚክሪክ ነቢዩ ተራነም⁝

ኢህዋኒይ ኣንተ ያፈሒይም፡፡

ሠይዲ ሙዚይሉ ዘላም⁝

ኢስሙሁ ሺፋኡል አሥቃም፡፡

ዐሊምና ኣንተ ያዐሊይም⁝

ቱውጀዱ ቢእሥሚሂ ነዒይም፡፡

ኩሉ ኒዕመቲን ወጧዓም⁝

ሚን ሚሪ ጦሃ ሙከረም፡፡

ቢጃሂ ሀያተል ዓለም⁝

ሰቢትና ረቢይ ያቀዩም፡፡

በአንቢያ በሙርሰሉዎችም⁝

ስጠነ ጀነተ ነዒይም፡፡

ባራቶች ኹለዎችም⁝

አርገነ በሱናው ቃኢም፡፡

በአስሃባ ኣህለል በይቶችም⁝

ከሀቁ አርገነ ግጥም፡፡

ባራቱ ኣኢማዎችም፧

ወፊቅና ሊፈይዷቲሒም፡፡

በአኽያር በአቅጧቦችም፧

ከኸይራት አርገነ ግጥም፡፡

በአብዳል በአውታዶችም፧

አታልፋን በለለው ጥቅም፡፡

በኑቀባ በኑጀቦችም፧

ያዝልን ሸረኛን ዟሊም፡፡

በወሊይ በወልያትም፧

ጠብቀን ከሸርካ ግም፡፡

ቢኣምይን ወህዩ ጅብሪል፧

ጁድ ለና ኒዕመተን ዐሚይም፡፡

ነጅይና ሚን አምሪ ሙሒም፧

ኢላሒይ ቢኢስሚከል አዕዟም፡፡

ያረቢ ሠሊም ያሠላም፧

በሺርና ቢሁሥኒል ኺታም፡፡

መኪይና ቢአምከኒ ታም፧

ቢጃሂ ሚስባሂል ዓለም፡፡

ኢላሒይ መደደል ወፋ፧

የሆነ የሞላ ተማም፡፡

በዐዲል ሀርፊ ኩሊሂም፧

የንዚሉ ሶላት ሠላምም፡፡

ዐላ ሙሀመድ ዚይ እረሂይም፧

ወዐለል ኣሊ ኩሊሂም፡፡

*ግጥም 3*

***አሏሁ ያአሏህ አሏሁ አረህማን፤ (2 ጊዜ)***

***ቢጃሂ ሙስጦፋ ኣሁን ፈርጀን፡፡***

ቢስሚሏሂ ብለን ብዙ እናመስግን፤

ለኣለሙ ሺፋ ኡመት ላረገን፡፡

ብታመሰግኑኝ ልጨምር አለን፤

እንዲህ ያለ ሲሆን ምን ዝም አሰኘን፡፡

በሙልክህ በቁድራህ አርቅ ሠታሪን፤

ዐዱው ሽይጧንን ውድቅ አድርግልን፡፡

ያረህማን ያረሂይም አሁን አርግልን፤

በኸለቅከው ነቢይ አድርገህ መዕዲን፡፡

ያማሊክ ያቁዱውሥ በረህመት ሙላን፤

በሙሀመድ ኣሚይን ባረከው አማን፡፡

ያሠላም ያሙውእሚን ሰሊይም አድርገን፤

በላይም በውስጥም እማንኸይን፡፡

ዙውልጀላል ወልኢክራም ኣንተል መሒይሚን፤

ጥቅልል ሽክፍ አርገህ ከሀድራህ አግባን፡፡

መን ካነ ፊይል ሀድራ የኩውኑ ኣማን፤

ሚን ወስዋሢ ናሲ ወሚነል አጅናን፡፡

ያዐዚይዝ ያጀባር ጠግነን አሁን፤

ደካማ ጅሎች ነን ብልሀትም የለን፡፡

ያከቢር ያኻሊቅ ደግ ኸለቅልን፤

ሁልጊዜም ኻሊቅ ነህ በተሎ አሁን፡፡

ጌታየ መውላየ ለመነህ አሁን፤

በዱንያም በአኺይራም አታመናትለን፡፡

ለምኑኝ ብለህል ግጠመን አሁን፤

በሁለቱም አገር አታሳፍረን፡፡

ወንጀለኛ ኡመት ባሪያዎችህ ነን፤
የሀቂቃ ኡመት እባክህ አርገን።
ቅርብ ነው ፈረጃህ አሁን ፈርጀን፤
ካንተ በቀር ሌላ መድረሻም የለን።
ኣሗሁል ባሪይኡ ኣንተል ሙሶዊር፤
በደህና በሰላም በኑውር ዘይነን።
ኸይሩን ነገር ሁላ ገር ገር አርግልን፤
ኣንተ ስታገራው መቸም አይጠናን።
ያገፉር ያቀሓር ማረን ታረቀን፤
ነፍሥያና ሐዋ አትረክብብን።
አዱኒያና ኒሳእ ደሞ ሸይጧንን፤
የኒህን መካይድ አንተ ያዝልን።
ያወሓብ ያረዛቅ እርዘቀን ደጉን፤
ዳኢም ቀላቢ ነህ ሰውን አውሬውን።
መኸሉቃትን ኸልቀህ እማትረሳነን፤
በብልሃት በቁዋ እኛ መሰለን።
ያፈታህ ያዐሊይም ክፈተው ኸይሩን፤
መቸም ታውቀዋለህ ያለንበትን።
ያቃቢድ ያባሲጥ አትጨብጥብን፤
ቀልባችን ዶዒፍ ነው መቻልም የለን።
ያኻፊድ ያራፊዕ በመቃም አርገን፤
ኣንሶ እሚያሳንስን ኣንተ አርቅልን።
ያሙዒዝ ያሙዚል አታኋድልብን፤
በኢማን በአማን አርገህ አኑረን።
ያሠሚይዕ ያበሲይር ወልውለን ኳለን፤
የውስጡም የላዩም ይገለጥልን።
የማይሸነግለን የስቲድራጅ ያልሆነ፤
ከብዙ ስጦታህ ገምበር አርግልን።

ያሀከም ያአድሉ በሀቅ ቀጥ አርገን፤
ከእውነቱ መንገድ አታዘናብለን።
ያለጢይፍ ያኸቢይር እዝነት እደለን፤
ኸይራትን በመስራት በዲን ሰው አርገን።
ያሀሊም ያዐዚይም መቻል እደለን፤
ባረባ ንግግር አታነጋግረን።
ያገፉውር ያሸኩውር አመስጋኝ አርገን፤
ባጣቀምከን ሁሉ አንችልም ቁጥሩን።
ያዐሊይ ያከቢይር ካሚል አድርገን፤
ከሸሪዓው መንገድ ጠመም አታርገን።
ያሀፊይዝ ያሙቂይት ጠብቀን ሽሩን፤
መቸም ጠባቂ ነህ ትንሽ ትልቁን።
ያሀሲይብ ያጀሊል ስጠን ዋናውን፤
ውዴታና ተቅዋ ደሞ ማርታህን።
ያከሪይም ያረቂይብ ልግስ አርግልን፤
ዘላለም ለጋሽ ነህ እማሰለቸን።
ያሙጅይብ ያዋሲዕ መርሀባ በለን፤
ተለማኝ ጌታ ነህ ተሎ ወፍቀን።
ያሃኪይም ያወድውድ ሀቅ አስወድደን፤
ሀቅ የያዝነ ጊዜ ሁሉም ወደደን።
ከጠማማ በቀር ዋይ የለው ለዲይን ፤
ኪታብም ቢቀራ ያልቀራም ቢሆን።
ዲይኑውን ሣንይዘው ሁሉ ቢወደን፤
ልግዛ እንደሚል ሰው ነው ሳይዝ ዋጋውን።
ኣዱንያን በሙሉ የገዛ ነበር፤
ሸዳድ የሚባል ሰው አሽደ ጡግያን።
ጌታየ ከሪይሙ ለዲይን አህል አርገን፤
ጠማማን አቅንተህ ያንተ ሰው አርገን።

ያመጅይድ ያባዒስ በኸይር አላውሠን፤
እኛ ለመላወስ ቺሎታም የለን።
ያሸሒይድ ያሀቁ በሀቅ ኣቁመን፤
ለትልቅ ለትንሽ ዟሊም አታርገን።
ያወኪይል ያቀዊይ አጥናን አስጠጋን፤
አንተ ካስጠጋሀን ፍራትም የለን።
ያወሊይ ያሀሚይድ ከብካቢ ሁነን፤
በዱንያም በአኺይራም ሙሽር አድርገን።
ያሙሀሲይ ያመቲይን ባሉቅዋ አርገን።
ኣዛና ሽያጢይን እንዳይዶርረን፤
ያሙብዲይእ ያሙኢይድ አሣምርልን።
ኑሯችን በተውበት ስንሞት ኺታምን።
ያሙህይ ያሙሚይት መይት አታርገን፤
መርሳት መዘንጋትንከቀልብ አውጣልን።
ነሥአሉከል ሀያት ከዓፊያ ጋር፤
ቢጃሂ ሙስጦፋ ሩውሂል አክዋን።
ያዋጅድ ያማጅድ ቀልበ ጥሩ አርገን፤
በውሸት በወሬ ደፍራሽ አታርገን።
ያዋሂድ ያሶመድ ባሪያየ በለን፤
በሙስጦፋ መንገድ ሠሪ መሪ አርገን።
ያቃዲር ሙቅተዲር ቀድረው ኸይሩን፤
ቀድርሀን ለመጥላት አትላክብን።
ወላቱሀሚልና ያሀናን ያመናን፤
ቢማላ ነሀሚሉ ረቢ ያደያን።
ሙቀዲም ሙአውኺይር ቀዳሚ አድርገን፤
ከኸይር እጣ ሁላ በኋላ እንዳንሆን።
ያዟሂር ያባጢን ኑውሩን አብራልን፤
ከሽርክና ከሽክ እሚያጦሀራን።

ያዋሊይ ያሙተዓሊይ በላይ አድርገን፤
ለጂን ለሸያጢን ገባሪ አታርገን።
ያሙንተቂም ያዐፉው ነጻ ወጭ አርገን፤
ከጎሳችን ጋራ በእዝነትህ እየን።
ያበሩ ያተዋቡ ቀቡውል እርዘቀን፤
ከሸር እየጠበክ ደግ አስከለበን።
ያረኡውፍ ያማሊክ ደህና አስመልከን፤
አዛኙ ማውላየ ደል ደል አድርገን።
ያሙቅሢጥ ያጃሚይእ ኣዲል አድርገን፤
ቀልብ በሚያዋልል አትፈትነን።
ያገኒዩ ያሙግኒይ ተብቃቂ አድርገን፤
ከሰው ያለን ኒዕማ አታስመልክተን።
ያማኒዕ ያዷሩ ያዝልን ዱርን፤
ከሴትም ከወንድም ደሞ ከቀሪይን።
ነጅይና ያረቢ ሚን ሱኢል ቀሪይን፤
ቢሁርመቲ ነቢዪ በሕጀቲ ዘማን።
አይጎዳንም ስንል ጨርሶ አወጣን፤
ነገ የቂያማ ዕለት ተተያቂ ነን።
ያናፊዕ የኑውሩ አልብሰን ኑውሩን፤
ኣኺይራ እሚያስጠቅም አስታውቀን ሢሩን።
ያበዲይዕ ያባቂይ ለጀነት አርገን፤
አዱንያ ፈራሽ ነው ቢያምር ቢዘየን።
ያሀዲይ ያዋሪስ ሐብ ለናል ዒርፉን፤
ቢበርከቲ ነቢዪ መግነሚል አክዋን።
ያረሽድ ያሰቡወር ሷቢር አድርገን፤
ሥራ ብንሠራ እንዳይፈስድብን።
ወደፊት የሚገኘኸይራት አውሰን፤
በመጨረሻ ቀን እንዳይቸግረን።

በዘጠና ዘጠኝ ሰምአድርገን ለመን፤
ዱዓችንን መቅቡውል ኢላሂይ አርግልን፡፡
ይውረድ ረህመቱየሞላ በምድር፤
በኸልቁ መብራት ላይ ሙሀመድ አሚይን፡፡
በኣስሃቦችም ላይ ኣቡው በክር ዑመር፤
ሠይድ ዐሊይ እና ሠኺዩ ዑስማን፡፡
በተከታዮችም ባቆሙት ዲኑን፤
ባጢሉን አጥፍተው ባሠፉት ሸርዑን፡፡
በኒህም ተከታይ በሆነ ሙዕሚን፤
ዐደድ የለው ዲካ በለይልም በቀን፡፡

## *ግጥም 4*

***ሺሊሏህ ሠይዲ ሸይኽ ሙሀመድ ባህሩ፤***
***አጊሰና ሠይዲ ሸይኽ ሙሀመድ ባህሩ፤***
***ፈይዱ ረህመቲእሏህ ዐለይኩም ኣስራሩ፡፡***
ቢስሚእሏሂ ብዬ ልጀምር በስሙ፤
በስሙ መጀመር ብዙ እኮ ነው ጥቅሙ፡፡
የነገሩ ሁሉ ሀቃኢቁ ሲሩ፤
ታጥቀው ካልፈለጉት አይገኝ ስመሩ፡፡
በአውሊያዎችህ ሁሉ ለመነህ ገፉውሩ፤
ላኸውፉውን ዐለይሂም ወላሑም የህዘኑዉን፡፡
ወሊይ ብሎ ማለት መቆሙ ነው በኣምሩ፤
ክልክልን በመራቅ ሥራ እያሳመሩ፡፡
ምክር እየሰጡ በየወቅቱ ሁሉ፤
አሏህ ከጠላው ጋር ሳይመሳጠሩ፡፡
ሺሊሏህ ሠይዲ ሸይኽ ሙሀመድ ባህሩ፤
ለጠላው ደራሽ ነው ምን ቢርቅ አገሩ፡፡
ለሰው ቢገለጥ ያለው ከባህሩ፤

አያዩም ነበረ ችለው ሊናገሩ።
እኔስ ይገርመኛል የሰው ነገሩ ፤
ይላል እንዘይር ቀልቡን ሣያጠሩ።
አይታይም መስሎት የቓጠረው ሶድሩ፤
መጀን መጀን ይላል ባፉ በከንፈሩ።
ከእንዲሃለ ነገር ጠብቀን ከሪይሙ፤
መቸም ጠባቂ ነህ ሀሊይሙን ሠታሩ።
ሺሊኋህ ሠይዲ ሸይኽ ሙሀመድ ባህሩ፤
ለሁሉ ሸፋ ነው ለልጅ ለከቢይሩ።
ቀልቡ የቋጠረው ቢገለጥ ለኸልቁ፤
አይለይም ነበር በቀንም በለይሉ።
ይሁንብህ ጀባር በሪጃሉ ሁሉ፤
ኣሽራብና ሸራበን ሚን ሸራቢሒሙ።
በላውን ሙሲይባን ሲያዩት በሚስጥሩ፤
ዱዓ አርጉ ይላሉ እንዲቀል ነገሩ።
ከራማው ብዙ ነው
ተከትቦ አያልቅም የታደለው ሚሩ።
ብዙ ሰዎች አሉ ያልገቡ ከኸይሩ፤
እንዲያው ብድግ ብለው ደርሠው የሚነክሩ።
ባህሩ ዋይ የለው ሲነክር መንኪሩ፤
በተዐጅብ እንጅ በሠራው ጀባሩ።
የሚነክሩ ሰዎች በሣዳቱ ሁሉ፤
ይነሣል ከነሱ የበረካው ጥቅሙ፡፤
አጊስና ሠይዲይ ጂእቱ ኢለይኩሙ፤
ሊቁዳዊይ ቀልቢ ቢደዕወቲኩሙ።
ወመዓ ኣውኣሪይ ጂእቱ ኢለይኩሙ፤
ሊቱምሃ ቀሶድቱ ቢሊቃኢኩሙ።
ስጦታው ይደንቃል የሠይዲ ባህሩ፤

ልግስ አርኀለታል ጌታችን ጀባሩ።
የሙሀመድ ባህሩ የራቀ ነው ሢሩ፤
ከኣህለ ዲይዋኖች የሆነው ሁዱሩ።
ኣይለዩም ነቢይ ከሠይዲይ ባህሩ፤
በመወደድም ከኣሏህ ከገፉውሩ።
ይዓጅባል ይገርማል የጌታ ሚነሩ፤
ከባሪያው ቀልብ ውስጥ ሚስጥሩን ማኖሩ።
ሚስጥር ብሎ ማለት እጅግ ነው ነገሩ ፤
ሌላ እማያውቀው ነው ካልሆነ ገበሩ።
የስጦታው ነገር ብዙ እኮ ነው ወንዙ፤
ባህሩን ቀደደው ገንፍሎ ከስሩ።
ሠይድ ይህን ያህል አፍነውት ኖሩ፤
ፈይዱ ገልቦ እንጅ ነው መቸ ወዶ ባህሩ።
ዱስቱውር ያ ኡስታዚይ ሙሀመድ ባህሩ፤
ከእሱ የሆነን ዒልም ያደለው ጀባሩ።
ሥራው ተፈኩር ነው በቀንም በለይሉ፤
ተከፍቶ እየታየው የቀብሩ ነገሩ።
ሸርዑውን ብለው እንጅ ሸርዑውን ባይጠብቁ፤
ይናገሩ ነበር ኣወሉን ኣሂሩ።
እጅዐልና ኢላሂይ ፊዙምረቲሒሙ፤
ቢሠይዲል ውጁውድ በድሩን ሙተመሙ።
እጅዐልና ኢላሂይ ፊይ ከነፊሒሙ፤
በሙስጦፉል ሓዲይ በድሩን ሙነወሩ።
የንዚሉ ሶላት ሠላም ዐላ ጣሃ ዘይኑ፤
መዓ ኣስሃቢሂ ሲዲይቁ ዑመሩ።
ወሠይዲይ ዑስማን ተቂዩ ሠኺዩ፤
ወሠይዲ ዐሊይ በጦሎል ኣብጡዋሉ።
ወዐላ ኣሊሂ ወመን የሊሒሙ፤

ኢላ የውመልቂያም ማዳመል ኣያሙ።

***ግጥም 5***

## ***<u>ሙሐመድ ነብየ</u>***

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***መርጦ የላከው በውዴታ***

***የሁሉም አይነታ***

አላሀምዱሊላሂ መጣልን ሱሩሩ

ጨለማ አግሎ ዘለቀልን ፈጅሩ

የሙሀመድ ነገር የራቀ ነው ሲሩ

ባንድ ይሆን ነበር ፍየልና ነብሩ

ቢስሚላሒ ብየ ስሙን ላወድሰው

እንዲህ አዘን ብሎ ፈይዱን ከለገሰው

የኒእማው አይነው መቼም ለቀመሰው

የሩህ ቀለብ ብሎ አላህ የደገሰው

ምስጋና ይድረሰው በጣም ለኛ ጌታ

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***መርጦ የላከው በውዴታ***

***የሁሉም አይነታ***

እጅግ በጉዳዩ በፈተኞቹማ

ብዙ ነገር አልፏል ወሬ ስንሰማ

ወንጀል የሰሩ እንደው ዱር ገብቶ ካውድማ

ሰው እንዳያያቸው ወይም ከጨለማ

ይታይ ነበር አሉ በያሉበት ቦታ

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***መርጦ የላከው በውዴታ***

***የሁሉም አይነታ***

ከጀመርኩትማ  ጨርሸ ላውራው

ያለፈውን ሚህና በፊተኛው ሰው

የጌታን ውለታ ሁሉም እንዲያውቀው

በሙሀመድ ሰበብ እንዳቀለለው

ወንድሜ ስማው እንዳይመስልህ ቧልታ

***አላሁም መሰሌ አላሙሀመዴ***

***መርጦ የላከው በውዴታ***

***የሁሉም አይነታ***

ሙሳ ከሊመሏህ የካለ ሹመት

አላህ የሰጦዎት ከራማ ጉልበት

ፊራኦውንን ያጠፉት የዲኑን ጠላት

ሌት ተቀን ተጽናንተው ያን ሁሉ አመት

ጭር ያደረጉት ሁነው በቀጥታ

***አላሁም መሰሌ አላሙሀመዴ***

***መርጦ የላከው በውዴታ***

***የሁሉም አይነታ***

እየው እሰዎ እንኳ ያን ሁሉ ሰርተው

ኡመት ልሁን ብለው ነበር ተመኝተው

ጌታ አለዎት እንጅ አይዞህ አብሽር ተው

የኛን ደረጃችን በተውራፍ ላይ አይተው

ኢኒስቶፊይቱከ ላንቱ አዋጅ ተመታ

***አላሁም መሰሌ አላሙሀመዴ***

***መርጦ የላከው በውዴታ***

***የሁሉም አይነታ***

አደራ እሉሀለሁ አሁንም አደራ

ከድንኳኑህ ዱሉኝ እንዳላይ መከራ

ያረሱሉሏሒ ያአክረመን ወራ

አምኘብሁአለሁ ባይኖረኝም ስራ

እንዳላይ መከራ ነፍሴ ፈቃጅ አጥታ

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***መርጦ የላከው በውዴታ***

***የሁሉም አይነታ***

የሙሀመድ ኡመት የሆነ እንደሁሳ

ከኪታብ ያየውን በቀልቡ የማይረሳ

ትዝታ ተሰጥቶታል በከጀለው ጎሳ

ለመቅራት ሲከጅል ሲሻው እንዲያነሳ

ወይ አውቆት አልተወው ሆነው በቸልታ

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***መርጦ የላከው በውዴታ***

***የሁሉም አይነታ***

ያላወቀ የለም የነቢን መላቅ

ጎራውም ለመነ ልሁን ብሎ ወርቅ

ተው አሉት እንጅ ነቢ አሽረፈል ኸልቅ

አዱኒያን ንቀዋት ብለው ለምታልቅ

ፈርሳ ለምትቀረው ወንጀሏል አስታቅፋ

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***በይደል ምስጦፋ***

***የኡመቱ ሽፋ***

ዋይታ ነገረወት ግመሉ እንደሰው

ግለቱ ጠንቶበት በጣም ቢብሰው

አይዞህ አሉና አዝነው አልቅሰው

ወዲያውኑ ሁር አሉት ገዝተው ከዚያ ሰው

እንደከጀልክ ሁን እንግዲህ አትልፋ

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***በይደል ምስጦፋ***

***የሑመቱ ሸፋ***

ዳመናው አጥሎ በራሰዎ ላይ

ይሰምጥ ነበር ድንጋው ወደታይ

ይጋረድ ነበረ እንዳይሆን ጸሐዩ

ለሰው እንዳይከላ ተመንገዱ ላይ

ሰርንዳው ይሞላል ሸቅብ እየገፋ

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***በይደል ምስጦፋ***

***የሑመቱ ሸፋ***

ያለቀሰው እኮ ጉማጁ ነው ግንዱ

ገደፍ ብለውት ሁጥባ ሲያካሒዱ

በኋላ አበቁና ተመሬት ሲወርዱ

አትልቀቁኝ አለ ሰፈረበት ውዱ

ሊነሱ ቢሔዱ የጦይባው ሸረፋ

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***በይደል ምስጦፋ***

***የሑመቱ ሸፋ***

የመካ ሙናፊቅ የታወረው ልቡ

በሰው ቢመከር በአላህ ሙቅረቡ

አቡበክር ጋራ ወደዋሻው ገቡ

ይጋረድ ቀረበ ሸረሪት እርግቡ

መላይካውም መጣ ለሰው በይፋ

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***በይደል ምስጦፋ***

***የሑመቱ ሸፋ***

አሏህ የሾመውን ላይኖር የሚጥለው

እሱ የሻበትን ያላቅሙ አታግለው

እረህመተል አለም ባላህ አዋጅ ተብለው

እጅጉ ሰው ጠሞ ጥሙ ከለከለው

ቀለሙ በግራ በአዘል ቢጠፋ

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***በይደል ምስጦፋ***

***የሑመቱ ሸፋ***

የተከተበበት የነቢ ሱይፈት

ሀል እና ፊእላቸው ሁሉም ያሉበት

በየኪታባቸው እንዲያው ሲያምኑት

አልቁት የሚል ነው ውደዱ አክብሩት

እኔ አርጌዋለሁ ተሁሉም ሼሮፋ

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***በይደል ምስጦፋ***

***የሑመቱ ሸፋ***

ያልሞከሩት የለም አንድ ያልፈተኑት

ሲህርም አልቀራቸው ደብተራ ድግምት

አፈሰዱት እንጅ በቁርአን አያት

ሂስድ የገፋው ሁሉ በሚስን ቢለፋ

***አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ***

***በይደል ምስጦፋ***

***የሑመቱ ሸፋ***

ተስጋው ሱም አርጋ አንዲት ሴት ሰጥታቸው

ሱም ሆኖብኛል አትብላኝ አላቸው
ለሷ እንጃላት እንጅ ምን አልሆኑ እሳቸው
እንዲያው ለቀራቸው ወንጀሏን አትርፋ
*አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ*
*በይደል ምስጦፋ*
*የኡመቱ ሽፋ*
ኸረ የነሱንስ እንተወው ይቅር
ወሬቸው ሲነሳ ያሳጣል ሶብር
እንግዲያስ ሀምዛ ነው እንግዲያስ ጃፋር
እንግዲያስ አሊ ነው ባለዙል ፊቀር
ጠቅልሎ ሚነዳው እመም እያሰፋ
*አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ*
*በይደል ምስጦፋ*
*የኡመቱ ሽፋ*
ለነቢ የገቡት አወል መጀመር
ታዋቂ አቡበክር ሲዲቀል አክበር
ተልጅ አሊ ነዎት ጀግናው ባለምር
ተሴት ሀድጀት ናት ሲሂበተል ኸይር
ቀጥሎ ቢላል ነው የአሷሒብ ሶፋ
*አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ*
*በይደል ምስጦፋ*
*የኡመቱ ሽፋ*
የኡመርን ድፍረት ጀግንነትን አይተው
ለእስልምና ዶሉት በዱአ ጎትተው
ለሰዎ እጅ ሰጠ ደግ አስመለከተው
የመካን ሙናፌቅ ስንቱን አበቀተው

እያንቀጠቀጠ በራሱ እየደፋ

*አላሁም መሶሌ አላሙሀመዴ*

*በይደል ምስጦፋ*

*የሑመቱ ሽፋ*

***ግጥም 6***

## *አላሁም መሶሌ አሏ መኂመዴ (2)*

## *ጌታዬ እንዴነዎ ምነው ባየነዎ (2)*

ምስጋና ይድረሰው እንደዘየነዎ

ተሞላውም በፊት እንዳየነዎ

በሁሉም ላይ ተሾሞ እንዳየነዎ

ከሌላው በመውደድ እንደለየነዎ

ሂጃብ ገልጠውልን ምናለ ባየነዎ

ገለታ ይድረሰው ለኛ እንዳመጣዎ

ከሁሉም አብልጦ ለኛ እንዳመጣዎ

ከሙሃባ ደርሰን ጌታዬ አንጣዎ

ጌታዬ እንዴነዎ ምነው ባየነዎ

…

አላሁም መሶሌ አሏ መኂመዴ (2)

ጌታዬ እንዴነዎ ምነው ባየነዎ (2)

ሆ ሆ ሆ አጀብ ሆ ሆ ሆ

ቅንድብህ መድመቁ ከጥቁረቱ ጋራ

እኩያት የለውም በሁስኑ የሚጋራ

ስንቱን ገፎ ጣለው የሙሃባው ጋራ

ቢያወሩት አያልቅም የአንቱማ ፊንድልሁ

የሚንተከተከው አይንሁ እንዳጥሚት

እጅግ ያስገርማል የጥቁሩ ጥቁረት

በነጭ ተከቦ በሌለው ብረት

ወደ መቅላት ሄዶ የነጩ ንፃት

በቀዩ ኑር ሆኖ ጥቁር መቀነት

ኩላቸው አይረግፍም የአዘን ነው ከጥንት

በርግጥ አይወራም አጀብ ነው ሁለዎ

ጌታዬ እንዴነዎ ምነው ባየነዎ

አላሁም መሶሌ አሏ መኊመዴ (2)

ጌታዬ እንዴነዎ ምነው ባየነዎ (2)

…

## አባሪ አራት፡ ፎቶ ግራፎች



**አባሪ ፎቶግራፍ 1፡ በክብረ በዓሉ ዕለት ምግብ በመመገብ ላይ የነበሩ የክርስትና እምነት ተከታዮች፤**




**አባሪ ፎቶግራፍ 2፡ ከአቶ ኡስማን ሰኢዱ ጋር በ09/06/2005 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ በማድረግ ላይ፡፡ (ለክርስትና እምነት ተከታዮች በተዘጋጀው ድንኳን ውስጥ)**



አባሪ ፎቶግራፍ 4፡ የሴቶች የጸሎት ማከናወኛ ዳስ (በስተግራ በኩል ከሚገኘው ግድግዳ ላይ የተወጠረው ነጭ ሼራ ምሽት ሴቶቹ ከመድረኩ የሚባለውን የመንዙማና ዳዕዋ ሁነት በቀጥታ በኤል.ሲ.ዲ ፕሮጀክተር አማካኝነት የሚከታተሉበት ነው፡፡)



አባሪ ፎቶግራፍ 4፡ በሴቶች ዳስ ውስጥ ዳዕዋ ሲያደርጉና ሲመራረቁ፤



**አባሪ ፎቶግራፍ 5፡ ከላይ የሚታዩት ምስሎች በወንዶቹ ዳስ ተሳታፊዎቹ ከእድሜ እኩያቸው ጋር ምግብ ሲመገቡ የሚያሳዩ ናቸው።**



አባሪ ፎቶግራፍ 6፡ አቶ ሙሀመድ አሊ (ሼህ ሁሴን አለሙ የተመለከተ መጽሐፍ በማዘጋጀት ላይ የሚገኝ) ግለሰብ በቀን 09/05/2006 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ በማድረግ ላይ።



አባሪ ፎቶግራፍ 6፡ የሌሊቱ የዳዕዋ ስነ ስርአት በወንዶች ዳስ ውስጥ።